# ጥያቄ እና መልስ
# በመንፈስ ቅዱስ ዙርያ

ከትላንትናው ምሽት በኋላ ሁላችንም ተሞልተናል። መንፈስ ቅዱስን ስለተቀበሉ ብዙ ሰዎች መልካም ምስክርነት ዛሬ ሰምቻለሁ። እና ደስተኞች ነን።

2 ከተበርናክሉ ከመጡ አጋሮቻችን አንዱ የሆነውን ወንድም ግራሃም፡ ዛሬ ማታ ከእኛ ጋር በማየታችን ደስተኞች ነኝ፡ በኡቲካ የሚገኘው የሆሊነስ ቤተ ክርስቲያን ፓስተር ነው። እና ወንድም ጃክሰንም፡ ትላንት ማታ፡ እዚህ ተበርናክል፡ እንደነበረ አምናለሁ፡ ዛሬም እዚህ ሊሆን ይችላል፡ ብለውኛል፡ የሆነ ሰው ነግሮኛል... አዎን፡ ወንድም ጃክሰን በታዳሚዎቹ መካከል አሁን አየሁት። ወ—ወንድም ሩዴልስ፡ ዛሬ ማታ እዚህ አለ? እሱም እዚህ በ "62" ካሉት አጋሮቻችን አንዱ ነው። እነሱን መቀበል ደስታችን ነው። ሌሎችም... ኦህ፡ ወንድም ፓት፡ እና—በጉባኤው የምትገኙ፡ ሌሎች ወንድሞች ሁላችሁም እንዲሁ። በዚህ ምሽት ሁላችሁንም በመቀበላችን ደስተኞች ነን።

3 አሁን፡ ምክንያት መደርደር ብፈልግ፡ ትናንት ማታ ከነበረን ታላቅ ጊዜ የተነሣ ጉሮሮዬ ጎርንፏልና፡ ከእነዚህ ታላላቅ ሰባኪዎች መካከል እንዲሰብኳችሁ ማምጣት እችል ነበር።

4 እና፡ ባለቤቴ፡ እርማቴ ናትና፡ ወንድሞች ሆይ፡ የምለውን ነገር፡ ይገባችኋል። ትናንት ማታ ሰናገር የተጠቀምኩበት ይህ ስለነበረ፡ ከኋላ የነበሩ ሰዎች እንዳልሰሙኝ ነግራኛለች። አሁንም፡ ከመጀመሬ በፊት፡ ሙከራ ላድርግ። ምናልባት፡ የተሻለ ሊሆን ይችላል። ከኋላ ያላችሁ አሁንስ ይሻላል? ወይም ይህ የተሻለ ነውን? ይሻላል ወይ? አሁን፡ የኔ ማር፡ ይኸው አንድ ነጥብ አስቆጥሬብሻለሁ። ይኸው፡ ይሻላል ብለዋል። በጣም ጥሩ። ኦህ፡ ማይ! ሴት'ኮ ናት። ድንቅ ነች፡ መልካሚቱን ካገኘኋት ቆየሁ። እሷ ብዙውን ጊዜ ትክክል ነች።

5 እንግዲህ፡ በእርግጥ በእነዚያ ሶስት ሌሊት አገልግሎት ላይ ጥሩ ጊዜ አሳልፈናል፡ እኔም እንዲሁ። አሁንም፡ ከትናንትናው ማታ ካሴት በቀር፡ ሌሎቹ ካሴቶች... ወንድም ጓድ መጥቶ ለተብርናልክል እንዲወስድላቸው ጠራሁት። በኋላ እንደተረዳሁት ግን ለካ ቢሊ ፖል መኪናውን ይዞ ሄዶ ነበር፡ አሁንም እንደማውቀው ከሆነ ቴፖቹ አልሄዱም። ስለዚህ ይህ አልፎብናል። ለቤተክርስቲያኒቱ ሰል—ምናልባት ስለ እምነታችን—የሚጠይቅ ስለሚመጣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ላቆየው እፈልጋለሁ።

6 አሁን፡ ጥያቄዎቹን በጊዜ ከጨረስኩ፡ ዛሬ ማታ **ታላቁ ኮንፈረንስ** በሚል ርዕስ እናገራለሁ። ከዚያ በኋላ፡ ነገ ጠዋት የፈውስ አገልግሎት እናደርጋለን። እና ለታመሙ ሰዎች እንጸልያለን። እንግዲህ፡ ዝም ብለን አንስጥም—ወይም "አሁን፡ አንቺን፡ እና አንተን፡ እንዲሁም አንተን፡" ልውሰድ አልልም። ያ ትክክል አይሆንም። ነገር ግን ካርዶችን ሰብስበን እንበትናለን፡ ከዚያ በኋላ በካርዶቹ፡ ጥቂቶችን ወደ መድረክ እጠራለሁ። ከዚያ በኋላ፡ መንፈስ ቅዱስ መግለጥ

ከጀመረ፡ እና ወደ ጉባኤው ከተንቀሳቀሰ፡ በጉባኤ ያሉትን ሰዎች ለፈውስ አገልግሎት እንጠራቸዋለን። ከዚያም፡ ነገ ጠዋት፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ከፈውስ አገልግሎት ጥቂት ቀደም ብሎ፡ እናገራለሁ።

7 ሚስቴ ስትስቅ እያታለሁ። የኔ ማር፡ በጭራሽ አልሰማሽኝም? ኦህ፡ እየሰማሽኝ ነው። ደህና፡ ጥሩ ነው። ካልተሰማ—እራሷን እንድትነቀንቅ፡ "እ... አይሰማም፡ አይሰማም፡" ለማለት ከኋላ ተቀምጣለች።

8 ስለዚህ ነገ—ነገ ምሽት የውሃ ጥምቀት ያለው የሰብከተ ወንጌል አገልግሎት ይኖረናል። ከዚያ በኋላ፡ የነገ ማታ ሰብከት እንደጨረሰኩ፡ ነገ ማታ መጋረጃዎቹን ወደ ኋላ እንሰባቸዋለን የውሃ ጥምቀትም እናደርጋለን። ጌታ ቢፈቅድ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ማለዳ ወይም ነገ ማታ—በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ መናገር እፈልጋለሁ፡ **ም—ምልክት ተሰጥቷል** በሚል ርዕስ። እና ከዚያ፡ እሮብ ማታ እዚህ ከሆንን፡ ጌታ እዚህ እሮብ ምሽት እንድገኝ ከፈቀደልኝ፡ **ኮከቡን በምስራቅ አይተን እርሱን ለማምለክ መጥተናል፥** በሚል ርዕስ ላይ መናገር እፈልጋለሁ። እና፡ ያም የገና ዋዜማ ነው።

9 ከዚያም፡ ከክሪስማስ በኋላ የክሪስማስ በዓል ሳምንት ነውና። ፊደሎቹ ሁሉ የምንወስድበት ሰፍራ አለ... ወንድም መርሴር እና ሌሎቹ ብዙውን ጊዜ ሁሉንም ይወስዳሉ። ሁሉንም ዘርግፈን፡ ፊደሎቹ ላይ እንጸልይባቸዋለን እና ወደምንሄድበት አለም ጌታ ወደየትኛው ቦታ እንዲመራን እንለምነዋለን።

10 እና፡ እነዚያ፡ ክርስቲያን ቢዝነስ ሜን፡ ታላቅ ጉባኤ አላቸው፡ ይህም ለጉባኤያቸው ወዲያውኑ ፍሎሪዳ ውስጥ መሆኑ ነው። ከዚያ ወደ ኪንግስተን፡ ከዚያም ወደ ሄይቲ፡ እና ወደ ፖርቶ ሪኮ፡ ወደ ደቡብ አሜሪካ፡ በሜክሲኮ በኩል እንመለሳለን።

11 ጌታ ግን ወደ ኖርዌይ እየመራኝ እንደሆነ ይሰማኛል። ለምን እንደሆነ አላውቅም። **ከእግዚአብሔር የተላከ ሰው** የተባለችውን ትንሿ መጽሐፍ ታውቋታላችሁ አይደል? በኖርዌይ ውስጥ ትልቁ ሃይማኖታዊ ህትመት እሷ ናት። እስቲ አስቡት፡ ጌታ በዚያ ያደረገውን ነገር። እና እዚያ በነበርኩበት ጊዜ፡ በታመሙ ሰዎች ላይ እጄን እንድጭን አልፈቀዱልኝም። እዚያም ለሦስት ምሽቶች ነበርኩ። እና በታመሙ ሰዎች ላይ እጄን እንድጭን አልፈቀዱልኝም። ስለዚህ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ተመልከቱ። ህዝቡ እጅግ ብዙ ስለነበረ፡ እኔ ወደ ሰፍራው እንድገባ፡ ህዝቡን ገለል የሚያደርጉ ብዙ ፖሊሶች ፈረሶችን ማዘጋጀት ነበረባቸው። እና በታመሙ ሰዎች ላይ እጄን አልጫንኩም። በርግጥ አንዱ በሌላው ላይ፥ እጃቸውን እንዲጭኑ በማድረግ ጸለይኩላቸው።

12 ስለዚህ... [አንድ ሰው ወንድም ብራንሃምን አነጋገረ—አርታዒ።] አዎን፡ ያለ ጥርጥር፡ አደርጋለሁ። አሁን፡ ነገ ጥዋት... አሁን፡ ዛሬ ማታ፡ ምናልባት ወደ እነዚህ ጥያቄዎች ብቻ እንገባለን፡ ምክንያቱም ጥሩ ጥሩ ጥያቄዎች ናቸው። እና ጌታ ለምን ያህል ጊዜ በእሱ ላይ እንደሚያቆየን አላውቅም። ከዚያ በኋላ፡ ነገ ጠዋት ቢሊ ፖል፡ ጂን፡ ወይም ሊዮ፡ አንዳቸው፡ የጸሎት ካርዶችን ለመስጠት ከሰምንት እስከ ሰምንት-ተኩል እዚህ ይገኛሉ። አሁን፡ ከከተማው-ውጪ-ያላችሁ ሰዎች፡ እንዳትረሱ ደግሜ ልናገረው። ወደ ሰልፉ መምጣት ከፈለጋችሁ፡ ከተቻለ ከከተማው-ውጭ-የሆኑ ሰዎች እንዲሰለፉ እንመርጣለን።

13 አሁን፡ አንዳንድ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲህ ይገጥመናል፡ “እንግዲህ… ” ከከተማው-ውጭ-የሆኑ ሰዎች አሰልፈናል ይሉና፡ ያመጧቸዋል… አንዱም እንዲህ ይላል፡ “እኔ፡ ችግራቸው ምን እንደሆነ አላውቅም። የተሳሳተ ነገር እየነገሩ ሊሆን ይችላል።” ከዚያም በከተማ ውስጥ ሰዎችን ሲያገኙህ፡ “ኦህ፡ ከዚህ በፊት ስለምትተዋወቁ ነው፡” ይላሉ። ከዚያም… እንዲህ ብለው—ይናገራሉ፡ “አይ፡ እኔ ልንገርህ፡ የጸሎት ካርዱ ነው።” እሺ፡ የጸሎት ካርድ ያልያዙትስ? ይህ በሆነ ጊዜ ሁሉ ከቀን ወደ ቀን ይህ አለ…

ምን ይላሉ? [ወንድም ብራንሃም ከማይክሮፎን ኋላ እንዲቆም ተጠየቀ—አርታዒ።] ከማይኩ ጀርባ ሁን? እንግዲህ፡ እንደምታውቁት፡ እኔ ሁል ጊዜ የመንገዱን መሃል እሰብከዋለሁ። ስለዚህ ምናልባት ይሁን ብዬ እቀበለዋለሁ። አይሻልም? ይሻላል። ጥሩ ነው። ምን እንደሆነ እነግራችኋለሁ። የመገናኛ ብዙሃን ዘዴ—ዎቻችን ደካማ ናቸው፡ እጅግ ደካማ። በቅርብ ጊዜ የተሻለውን እንገዛለን ብለን አናስብም፡ ምክንያቱ አዲሱ ተበርናክል በፍጥነት እንዲገነባ እንፈልጋለንና። እና ያን ጊዜ ዙርያውን አስፍተን (አያችሁ? )፡ ሰፍራውን ትንሽ ተለቅ እንዲል ካደረግነው፡ ጥቂት ተጨማሪ ቦታ ካበጀን ሰፊ ቦታ ይኖረናል፡ እና ያን ጊዜ ስለሚኖሩን ለጉባኤው ተዘጋጁ።

14 አሁንም አስታውሱ፡ ከወጣቶቹ፡ ከሶስቱ አንዱ፡ ጠዋት ሰምንት-ተኩል አካባቢ ላይ ካርድ ይሰጣሉ፡ ወይም፡ ከሰምንት እስከ ሰምንት-ተኩል። ይህም ሰውን ሁሉ ተረጋግቶ እንዲቀመጥ ዕድል ይሰጣል። ካርዶችን እንዴት እንደሚሰጡ፡ ለምን እንደምናደርገው ተናግሬአለሁ። ሥርዓትን ለማስጠበቅ ነው። አያችሁ? ለምሳሌ፡ ልክ እንደ አሁን፡ እኔ መጥቼ እንዲህ ብልስ፡ “**ይህች** ሴት፡ **ይህች** ሴት፡ እና **ያን** ሰው፡ እና **ይህች** ሴት ብልስ… ? ” አያችሁ፡ ምን ይሆናል—ከባድ ይሆናል። አያችሁ? እና፡ ከዚያም… ብዙ ጊዜ ይህን አድርጌያለሁ። እና ጠዋት ላይ በጣም ብዙ ካልሆኑ፡ እንዲሁ ማድረግ እችላለሁ። እላቸዋለሁም፡ “የዚህ ከተማ ነዋሪዎች ያልሆናችሁ በውስጣችሁ ግን የሆነ አይነት ችግር ያለባችሁ ስንቶች አላችሁ? እስኪ ቁሙ።”

15 ወንድም መርሴር፡ ስለ ደህንነቴ ትመጣልኛለህን። ትረዳኛለህን? [ወንድም መርሴርም “እረ ስለ ራሴ ደህንነት እመጣለሁ፡” አለ።—አርታዒ።] ኦህ፡ ትመጣለህ… እራሱን ለማዳን እየመጣ ነው። ዛሬ ከሴት ጓደኛህ ጋር ተነጋግሬአለሁ። ስለዚህ፡ ከኔ ጋር ብትሰማማ ይሻልሃል። አየህ? በጣም ጥሩ። ጥሩ ነው። ወ—ወንድም ሊዮን ስለ ጽናቱ አደንቃለሁ። ትክክል በማይሆንበት ጊዜ፡ በቻልነው ያህል እና በምናውቀው በተሻለ መልኩ፡ ለ—ለማስተካከል እንትጋ።

16 ስለዚህ ከዚያ በኋላ፡ ከከተማ-ውጪ-ያሉ ሰዎች ችግር ያለባቸውን እጃቸውን እንዲያነሱ እንጠይቃለን። ከዚያም መንፈስ ቅዱስ እስኪጀምር ድረስ፡ በአንድ ሰው ላይ ተግቼ እጠብቀዋለሁ፡ ከዚያ በኋላ መላውን ጉባኤ ላይ አዳርሰዋለሁ። እስኪ ይህ ሲከናወን እዚህ አይታችሁ የምታውቁ ስንቶች አላችሁ? በእርግጠኝነት! እዩት፡ አያችሁ? ስለዚህ በምንም መልኩ ይሁን ልዩነት አይፈጥርም። ይህ…

17 ማለዳው ላይ እንደገና እንደምመለሰበት፡ ይህንን እንድታስታውሱት

እፈልጋለሁ፡ አሕዛብ፡ የተሰጣቸው ወንጌል የእምነት ወንጌል እንጂ፡ ሥራ አይደለም። አያችሁ? እና ትናንት ማታም ተናግሬዋለሁና። በበዓለ ሃምሳ መንፈስ ቅዱስ በወረደ ጊዜ፡ ወደ አይሁድ ሲሄዱ (ሐዋ 19፡5)፡ ይቀበሉት ዘንድ እጃቸውን ይጭኑባቸው ነበር። ወደ ሳምራውያንም በወረዱ ጊዜም፡ እጃቸውን ይጭኑባቸው ዘንድ ወርደው ነበር። ነገር ግን ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት ወደ አሕዛብ በመጡ ጊዜ ግን፡ "ጴጥሮስ ይህን ሲናገር... " እጅ መጫን አላስፈለገውም።

18 የኢያኢሮስ፡ ትንሿ ልጅ በሞተች ጊዜ፡ ካህኑ፡ እንዲህ አለው፡ "ና እጅህን ጫንባትና፡ በህይወት ትኖራለች።" አሕዛብ የነበረው፡ ሮማዊው የመቶ አለቃ በመጣ ጊዜ ግን፡ እንዲህ አለ፡ "ቃል ብቻ ተናገር፡ ከጣሪያዬ በታች ትገባ ዘንድ እኔ ብቁ አይደለሁምና።" ይኸው ነው። አያችሁ?

19 ግሪካዊት የነበረች፡ ሲሮፊንቂያዊቷ ሴት፡ እንዲህ—ኢየሱስ በተናገራት ጊዜ፡ "የልጆችን እንጀራ ወስጄ ለውሾች መስጠት ለእኔ አይሆንልኝም፡" አላት።

እሷም "እውነት ነው፡ ጌታ ሆይ፥ ግን ውሾችም ከጠረጴዛው በታች የልጆችን ፍርፋሪ ይበላሉ፡" አለችው።

እሱም "ስለዚህ አባባልሽ፡ ጋኔኑ ልጅሽን ለቆ ሄዷል፡" አላት። እንግዲያውስ ጥሩ ነገሮች ተናገሩ። ስለ አንድ ሰው ጥሩ ነገር ተናገሩ። ስለ ኢየሱስ ተናገሩ። ታማኝ የሆነ ነገር፡ እውነተኛ የሆነውን ተናገሩ። አጋንንቶች ማስወገዲያው መንገድ ይህ ነው። ምንም አላለም—ለልጅቷም ፈጽሞ አልጸለየላትም። ስለ መፈወሷም አንዳች ነገር አልተናገረም፥ እንዲህ ብቻ አለ፡ "ስለ አባባልሽ፡ ስለ አባባልሽ... "

20 ሃቲ ራይት፡ በቀደምለት፡ ምንም ነገር አልጠየቀችም። እንዲሁ ቁጭ ብላ ነበረች፡ መንፈስ ቅዱስን የሚያስደስተው ነገር፡ ብቻ ተናገረች። መንፈስ ቅዱስም መልሶ፡ "ሃቲ፡ የፈለግሽውን ነገር ተናገሪ፡ የወደድሽውን የፈለግሽውን በይ። ይህ እውነት ነው ወይስ አይደለም ጠይቁ። አንዳች ነገር ጠይቂ (የአካል ጉዳተኛ የሆነች እህቷም ቢሆን ፈውሱ ተዘጋጅቷል፥ ኮረብታው ላይ ወጥታ ከመቆፈር የሚያሳርፋት አስር ሺ ዶላርም ይሁን፥ የደከመው-አካሏ ወደ ወጣትነት እንዲመለስ)፥ መጠየቅ የፈለግሽውን፡ አሁን ጠይቂ። አሁኑኑ ካልመጣና ካልሰጠሽ፡ እኔ ሐሰተኛ ነቢይ ነኝ።" እ—እንግዲህ ይህ ከበድ ይላል፡ አይደል?

21 ኢየሱስም፡ "ይህን ተራራ እንዲህ በሉት አለ... " እና ከዚያ በኋላ—የሆነውን ነገር ሰምታችኋል፥ እየገባንበት ያለነው አገልግሎት ያ ነው። አሁን በመንገዱ ላይ ተቃርበናል። በቅርቡ የጌታ ኢየሱስ መምጣት ይሆናል። እና በቅጽበት ዓይን፡ በቅጽበት መለወጥ የሚያስችል የመነጠቅ እምነት ያላት ቤተ ክርስቲያን መሆን ይጠበቅብናል፡ ካልሆነ ግን አንሄድም። ይሁን እንጂ አትጨነቁ፡ መሆኑ አይቀርም። መሆኑ አይቀርም። እናም **የዚህች** ቤተ ክርስቲያን ኃይል ሲጨምር፡ ያን ጊዜ ውንድሞችን ያመጣል፥ **የዚያች** ቤተ ክርስቲያን ኃይል ሲጨምር፡ ወንድሞችን ይሰባቸዋል፥ **የዚያች** ቤተ ክርስቲያን ኃይል ሌሎች ወንድሞችን ያመጣል፥ ከዚያ በኋላ ጠቅላላው ንጥቀት ይፈጸማል። እኛም በጉጉት እየተጠባበቅን እንገኛለን።

22 አሁን፡ የጸሎት ካርዶች፡ ከጠዋቱ ስምንት ሰዓት እስከ ስምንት-ተኩል ድረስ እንደሚሰጥ አትርሱ። ከዚያ በኋላ የሰጣችሁትን ካርዶች ሰጥታችሁ፡ አቁማችሁ፡ ወደ ኋላ እንድትመለሱ፡ እና ቁጭ እንድትሉ እሳስባችኋለሁ (አያችሁ? )፡ በርግጥ እስከዚያ ሰዓት ድረስ ሰጥተው መጨረሳቸው የማይቀር ነውና፡ ወይም መምዘዝ የቻሉትን ያህል ይሰጣሉ። ወጣቶቹ ተነስተው፡ በአይኖቻችሁ ፊት ካርዶቹን ይቀላቅሏቸዋል፡ አንድ ከፈለጋችሁ፡ አንድ ትፈልጋላችሁ፡ ወይም ሌላ ተጨማሪም ከሆነ እንዲሁ... ከዚያ በኋላ እኔ ሰገባ፡ እንዲሁ... ጌታ ጥራ ከሚለኝ እጀምራለሁ... እና "በፍጹም አትጥራ፡" ካለኝ፡ ምንም አልጠራቸውም (አያችሁ? )፡ ምንም ይሁን ምን።

23 በርግጥ ደግሞ... ያን አገልግሎት በመደብዘዝ መንገድ ላይ ነው፥ ከዚያ የተሻለ ሊጀምር እየተጠባበቅን ነው። አስታውሱ፡ ከዚህ መድረክ ላይ ወይም ከዚህ ጡልቢት የተነገረ ነገር ሁሉ፡ ፍጹም መሬት ላይ ወድቆ አያውቅም። በእጅ ስለነበረው አገልግሎት ትዝ ይላችኋል? ምን እንዳደረገ አያችሁት? የሰው ልብ አሳብ ማወቅ፡ ምን እንዳደረገ አያችሁት? አሁን ደግሞ፥ ቃል በመናገር፡ ምን እንደሚያደርግ ተመልከቱት። አያችሁ? ከአመታት በፊት ነግሬአችኋለሁ—እዚህ ቤተ ክርስቲያን (ለተበርናክሉ እየተናገርኩ ነው)—ከአመታት በፊት፡ ከሶስት ወይም ከአራት ዓመታት በፊት፡ አንድ ነገር እውን ለመሆን፥ አንዳች ነገር ሊፈጸም እየተዘጋጀ እንደሆነ ተናግሬ ነበር። አሁንም ወደ መሆን እየተቃረበ... እራሱን ቅርጽ እያሰያዘ ይገኛል። አሁን፡ ስለዚያም እናመሰግናለን። ኦህ፡ እጅግ እናመሰግናለን። ደስ ይለናል።

24 አሁን፡ እዚህ አንዳንድ ጠንከር ያሉ ጥያቄዎች ደርሰውናል፡ እና በቀጥታ ወደ እነርሱ መግባት እንፈልጋለን። አንድ ሰው መጻሕፍቶቼን ሁሉ አየ። እኔም "አይ፡ ብልህ ሰው አንዲት ትበቃዋለች፡" አልኩኝ። በርግጥ ብልህ ሰው አይደለሁም። ሁሉንም መዳሰስ ይጠበቅብኛል። እንግዲህ፡ ይህ በሁለት ቋንቋ የተዘጋጀ አዲስ ኪዳን ነው፡ ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡ ይህ ደግሞ የቃላት ማብራሪያ ነው። ስለዚህ... ጌታ እንደ መለኮታዊ ፈቃዱ እና እንደ ቃሉ እንዲረዳን እና ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ እንድንሰጥ እንዲመራን ብቻ እንጠይቀዋለን።

25 እንግዲያውስ፡ ለጸሎት ለአፍታ ብቻ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ። ጌታ ሆይ፡ ባለፉት ሦስት ሌሊቶች ሰላደረግልን ነገሮች ከልባችን ጥልቅ አንተን እናመሰግናለን። ኦህ፡ አገልጋዮች በዚያ ክፍል ተገናኝተው፡ እምነታቸው ሲታደስ እጅ ለእጅ ሲጨባበጡ፡ እ—እና አዲስ እርምጃ ሲሆን አየን። በስልክ መስመር ላይ... ልባችን ደስ ይለዋል፡ ሰዎች ቃልህን—ካዩ በኋላ መንፈስ ቅዱስ እየተቀበሉ ናቸውና፡ መንፈስ ቅዱስን እንዴት እንደሚቀበሉ ደረጃ በደረጃ እንደተነገረው ሆኗልና። ስለዚህም ጌታ ሆይ፡ በጣም እናመሰግናለን።

26 ዝቅ ያሉ ሰዎች ስለሆንን፡ ነገሮችን ቀላል አድርገህልናል። እግዚአብሔር ሆይ፡ እ—አሁንም እራሳችንን ሁል ጊዜ ዝቅ እንድናደርግ፡ እንድትረዳን እንጸልያለን። ምክንያቱ... ራሱን የሚያዋርድ ከፍ ከፍ ይላልና። የዓለምም ጥበብ በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት ነውና፥ በስብከት ሞኝነት የጠፉትን ያድናቸው ዘንድ እግዚአብሔር ወዷልና።

27 አሁንም፡ አባት ሆይ፡ ከቅን ልቦች የተጠየቁ ብዙ ጥያቄዎች እዚህ ከእኔ ጋር አሉ። አንዳቸውም በተሳሰሳተ መንገድ ቢመለሱ ግለሰቡን ወደ ስህተት

ይመራዋል፡ በሚያስጨንቃቸው ጥያቄያቸው ላይ የተሳሳተ ብርሃን መጣል ነውና። ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ መንፈስህ በእኛ ላይ እንዲንቀሳቀስ እና እነዚህን ነገሮች እንዲገልጥ እጸልያለሁ፡ በመጽሐፍም ተጽፎአልና፡ “ጠይቁ ትቀበላላችሁ፥ ፈልጉም ታገኙማላችሁ፥ አንኳኩ ይከፈትላችኋል።” አሁንም እያደረግን ያለነው፡ ጌታ ሆይ፡ የምሕረትህን በር እያንኳኳን ነው። በመለኮታዊው ፍርድህ ጥላ ውስጥ ቆመናል፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለ ክርስቶስ ደም እና ስለ መንፈስ ቅዱስ እንማጸናለን።

28 እናም ዛሬ ሌሊት የመጣነው ከሶስቱ ምሽቶች የመንፈስ ቅዱስ ስብከት ስለወጣን ብቻ ሳይሆን፡ በጥልቅ አክብሮት እና ቅንነት ነው የመጣነው። በምድር ላይ የመጨረሻው ምሽታችን እንደምንኖር ሆነን መጥተናል። ለጸሎታችን መልስ እንደምትሰጥ በማመን ነው የመጣነው። እናም ጌታ ሆይ፡ አሁን በዘላለማዊ ህይወትህ እንድታረካን እንለምንሃለን። አምላክ ሆይ፡ ለቃልህ መልስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ያለኸው፡ ራስህ እንደሆንክ ስለገባን፡ የምንፈልገውን ነገሮች እንድትገልጥልን በዚህ ምሽት እንጸልያለን። ፍላጎታችንም ነፍሳችን እረፍት እንድታገኝ አእምሮአችንም ሰላም እንዲሆን፡ እና ቃል የገባልንን በረከቶች በመውረስ ወደፊት ለመራመድ በእግዚአብሔር ላይ እምነት እንዲኖረን ብቻ ነው። ይህንን በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። ኣሜን።

29 አሁን፡ ከአንዱ በስተቀር፡ የተሰጡኝ ጥያቄዎች ሁሉ ይዣለሁ። ባለፈው ምሽት አንድ ጥያቄ ለጠየቀኝ ታናሹ ወንድም ማርቲን፡ አንድ ጥያቄ መልሻለሁ። ትናንት ማታ ብዙ ነበሩ፡ ግን የጸሎት ጥያቄዎች ናቸው። ወንድም ማርቲን በዮሐንስ 3:16 ላይ ያለውን ጥያቄ ጠየቀኝ—ወይም ዮሐንስ 3፡ ይመስለኛል፡ ስለ፡ “ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር፡ መንግሥቱን ሊያይ አይችልም፡” ስለ ዕብራውያን ላይ ከላኩት ካሴት ጋር አነጻጸረው። እና ባለፈው ምሽት እዚህ ከኋላ ባለው ክፍል ውስጥ አገኘሁት፡ እና—መልስ ለመስጠት ይህ እድል ከማግኘቴ ቀድሜ፡ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ፡ እዚያው መለስኩለት።

30 አሁን፡ ትላንትና ማታ እዚህ ያልነበረ ሰው አለ? ትናንት ማታ እዚህ ያልነበራችሁ፡ እጆቻችሁን እንይ። ኦህ፡ በእውነት፡ ከእኛ ጋር እዚህ በነበራችሁ እንላለን። ድንቅ ጊዜ አሳልፈናል። መንፈስ ቅዱስ...

31 ምናልባት፡ አንድ አፍታ... አይጎዳችሁም። ይህ ተቀድቷል። እና አሁን በምናገራቸው ነገሮች አገልጋይም ይሁን—ግለሰብ አሁን በምላቸው ነገሮች፡ ወይም በጥያቄዎቹ ካልተስማማችሁ፡ ወንድሞች ሆይ፡ እንግዳ ነገር አድርጋችሁ እንዳታስቡት፡ እጠይቃችኋለሁ፡ ይሁን እንጂ—ይህ ቴፕ ቅጂው በገዛ ተበርናክላችን ውስጥ እንደሚቀዳ ማሳሰብ እንፈልጋለን። የምናስተምረው ለራሳችን ህዝብ ነው። ብዙ ከተለያየ እምነት የመጡ አገልጋዮች ተቀምጠዋል። እና እንደገና ወደ ርዕሰ ጉዳዩ ልግባ፡ ምክንያቱም ትላንት ሌሊት መግባት ያልቻሉ አንዳንድ ወገኖቻችን ዛሬ ማታ መግባታቸውን አስተውያለሁ። እናም ከፈቀዳችሁልኝ፡ ትናንት ምሽት በተናገርኩት ነገር ላይ፡ ለአፍታ ብቻ መዳሰስ እፈልጋለሁ፥ ይህም መንፈስ ቅዱስን በመቀበል ዙርያ፡ ስለ በዓለ ሐምሳ ቀን ነበረ።

አሁን፡ ትናንት ምሽት ላይ የነበርኩበትን የግሪክ ትርጉም፡ **እምፋቲክ ዲያግሎት** በማንበብ ላይ ነበርኩ፡ አሁንም በፊቴ ተቀምጧል። ይህም

ከግሪክኛ ወደ እንግሊዝኛ የተተረጎመው ኦሪጂናል ትርጉም ነው። በሌሎች ተርጓሚዎች፡ እና—በሌሎች ዕትሞች በኩል ያለፈ አይደለም፡ ከግሪክ ወደ እንግሊዝኛ በቀጥታ ነው። አሁን፡ የእንግሊዘኛ ቃላቶች፡ ብዙ ጊዜ እንደዚህ አይነት ፍቺዎች አሏቸው፡ ለምሳሌ አሁን board፡ እላለሁ። Board የሚለውን ቃል ውሰዱ። እንዲህ ትላላችሁ፡ "እንግዲህ፡ **አሰልቺ** ማለቱ ነው።" አይደለም! "ኦህ፡ የ—የትምህርት ቤት **ክፍያውን** ከፈለ ነው።" አይደለም! ስለዚህ፡ ይህ... "በቤት ግድግዳ ሰላለው **ሰሌዳ** ነው።" አሁን፡ አያችሁ? ማናቸውም ማለት አይደለም... በዚህ አራት ወይም አምስት የተለያዩ ቃላት፡ መጠቀም ይቻላል፡ ስለዚህ አረፍተ ነገሩን መረዳት አለባችሁ። See የሚባል ቃል አለ። ትርጉሙም ማየት ማለት ነው፡ see በኢንግሊዘኛ "መረዳት" ማለት ነው። sea ማለት ደግሞ "የውኃ አካል" ባህር ማለት ነው። see ማለት ሌላ "መመልከት" ነው። አያችሁ? በእነዚህ ትርጉሞች ላይ ግን፡ ባለፈው ምሽት፡ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 ላይ የተጠቀምኩት ቃል፡ እንዲህ ይላል፡ "የእሳት ልሳኖች በላያቸው ላይ ተቀመጡባቸው... " አሁን; ለአንድ አፍታ ብቻ ወደ ኋላ መመለስ እፈልጋለሁ። ወደ ፊት ከመሄዳችን በፊት፡ ለአፍታ ብቻ፡ እና ለአፍታ ብቻ መከለስ ትፈልጋላችሁ?

32 አሁን፡ ኪንግ ጀምስ ይሁን ምንም ይሁን የምታነቡት... ትርጉም ክፈቱና፡ ማንበብ እፈልጋለሁ። እና በደንብ አዳምጡኝ። በተሳሳተ መንገድ እንዳትረዱት። ዛሬ ብዙ ሰዎች፡ እህቴን ጨምሮ፡ ብዙዎች ደውለዋል፡ እነ... ወይዘሮ ሞርጋን... እና ብዙዎች ትናንት ማታ ነበሩ። ወይዘሮ ሞርጋን ተሰፋ ተቆርጦባት ከነበሩ ሰዎች አንዷ ነበረች፥ እና በሉዊስቪል ውስጥ ከአስራ ሰድስት፡ አስራ ሰባት አመታት በፊት በካንሰር በሟቾች ዝርዝር ውስጥ ነበረች። ዛሬ ማታም በድጋሚ ቁጭ ብላ እዚህ እንደምትገኝ እገምታለሁ። በቀጥታ ወደ ማይክሮፎኑ እየተናገርኩ ሰለነበረ፡ መስማት እንዳልቻለች፡ ነግራኛለች። ስለዚህ ሰለነሱ ሰል ለአፍታ ያህል እንድደግመው እፈልጋለሁ።

33 አሁን፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ከሐዋርያት ሥራ 2 እነባለሁ፥

> ... **በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም** በ**አንድ** አሳብ **ነበሩ**... (አሁን፡ በአንድነት ነበሩ ከሚለው ይልቅ ይህን እወደዋለሁ፥ ምክንያቱም በብዙ ነገር ላይ በአንድነት ልትሆኑ ትችላላችሁ፡ እዚህ ጋር ግን አሳባቸው አንድ ነበር።)... በ**አንድ** አሳብ እና **በ**አንድ **ቦታ**።
>
> **ድንገትም** እንደ**ሚነጥቅ** ዐውሎ ነፋስ **ከሰማይ ድምፅ መጣ፡ የተቀመጡበት ቤትም** ሁሉ... **ሞላው**። (ተንበርክከው ሳይሆን፡ እየጸለዩ ሳይሆን፡ ተቀምጠው።)...
>
> ... የተከፋፈሉ **ልሳኖች**... (T-o-n-g-u-e-s—ልሳኖች። "የተከፋፈሉ" ማለት፡ "ለየብቻ የሆኑ።")... ልሳኖች... **እንደ... እሳት... ታዩአቸው፡ እና** በእያንዳንዳቸው... ("አንድ፡" ነጠላ)... **በእያንዳንዳቸው** ላይ **አረፉባቸው**።
>
> **እና በሁሉም ላይ ሞላባቸው**... ("እና፡" መስተጻምር ነው።)... **ሁሉም** በመንፈስ **ቅዱስ ተሞሉ፡ እና መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው፡ በሌላ ልሳኖች መናገር** ጀመሩ።

> አሁን **ከሰማይም በታች ካሉ ሕዝብ ሁሉ በጸሎት የተጉ አይሁድ፡** በ**ኢየሩሳሌም ይቀመጡ ነበር።**

> ... **ይህም በሆነ ጊዜ**... ይህ ወሬ ከተወራ በኋላ፡ **ሕዝቡ ሁሉ በአንድነት ተሰበሰቡና፡** ተገረሙ፡ **ምክንያቱም...** እያንዳንዳቸው **በራሳቸው ቋንቋ** ሲናገሩ... **ሰምተው ነበርና።**

34 አሁን አስተውሉ! እሳቱ በመጣ ጊዜ፡ ልሳን ነበረ፡ ሲናገሩት ደግሞ፡ ቋንቋ ነበር። አሁን፡ በልሳን እና በቋንቋ መካከል ሰፊ ልዩነት አለ። በኛ ዘንድ ሁሉም ተመሳሳይ ነው። በግሪክ፡ ግን፡ "ልሳን" ማለት **ይህ** ነው። [ወንድም ብራንሃም በምሳሌ አስረዳ—አርታዒ።] ጆሮ **ይህ** ነው። አያችሁ? ቋንቋ ማለት አይደለም፥ ልሳን ማለት የሰውነት ክፍላችሁ ምላስ ነው። ካስተዋላችሁ፡ ሲጻፍ **የእሳት ልሳኖች** ይላል ትርጉሙም "እንደ ምላስ" ማለት ነው፡ ልክ እንደ እሳት ጫፍ፡ እንደ እሳት ነበርልባል ነው። አሁን፡ ምን ማለቱ እንደሆነ አስተውሉ። እያንዳንዳቸው እነዚህ ቦታዎች፡ አትርሷቸው።

35 አሁን፡ አነስ ያለች ድራማ እናደርጋለን። ከዚያ በኋላ ለእናንተ እተወዋለሁ። አሁን አስታውሱ፡ ሁሉም ነገር ተቃራኒ ከሆነ፡ ከራሳችሁ ነው። ነገር ግን ማንም ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ ምንም ነገር የሚያገኝበት ብቸኛው መንገድ በእምነት ነው። እና ከመቻላችሁ በፊት...

36 በማደርገው ነገር እምነት ካማሳየቴ በፊት የማደርገውን ነገር ማወቅ አለብኝ። ሚስትህን ለምን አገባሃት? በእሷ ላይ እምነት ስለነበረህ። ከምን እንደመጣች፡ ማን እንደሆነች፡ ፈትነሃታል፡ አይተሃታል። በእግዚአብሔር ዘንድ፡ የቅዱሳት መጻሕፍት አካሄድ ይህ ነው። ራእዮች እንዲሆኑ፡ የ—የእሳቱ አምድ፡ እና ሌሎች ነገሮች ሁሉ እንዲሆን የሚያደርገው ይህ ነው፡ እግዚአብሄር ቃል ገብቷልና። እግዚአብሔር ተናግሯልና። በቃሉ ፈትኜ እውነት እንደሆነ አወቅሁት። እናንተም ቃሉን ተከተላችሁት። ከዚያ የሆነ ቦታ ትንሽ ግራ መጋባት ካለ፡ የሆነ ቦታ የሆነ ስህተት አለ ማለት ነው። ምክንያቱ እግዚአብሔር (ስሙኝ!)—እግዚአብሔር የራሱ ከሆነው ጋር—ወይም ከሕግጋቱ ጋር የሚቃረን ነገር በጭራሽ አያደርግም። ክረምቱ በበጋው ውስጥ አይመጣም፡ በጋውም በክረምት ውስጥ አይመጣም። ቅጠሎች በፀደይ ወቅት አይረግፉም በመኸር ጊዜም አይመጡም። ይህን ማድረግ አይቻላችሁም።

37 ባለፈው ምሽት ሰብላችሁን ስለማጠጣት፡ ስለ አርቴዢያን ምንጭ እንደተናገርኩት ነው። ወይም ድብን ባለ ጨለማ ላይ፡ ማሳው መካከል ቆማችሁ፡ እንዲህ ብትሉት፦ "አንተ፡ ታላቁ ኤሌክትሪክ ሆይ፡ እዚህ ሜዳው ላይ እንዳለህ አውቃለሁ። እነሆ፡ መንገድ ጠፍቶብኛልና፡ ወዴት እንደምሄድም አላውቅምና። እንዴት መሄድ እንዳለብኝ አውቅ ዘንድ፡ አሁን አብራ! ሜዳውን ሊያበራ የሚችል በቂ ኤሌክትሪክ አለና።" ትክክል ነው። የሰ፡ ሰር! ባታበሯቸውም እንኳ፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ይህን ማብራት የሚችል በቂ ኤሌክትሪክ አለ። ይሁን እንጂ መግራት ይጠበቅባችኋል። እንግዲህ፡ አቅማችሁን ሁሉ አሟጣችሁ ልትጮኹበት ትችላላችሁ፡ ፈጽሞ አይበራም። በኤሌክትሪክ ሕጎች መሰረት ከገራችሁት ግን፡ ብርሃንን ታገኛላችሁ።

38 እንግዲያውስ፡ በእግዚአብሄር ዘንድም እንዲሁ ነው። እግዚአብሔር የሰማይና የምድር ታላቅ ፈጣሪ ነው፡ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም

ያው ነው። አሁንም አምላክ ነው። የሚሠራው ግን ሕጎቹን እና መመሪያዎችን ስትከተሉ ብቻ ነው። ወዳጆች ሆይ፡ ይህን እላለሁ፡ መሬት ላይ ሲወድቅ አንዴም አላየሁም፡ ወደፊትም አይወድቅም።

39 አሁን፡ እናስተውል። ኢየሱስ በሉቃስ 24፡49 ሐዋርያትን ከዳኑ እና እንደ ቃሉ ከተቀደሱ በኋላ ተልእኮ ሰጥቶአቸው ነበር፥ ጌታ ኢየሱስን በማመን ጸድቋልና፥ በዮሐንስ 17፡17 ላይ ኢየሱስ "አባት ሆይ፡ በእውነት ቀድሷቸው፡ ቃልህ እውነት ነው፡" ባለ ጊዜ ተቀድሰዋል። ቃሉም እርሱ ነበር።

40 እና፡ በሽተኞችን የሚፈውሱበት፡ አጋንንትን የሚገስጹበት፡ ሙታንን የሚያስነሱበት ስልጣን ሰጣቸው፡ እና በደስታ ተመለሱ። ስማቸውም በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ ተጽፎ ነበር። እንዴት እንዳለፍነው አሁን ትዝ ይላችኋል። ይሁን እንጂ አልተለወጡም ነበር። ኢየሱስ በተሰቀለ ሌሊት፡ ጴጥሮስን ተናገረው፡ "ከተለወጥህ በኋላ፡ ወንድሞችህን አጽና።"

41 መንፈስ ቅዱስ... በዘለአለም ህይወት ታምናላችሁ፡ መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ ግን የዘላለም ሕይወት እርሱ ነው። በምን እያመናችሁ ነው... ከመንፈስ የምትወለዱት በመቀደስ ሂደት ነው፡ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ እስኪገባ ድረስ ግን ፈጽማችሁ ከመንፈስ አልተወለዳችሁም። ይህ እውነት ነው። አንድ ሕፃን በእናቱ ማህፀን ውስጥ ሳለ ህይወት አለው፡ ትንንሽ ጡንቻዎቹ ይንቀሳቀሳሉ፥ እሱም ሕይወት ነው። ነገር ግን የህይወት እስትንፋስ በአፍንጫው ውስጥ ሲተነፍስ ግን የተለየ ህይወት ነው። የተለየ ነው። ይህም፡ ይኸው ነው...

42 የተወደዳችሁ የሜቶዲስት፡ የፕሪግሊም ሆሊነስ፡ እና የናዝሪን ወንድሞቼ ሆይ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከመቀደስ የተለየ ነው። መቀደስ መንጻት ነው፡ እርሱም የሕይወት ዝግጅት ነው። መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ ግን፡ እሱ ራሱ ሕይወት ነው። ማዘጋጀት ማለት ዕቃውን ማጠብ ማለት ነው፥ ዕቃው ውስጥ የሚሞላ መንፈስ ቅዱስ ነውና። **መቀደስ** ማለት "ጸድቶ ለአገልግሎት ዝግጁ መሆን" ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ወደ ስራ ይገባል። እግዚአብሔር የሚያጸዳው ዕቃ እናንተ ናችሁ።

43 መንፈስ ቅዱስ ማለትም እግዚአብሔር ራሱ በእናንተ ውስጥ ማለት መሆኑን አውቀናል። ከሙሴ ጋር በእሳት ዓምድ የነበረው እግዚአብሔር ደግሞ ከእናንተ በላይ ነበር። እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ከእናንተ ጋር ደግሞ ነበር። አሁን እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አምሳል በእናንተ ውስጥ ይገኛል። በሦስት መገለጫዎች የሰራ አንድ አምላክ እንጂ፡ ሦስት አማልክት አይደለም።

44 ከሰው በላይ የሆነው እግዚአብሔር፡ ከላይ ወደታች ወረደ። በኤደን ገነት ኃጢአት ስለ ሰራ እና እራሱን ከሕብረት ስለለየ፡ እሱ ላይ መድረስ አልተቻለውም። ከዚያስ ምን ተፈጠረ? ከእሱ በላይ መሆን ነበረበት። የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ዳግመኛ ከሱ ጋር ሕብረት እንዲኖረው አላስቻሉትም፥ ይሁን እንጂ ይህ የአሁኑ ዘመን እንዲመጣ፡ በጥላ መልኩ፡ በሬዎች፡ በጎች እና ሌሎች መስዋዕት በማቅረብ፡ በሕጎችን እና በትእዛዛት ስር ቆየ... ከዚያም እግዚአብሔር ከድንግል ሴት ተወልዶ፡ ወርዶ በተቀደሰ ሥጋ ባደረ ጊዜ፡ እግዚአብሄር ራሱ... እግዚአብሔር ያደረገውን ታውቃላችሁ? ሌላ ምንም አ—አላደረገም... ድንኳኑ ግን በእኛ መካከል ዘረጋው። እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በሚባል ድንኳን አደረ። ድንኳኑ ከእኛ ጋር ተከለ፡ እንዲህ

ሆነ... (ጠ—ጠዋት በዚህ ጉዳይ ላይ ስለምሰብክ፡ ብተወው ይሻላል።) አሁን፡ ይህ—የእግዚአብሔር ድንኳን-ከእኛ ጋር እንዴት አደረ...

45 አሁን ደግሞ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ይገኛል። ኢየሱስ በዮሐንስ ምዕራፍ 14 ላይ "እኔ በአብ እንዳለሁ፡ አብም በእኔ እንዳለ፡ እኔም በእናንተ እንዳለሁ፡ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ በዚያን ቀን ታውቃላችሁ፡" አለ። እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ። ዓላማው ምን ነበር? እቅዱን ለመፈጸም።

46 እግዚአብሔር እቅድ ነበረው። በሰዎች መካከል ሊሰራ ፈለገ፡ በእሳትም ዓምድ ውስጥ አመጣው፡ ይህም በእስራኤል ልጆች ላይ የተንጠለጠለው ምሥጢራዊ እሳት ነበረ። ከዚያም ያ እሳት በኢየሱስ አካል ውስጥ ተገለጠ። እርሱም ያ እሳት እኔ ነኝ "አብርሃም ከመወለዱ በፊት፡ እኔ አለሁ፡" አለ። እሱ ያ እሳት ነበር። እንዲህም አለ፡ "ከእግዚአብሔር ዘንድ መጥቻለሁ፡ ወደ እግዚአብሔርም እመለሳለሁ።" እና ከሞተ፡ ከተቀበረና፡ ከተነሳ በኋላም፡ ቅዱስ ጳውሎስ—ገና ሰሙ ሳውል ይባል በነበረ ጊዜ—በደማስቆ መንገድ ላይ ተገናኘው፡ እና ያን ጊዜ ወደ ቀድሞ ወደ እሳት አምድ ተመልሶ ነበረ። አይኑን የሚያጠፋ ብርሃን ሆነ። ትክክል።

47 እነሆ እርሱ ዛሬም፡ ያው የእሳት ዓምድ፡ ተመሳሳይ ሥራዎችን ተመሳሳይ ምልክቶችን እያደረገ ያለው፡ ያው እግዚአብሔር ይህ ነው። እንዴት? በህዝቡ መካከል እየሰራ ነው። እሱ በእኛ ውስጥ ነው። እኔ... አሁን ከእናንተ ጋር አለ፡ "እኔ ግን በእናንተ ውስጥ እሆናለሁ። እስከ መጨረሻው ድረስ እስከ ፍጻሜው ድረስ፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡ በውስጣችሁም እኖራለሁ፡" እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ። ከእኛ ጋር ይሆናል።

48 አሁን፡ አስተውሉ፡ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ወጥተው እንዲጠብቁት አዟቸው ነበር። tarry የሚለው ቃል "መጠበቅ፡" መጸለይ ማለት አይደለም፡ "መጠበቅ" ማለት ነው። ሰባኪ ለመሆን ገና ብቁ አልነበሩም፡ ምክንያቱም ትንሳኤውን የሚያውቁት፡ ውጭ ወጥቶ በሰውነቱ ሲያዩት ብቻ ነው። እሱ—እርሱም ከእንግዲህ እንዳይሰብኩ አዘዛቸው፡ አስቀድመው ኃይል ከላይ ሳይቀበሉ አንዳች እንዳያደርጉ አዘዛቸው።

ሰባኪ ሁሉ ከእግዚአብሔር የተላከ ነው ወይም በትክክል የተሾመ ነው ብዬ አላምንም... ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍጻሜ የሌለው ስለሆነ። እግዚአብሔር አንድ ጊዜ የሚያደርገውም፡ ሁሉ ጊዜ ያደርገዋል። አሁን፡ ወደ ጴንጤቆስጤ ደርሰው የጴንጤቆስጤ ልምምድ እስኪያገኛቸው ድረስ እንዳይሰብኩ ከከለከላቸው፡ እንግዲያውስ ሰው በራሱ ጥልቅ ፍላጎት ወይም በገዛ ድርጅታቸው ትእዛዝ፡ ካልሆነ በቀር፡ በመንፈስ ቅዱስ እስኪሞላ ድረስ ወደ ፑልቢት የመውጣት መብት የለውም። ይህ በትክክል ትክክለኛ ነው። ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ እስኪሞላ ድረስ በአንዳንድ ድርጅትና ምሁራዊ ፅንሰ ሀሳብ ይመራቸዋልና፥ ከዚያም፡ ባለፈው ምሽት **በጉ እና እርግብ፡** በሚል ርዕስ እንደተናገርነው፥ የርግብን መብል ይሰጣቸዋል።

49 አሁን አስተውሉ። እንዲህም አላቸው፡ "ወደ ኢየሩሳሌም ውጡና በዚያ ጠብቁ፥ የአብ የተሰፋ ቃል እስከምልክላችሁ ድረስ በዚያ ቆዩ።" ከዚያስ፡ ምን አደረጉ? ከእነርሱም አንድ መቶ ሀያ፡ ወንድና ሴት ነበሩ። በቤተ መቅደሱ ወደሚገኘ ሰገነት ወደ አንድ ክፍል ውስጥ ገቡ።

እንግዲህ፡ ከመቅደስ መንጻት ቀጥሎ፡ የጴንጤቆስጤ በዓል ቀን እየተቃረበ ነበረ፡ ይህም የፋሲካ በግ ከሚታረድበት—እስከ ጴንጤቆስጤ ቀን ድረስ ነው፡ የመኸሩ የመጀመሪያው ፍሬ፡ ኢዮቤልዩ፡ የጴንጤቆስጤ ኢዮቤልዩ ማለት ነው። እና በሰገነቶቹ ላይ...

50 አሁን፡ ብዙ አገሮችን አይቻለሁ። ምስራቃዊ የሆኑ ሀገራት በዉስጣቸዉ የውስጥ ደረጃ እምብዛም የላቸውም። ደረጃው ከውጭ ነው። ከቤተ መቅደሱ በስተውጭ፡ ወደ አንድ ትንሽ ክፍል የሚወጣ ደረጃ ላይ እንደነበረው፡ ተነግሮናል፥ መጋዘን ወደሚመስል አንድ ትንሽ ክፍል እስክትደርሱ ድረስ፡ ወደ ቤተ መቅደሱ እናት ላይ፡ ወደ ላይ፡ ወደ ላይ፡ እና ወደ ላይ ትወጣላችሁ፡ በላይኛው ደርብ ላይ፡ እነስ ያለ ሰገነት አይነት ነው። አይሁድንም ሰለ ፈሩ በዚያ እንደነበሩ ደጆቹም ተዘግተው እንደነበር፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡ ምክንያቱ ኢየሱስን የገደሉትን ሊቀ ካህኑ ቀያፋ፡ እና ጴንጤናዊው ጲላጦስ፡ ኢየሱስን በማምለካቸው ምክንያት፡ ሊያጠፏቸው ስለሚችሉ ነው። ክርስቲያን-የተባሉትን በሙሉ ለማጥፋት ይፈልጉ ነበርና። በሮቹ ተዘግተው፡ ሲጠባበቁ ነበር።

51 አሁን፡ እነዚያን አይኖት ቤቶች ውስጥ፡ መስኮት የላቸውም። መስኮታቸው ከበሩ ጋር አንድ ላይ የተሰሩ፡ ሰባችሁ የምትከፍቱት አይነት ነው። በክፍሉ ውስጥም ተንጠልጥለው የሚያበሩ የዘይት መብራቶች ነበሩ... ካሊፎርኒያ ውስጥ በክሊፍተን ካፌቴሪያ ውስጥ ከሄዳችሁ፡ ምድር ቤት ላይ ውረዱና፡ በሰገነቱ ላይ እንደነበረ፡ አንድ አይነት ነገር ታያላችሁ። ገብታችሁ ታውቃላችሁ? እስኪ ስንቶች ገብታችሁ ታውቃላችሁ? ራሶቻችሁን የምትነቀንቁ ሰዎች ይታዩኛል። እንግዲያውስ፡ ስለምን እንደማወራ ታውቃላችሁ። በጣም ጥሩ። ወደዚያ ስትሄዱ፡ የጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታን ታያላችሁ፥ ከመሄዳችሁ በፊት፡ ከወደ ምስራቅ የሚገኙትን ቤቶች አይነት ወደ አንዱ ትገባላችሁ። ይህ በትክክል እውነት ነው። በዚያም በወይራ ዘይት የተሞላች፡ የሚበራ አንስተኛ ክር ያላት ኩራዝ ታገኛላችሁ።

52 አሁን፡ ከውጭ በኩል ባለው መወጣጫ ወጥተው፡ በዚያ ነበሩ እንበል። አይሁድን ሰለ ፈሩ፡ ወደዚያ ወጥተው ተሸሸጉ። ኢየሱስ "በኢየሩሳሌም ቆዩ፡" ብቻ አላቸው። እንጂ ወደ ላይኛው ክፍል እንዲሄዱ አልነገራቸውም። ምን እንደሚፈጠር መገመት በማይቻልበት ሁኔታ ውስጥ ሆነው፡ በዚያ ቤት ውስጥ ነበሩ። ገብተው ሊይዟቸው ይችላሉና። እናም በላይኛው ፎቅ ላይ ወዳለው፡ ትንሽ ምስኪን ክፍል ሄዱ፡ በዚያም፡ አይሁድ ወደ እነርሱ እንዳይገቡባቸው ክፍሉን ቀረቀሩት። በዚያም አሥር ቀን እየጠበቁ ቆዩ።

53 አሁን፡ አሁን፡ በሐዋርያት ሥራ 1 ላይ ነን። አሁን፡ በደንብ ተከታተሉኝ። ምስሉ ገብቷችኋል? ከህንጻው በስተውጭ በኩል ወደ ላይ በሚወጣ ደረጃ በኩል፡ ወደዚህች ትንሿ ክፍል ውስጥ ገቡ። በቤተ መቅደሱ ውስጥ የጴንጤቆስጤ በዓል እየተደረገ ነበር። ኦህ፡ ታላቅ ጊዜ እያሳለፉ ነበር። አሁን፡ በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፡ ሁሉም በአንድ አሳብ ነበሩ፡ እግዚአብሔር የተሰፋ ቃሉን እንደሚልክ የሚያምን፡ አንድ አሳብ ነበራቸው። እዚህ ያለ እያንዳንዱ ሰው ዛሬ ማታ በዚያ አይነት አንድ አይነት አሳብ ውስጥ ይግባ እና የሚሆነውን ይመልከት። ይደገማል። ለእነርሱ እንደተባለው ለእኛም ተመሳሳይ ተስፋ ቃል ነው። አያችሁ?

54 ምን ያደርጉ ነበር? መመሪያዎችን፡ የእ—እ—እግዚአብሔር ሕጎችን በመከትል ላይ ነበሩ፥ “እስከዚህ ጊዜ ድረስ ጠብቁ... ”

55 አሁን፡ አይሁዶችን ፈርተው ነበር። አሁን፡ ያንን አትርሱ። አይሁዶችን ፈርተው ነበር። አሁን፡ በድንገት እንደ አውሎ ንፋስ ያለ ድምፅ መጣ። አውሎ ንፋስ አይደለም፡ እንደ አውሎ ንፋስ እንጂ። በተርጓሚው ላይ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ አስተያየቶቹን አነባለሁ። እንደ አውሎ ንፋስ ነበረ። በሌላ አባባል፡ መለኮታዊ ንፋስ ነበረ (ኦህ!)፡ ሊሰማቸው የሚችል ነበረ። ንፋሱ በውስጣቸው ነበር። እነሆ አ—አውሎ ንፋስ መጣ፡ እንደ አውሎ ንፋስ መጣ። ንፋሱ እንደ አውሎ ንፋስ የሚመስል፡ እንደሚሄድ ነገር እንጂ፡ የሚነጥቅ ንፋስ አልነበረም፥ ዊፍፍ! ተሰምቷችሁ ያውቃል? ኦህ፡ ማይ! እንደሚነጥቅ ንፋስ። አሁን ተመልከቱ። እና ሞላው... አሁን፡ እዚህ ጋር “ሁሉ” ይላል፡ በግሪክ ግን እንዲህ ይላል “በሙሉ (በትልቁ ፊደል W-h-o-l-e)፡ ቤቱን በሙሉ፡” ያሉበት ቦታ በሙሉ። እያንዳንዱ ስንጥቅ፡ ማእዘን፡ እና ንቃቃት ሁሉ ሙልት ያለ ይመስላል። እንዲህ ባይ አልነበረም፡ “ወንድሞች ሆይ፡ እኔን የሚሰማኝ አይነት ይሰማችኋልን፡ አላሉም? ” በጭራሽ! እንደሚነጥቅ ንፋስ፡ በሁሉም ስፍራ ነበረ። አሁን ተከታተሉኝ። “እንደሚነጥቅ ኃይለኛ ነፋስ ድምፅ መጣ እና (መስተጻምር። **እናዎቹን** አሁን አስተውሉባቸው። ካላስተዋላችኋቸው፡ ያላለውን እንዳለ ልታስመስሉት ትችላላችሁ። አያችሁ? )—ልክ እንደ (መጀመሪያ እንደተከናወነው ድምጽ ነው፡ እንደሚነጥቅ ንፋስ መሳይ—በላያቸው መጣ)—እና (ትናንት ማታ፡ ትዝ ይላችኋል ወደ ግሮሰሪው ሄጄ አንድ ዳቦና ሥጋ ገዛሁ። አብሮ የሚሄድ ነገር ነው። ዳቦው አንድ ነገር ነው፡ ስጋውም ሌላ ነገር ነው። እና አንደኛው የነካቸው ነገር ድምጹ ነበር)—እና እነሆ (በፊታቸው) የታያቸው ነገር፡ ልሳን—የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው።”

56 እዚህ ውስጥ የሴሲል ደሚልን **አስሩ ትእዛዛት** አይቶ የሚያውቅ ሰው አለ? ትእዛዛቱ እየተጻፉ ሳለ አስተውላችኋል? እንዴት እንዳወቀው፡ እኔ አላውቅም። አይቼ በጣም የወደድኳቸው ሁለት ወይም ሶስት ነገሮች ነበሩ። የመጀመሪያው ነገር ያን የኢመራልድ ብርሃን ነው፡ በትክክል እንደዚያ ይመስለዋል። አያችሁ? ሌላኛው ደግሞ ትእዛዛቱ እየተጻፉ ሳሉ ነው፡ ካለቀ በኋላ፡ ከዚያ ታላቅ የእሳት አምድ በርሮ ሲሄድ አስተውላችኋል፡ በርረው የሚሄዱትን የእሳት ፍንጣቂዎቹን? እነዚያን አስተውላችኋል? አሁን፡ በበዓለ ሃምሳ የነበረው እሱ ይመስለኛል። የታያቸው ነገር... ማየት የቻሉት ነገር ነው። “ወደ ውስጣቸው ወረደ፡” አላለም። ነገር ግን በዚያም ነበልባል ታያቸው (ምን እንበለው)፡ ምላሶች፡ ልክ እዚህ እንዳለ ምላስ **እንደዚህ** አይነት ምላስ፡ የምላስ ቅርጽ ያለው፡ የእሳት ነበርባል ነበረ። አሁን፡ ጆሮ—እንዳልኩት፡ ጆሮ ጆሮ ነው፥ ጣትም ጣት ነው። ጣት ተሰማኝ አይባልም፥ ጣት ይመስላል ይባላል እንጂ። ስለዚህ ጆሮ ከሆነ፡ ሰምተውታል ማለት አይደለም፥ ጆሮ ይመስላል እንጂ። ይህ ምላስ የሚመስል እሳት እንጂ፡ የሚናገር ሰው አልነበረም፡ ምላስ የሚመስል እሳት ነው።

57 አሁን፡ አዳምጡ። ግሪኩ እንዴት እንደሚነበብ እንመልከተው፥

> **በድንገትም** እንደ**ሚነጥቅ አውሎ ንፋስ**... **ታላቅ ድምጽ መጣ**... (3ኛ—3ኛው ቁጥር።)

> የተከፋፈሉ ልሳኖችም **ታዩአቸው**፡... (የተከፋፈሉ ልሳኖች በውስጣቸው ነበሩ፡ ወይም በተከፋፈሉ ልሳኖች ተናገሩ አይደለም፥ የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው ነው። አሁን፡ ተመልከቱ። ገና በላያቸው ላይ አልወረደም። በክፍሉ ውስጥ፡ እንደ ንፋስ እየተሽከረከረ ነው።)... ለ**ነሱ... እንደ... እሳት**... የተከፋፈሉ **ልሳኖች... ታዩአቸው**... (ይህም በፊታቸው ነው) **እንደ... እሳት**፡ (እንደ እሳት ያሉ ልሳናት) **እና** በአንድ (በነጠላ) በ**እያንዳንዳቸውም** ላይ አረፉባቸው። (ወደ ውስጣቸው ገባ አይልም፥ አረፈባቸው።)

58 አሁን፡ ኪንግ ጄምስ ያንን እንዴት እንደሚቆርጠው ተመልከቱ፥ "የተከፋፈሉ ልሳኖች በላያቸው ላይ መጡባቸው፡ ወይም አረፉባቸው (በዚያ በኪንግ ጄምስ ላይ እንዴት ይነበባል? ) በላያቸው ላይ ተቀመጡባቸው።" አያችሁ? አሁን፡ ወደዚያ ወጥቶ ቁጭ ሊልባቸው አይችልም። ይሄን እናውቀዋለን። ኦሪጂናሉ ግን እንዲህ ይላል፡ "አረፈባቸው፡" ይመስለኛል፥ አይደለም'ዴ? በትክክለኛ መልኩ ላምጣው። አዎን! "... በእያንዳንዳቸው ላይ አረፈባቸው።" በእያንዳንዳቸው ላይ አንድ የእሳት ልሳን አረፈባቸው። አያችሁት? ገባችሁ? በሁለተኛው ደረጃ የሆነው ይህ ነው። በመጀመሪያ ነፋስ ነበር፡ ከዚያም የእሳት ልሳኖች መታየት።

59 እነዚህ ትናንሽ የቅባት ኩራዞች እየነደዱ የሚበሩበት ክፍል ይህ ነበረ። ከላይ ቁጭ ብለው እስኪ አስቧቸው። አንዱ "ኦህ!፥ አለ፡ ሕንፃውን በሙሉ ተመለከተ፡ በህንፃው ላይ በሙላት ነበር። በህንፃው ዙሪያ ላይ የእሳት ልሳኖች መምጣት ጀመሩ፡ እና ሁሉም "ተመልከቱ!" ተባባሉ። አሁን ተከታተሉኝ። እነዚህም የእሳት ልሳኖች ያን ጊዜ ታዩ።

አሁን ቀጣዩን ተከታተሉኝ፥

> **እና** (ሌላ መስተጻምር፥ ሌላ ነገር ሁነ።) **ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ**፡... (ሁለተኛው ነገር ተከሰተ።)

60 አሁን እዩ፡ ያንን እንዲህ በማለት መለወጥ ያምረናል፡ "የእሳት ልሳኖች ነበሯቸው፡ በዚህም እየተንተባተቡ እየተመላለሱ፥ ወደ ውጭ ወጥተው በማይታወቅ ልሳን መናገር ጀመሩ።" ወዳጆች ሆይ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ ብሎ ነገር የለም። መንፈስ ቅዱስን በመቀበል በማይታወቅ ቋንቋ የሚናገር ሰው ሁሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ በተቃራኒው መንገድ ያደርገዋልና። እና ከአፍታ በኋላ እኔ በማይታወቅ ልሳን በመናገር እንደማምን አሳያችኋለሁ እንዲሁም አረጋግጥላችኋለሁ፡ ይህ ግን መንፈስ ቅዱስ መቀበል አይደለም። ያ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው። መንፈስ ቅዱስ መንፈስ ነውና።

61 አሁን ተመልከቱ። እነዚያ ልሳኖች በክፍሉ ውስጥ እንደ እሳት ነበሩ፡ በእያንዳንዳቸውም ተቀመጡባቸው። ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ (ሁለተኛው ነገር)፡ ከዚያም፡ በመንፈስ ቅዱስ ከተሞሉ በኋላ፡ በልሳኖች ሳይሆን ተናገሩ፡ በልሳኖች ሳይሆን፡ በቋንቋዎች ተናገሩ። ያን አስተውላችሁታል? ይናገሩ ዘንድ መንፈስ እንደሰጣቸው በሌሎች ቋንቋዎች መናገር ጀመሩ። አሁን፡ ወደ ውጭ የተሰማው ይህ ነው።

62 አሁን ተመልከቱ። አሁን፡ እንዳትረሱት ዘንድ ምሳሌውን እንደገና እንድገመው። በመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት መሰረት፡ በላይኛው ክፍል ውስጥ

እየጠበቁ ሳሉ፡ በድንገት እንደሚነጥቅ ነፋስ ድምፅ መጣ፡ ያ በላያቸው ነው፥ መንፈስ ቅዱስ ነበር። ያ የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ እንደሆነ ሰንቶች ታምናላችሁ? ልክ እንደ ንፋስ፡ እንደ መለኮታዊ ንፋስ። ከዚያ በኋላ ይህን አስተዋሉ። በዚያም አንድ መቶ ሀያ፡ ትናንሽ የእሳት ልሳኖች መጡ፡ እና በእያንዳንዳቸው ላይ መውረድ እና መቀመጥ ጀምሩ። ምን ነበር? ምን ነበር? የእሳቱ ዓምድ፡ እሱም እግዚአብሔር ራሱ በሕዝቡ መካከል ራሱን እየቆራረሰ፡ ወደ ሕዝቡ መጣ። ኢየሱስ ሙላት ነበረው፥ የማይሰፈር መንፈስ በእርሱ ዘንድ ነበረ፥ እኛ ግን በልክ ተሰጠን (ምን ማለቴ እንደሆነ ገባችሁ? )፡ ምክንያቱም የማደጎ ልጆች ነን። ሕይወቱ—የዘላለም ህይወቱ መጥቶ እየገባ ነበርና። ከዚያስ፡ ምን ተፈጠረ? ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ።

63 አሁን፡ አንድ ነገር ልጠይቃችሁ። ወሬው የተሰማው መቼ ነበረ? ከላይኛው ከሰገነቱ ወጥተው ደረጃዎቹን ወርደው ወደ ቤተመንግሰት አደባባይ—ወይም ወደ ውጭ መውጣት—ወደ ቤተመቅደስ አደባባይ መውጣት የነበራቸው ከሆነ፡ ከነበሩበት ከሰገነት ወርደው፡ ህዝብ ሁሉ በአንድነት ወደተሰበሰቡበት አደባባይ ለመሄድ፡ ከነበሩበት እስከዚያ ድረስ ምናልባት የአንድ መንደር ርቀት ሊኖረው ይችላል... በመንፈስም እንደ-ሰከረ ሆነው ከዚያ ወጡ። ሕዝቡም “እነዚህ ሰዎች አዲስ የወይን ጠጅ ጠግበዋል፡” ብለዋቸው ነበርና። እንደዚህ ያለ ነገር አይተው አያውቁም።

64 እያንዳንዱ ሰው እንዲህ ለማለት እየሞከሩ ነበርና፡ “መንፈስ ቅዱስ መጥቷል። የእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል በእኔ ላይ ነው። በ—በመንፈስ ተሞልቻለሁ።” እርሱም የገሊላ ሰው ሆኖ ሳለ፡ ያናግረው የነበረው ሰው፡ አረብ ወይም የፋርስ ሰው፡ በገዛ ቋንቋው ሰማው።

65 “ይህ እንዴት እንሰማለን (የማይታወቅ ቋንቋ አልነበረምና)—እያንዳንዳችን በተወለድንበት ልሳን እንዴት እንሰማቸዋለን? እነዚህ የሚናገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? ” ምናልባትም የተናገሩት የገሊላ ቋንቋ ይሆናል... ሲሰሙት ግን፡ በተወለዱበት ቋንቋ ነው። ይህ ካልሆነ ግን፡ ይህን እድትጠይቁኝ እፈልጋለሁ—ይህን ጥያቄ መልሱልኝ፥ ጴጥሮስ ወደዚያ ተነሥቶ በገሊላ ቋንቋ ሲናገር፡ ሕዝቡ ሁሉ የሚናገረውን እንዴት ሰሙ? በዚያም ሦስት ሺህ ነፍሳት ወደ ክርስቶስ መጡ ጴጥሮስም በማይታወቅ ቋንቋ ተናገረ። በትክክል! እግዚአብሔር ተአምር ሲሠራ ነበር። ጴጥሮስ፡ የሜሶጶጣሚያ ሰዎች፡ ለእንግዶቹ፡ እና ወደ ይሁዲነት ለተለወጡ ሰዎች ለተሰበሰቡት ተሰብሳቢዎች፡ እና ከመላው ዓለም የመጡ ሁሉም እዚያ ቆመው ነበር... ጴጥሮስም ቆሞ በአንድ ቋንቋ ይሰብክ ነበር፡ ሁሉም ሰሙት፡ ሦስት ሺህ ንስሐ ገብተው በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም ወዲያውኑ ተጠምቀው ነበርና። እንዴት ሆነ?

66 ወዳጆች ሆይ፡ ተመልከቱ፡ የራሴ የሆኑት የጴንጤቆስጤ የሐይማኖት ተቋም ወንድሞቼ፡ ይህን ይቀበሉታል ብዬ አልጠብቃቸውም። እናንተ ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ ፈልጋችሁ ድረሱበት እና መንፈስ ቅዱስ ከተቀበሉ በኋላ እና በልሳን በተናገሩ ጊዜ የሚሉትን ነገር አያውቁትም ነበር ወይ መርምራችሁ በማንኛውም ጊዜ ይሄን ንገሩኝ። በዚያን ጊዜ የተቀበሉት በዚያ መልኩ ከሆነ፡ ሉዓላዊው አምላክ... በእያንዳንዱ ዘመን በተመሳሳይ መንገድ ማድረግ አለበት።

67 አሁን፡ እ... አሁን፡ በቆርኔልየስ ቤት ውስጥ-... ትናንት ማታ፡ ወደ ሰማሪያ በወረድን ጊዜ፡ በሌላ ልሳን ስለመናገራቸው የተመዘገበ አንዳች መዝገብ እንዳልነበረ ሁላችንም እንስታውሳለን፡ ምንም የተባለ የለም። ወደ ቆርኔልየስ ቤት በወረዱ ጊዜ ግን፡ በዚያም የሦስት የተለያዩ አገራት ዜጎች ነበሩ፡ በልሳንም ተናግረው ነበር። በተናገሩ ጊዜም፡ ጴጥሮስ እንዳለው፡ በመጀመሪያ እንደነበረው አይነት ከሆነ፡ ከተናገሩ፡ ተቀብለዋል። አሕዛብም ከእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋ እንደ ተቀበሉ አወቁ፡ ምክንያቱም ልክ እንደ መጀመሪያው መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋልና። በዚህ ጉዳይ ላይ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ አንድ ጥያቄ አለኝ። ምን እንደሆነ ማየት እንድትችሉ፡ መሰረት መጣል እፈልጋለሁ።

68 ከሁን፡ ከዚህ በተለየ መልኩ ከተማሩ ሰዎች ምንም አልጠብቅም... የተወደዳችሁ፡ ውድ፡ የጴንጤቆስጤ ወንድሞቼ ሆይ፡ ስሙኝ። ይህንን ውጭ አላስተምረውም። ይህ... ውዝግብ ለመፍጠር ምንም ነገር አላደርግም። ግን እውነቱን ካላገኘን፡ መቼ እንጀምራለን? እኛን ለማቅናት እዚህ ሊሆን የሚገባው ነገር ሊኖረን ይገባል። እዚሁ እያለን የመነጠቅ ጸጋ አሁኑኑ መቀበል አለብን። እውነት መውጣት አለባት።

69 አንድ ሰው ደንቆሮ፡ ዲዳ፡ እና ምንም መናገር ባይችልስ ምን ያደርጋል? መንፈስ ቅዱስን መቀበል ይችል ይሆን? በመሰረቱ ምስኪኑ ሰው መዳን እየፈለገ፡ እንደበት የሌለው ቢሆንስ? እያችሁ? መንፈስ ቅዱስ ራሱ፡ ጥምቀት ነው። ከዚያ ቀጥሎ፡ በልሳን መናገር የመሳሰሉ ስጦታዎች፡ ልሳንን መተርጎም፡ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ወደ አካሉ ከገባችሁ በኋላ ነው። እነዚያ ስጦታዎች በክርስቶስ አካል ውስጥ ናቸውና።

70 አሁን፡ ይህን የምልበት ምክንያት... አሁን፡ ተከታተሉኝ። በዓለም ላይ ከሐዋርያት በኋላ የመጀመሪያዋ የተደራጀች ቤተ ክርስቲያን ከሆነችው፡ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ይህን ትጠብቃላችሁን... የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፡ ኦህ፡ የመጨረሻው ሐዋርያ ከሞተ ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ የተደራጀች ናት፡ ከሐዋርያት በኋላ፡ ልክ ከኒቂያ ጉባኤ በኋላ፡ ከስድስት መቶ ዓመታት—በኋላ፡ የኒቂያ አባቶች ተሰብስበው በተደራጁ ጊዜ፡ ያን ጊዜ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን፡ ዓለም አቀፋዊት ቤተ ክርስቲያን አድረጓት። በዚያም የዓለም ቤተ ክርስቲያን አቋቋሙ። **ካቶሊክ** የሚለው ቃል ትርጉሙ "ዓለም አቀፋዊ"፥ በሁሉም ቦታ የሚገኝ ማለት ነው። እነዚያ... ሮማውያን—አረማዊት ሮማ ጳጳሳዊት ሮማ ወደ መሆን ተለወጠች። የጴጥሮስ ቦታ የሚተካ ሊቀ ጳጳሳትን አቆሙ፡ ኢየሱስ የመንግሥቱን ቁልፎች ለእርሱ እንደ ሰጠ ያስባሉና። ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሱ ማለት የማይሳሳት አካል ነበረ፡ እስከ ዛሬ ድረስም እንደዚያው ነው። ይህ ማለት... የሱ ቃል ሕግና ሥርዓት ነው። የማይሳሳት ጳጳስ ነው። የሚለውን ተሰራጨ።

71 ከዚያም፡ በዚህ በካቶሊክ ትምህርት የማይስማሙ ሁሉ፡ ይገደላሉ፡ ግንድ ላይ ይቃጠላሉ፡ ሌላ ሌላው ሁሉ ይሆናሉ። ይህ ሁሉ ማወቅ የቻልነው በጆሲፈስ የተቀደሱ ጽሑፎች፡ እና በ **ፎክሰስ ቡክ ኦፍ ማርትይርስ**፡ እንዲሁም በሌሎች... በሂስሎፕ **ቱ ባቢሎንስ** የመሳሰሉ የተቀደሱ ጽሑፎች፡ እና በ—በታላላቅ ታሪኮች ነው። ከዚያ በኋላ፡ ከ—ከአንድ ሺ አምስት መቶ ዓመታት በኋላ፡ እንደምናውቀው፡ ጨለማው ዘመን፡ መጽሐፍ ቅዱስ

ከሰዎች እንዲጠፉ ተደረገ። እንደምናውቀውም፡ በማይረቡ መነኩሴዎች፡ እና በሌሎች—እንዲደበቅ ተደረገ።

72 ከዚያ በኋላ የመጀመሪያው ተሐድሶ ጀመረ፡ እሱም በማርቲን ሉተር ነበር። እርሱም ተነሳና ካቶሊክ ስለ ቁርባን ይህ የክርስቶስ አካል ነው—የራሱ የክርስቶስ ስጋ ነው የምትለውን ነገር፡ የክርስቶስ አካል ምሳሌ ብቻ ነው አላቸው። ቁርባኑንም በመሠዊያው ፊት ባለው መውጫ፡ ወይም በደረጃው ላይ ጣለው፡ እና የክርስቶስን እውነተኛ ስጋ ብዬ አልጠራውም አላቸው፡ እና፡ “ጻድቅ በእምነት ይኖራል” ብሎ ሰበካቸው። አሁን፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከእሱ ጋር ትስማማለች ብላችሁ አትጠብቁ፡ በፍጹም አትስማማም፡ ስሕተት አልባው መሪያቸው ይከለክላቸዋልና። እሺ።

73 ማርቲን ሉተር ስለ መጽደቅ ከሰበከ በኋላ፡ ጆን ዌስሊ፡ መቀደስን እየሰበከ መጣ። እርሱም ሰው ከጸደቀ በኋላ፡ (መልካም ሆኖ ሳለ) መቀደስ መጽዳት አለበት፡ የክፋት ሁሉ ስር በኢየሱስ ደም መወገድ አለበት፡ በማለት እየሰበከ መጣ። አሁንም፡ ሉተራኖች ስለማያደርጉት፡ ስለ መቀደስ ይሰብካሉ ብላችሁ አትጠብቁ።

74 ዌስሊ መቀደስን ከሰበከ በኋላ፡ ከሱ ዘንድ የወጡ፡ ጥቃቅን-ሰብርባሪዎች ተከትለውት መጡ፡ ዌስሊያን ሜቶዲሰት፡ እና ናዝሪኖች፡ እና የመሳሰሉት፡ በዘማናቸው ሁሉ እሳቱን ማቀጣጠል ቀጠሉበት፡ ከዚያ በኋላ ጴንጤቆሰጤ መጣና፡ እንዲህ አሉ፡ “ይኸው፡ በመንፈስ ቅዱስ በመጠመቅ ነው፡ እሱን ስናገኝ በልሳኖች እንናገራለን።” አዎን። ያ በመጣ ጊዜ፡ ናዝሬኖችን እና የዌስሊያን ሜቶዲሰቶች፡ እና ሌሎች ሁሉ፡ ያንን ያምኑታል ብላችሁ አትጠብቁ። አይቀበሉትም። ዲብሎስ ነው ይሉታል። እሺ። ከዚያስ ምን ተፈጠረ? እነሱ መውረድ ጀመሩ፡ ጴንጤቆሰጤ ከፍ ከፍ ማለት ጀመረ። ጴንጤቆሰጤ እስኪራገፍ ድረስ ከፍ ከፍ ብሎ ወጣ። በኋላ ግን ሌላ ነገር አትቀበሉ በማለት፡ ተደራጅቶ ጠፋ። የየራሳቸውን ህግና መመሪያ አረቀቁ፡ ያን ጊዜ አበቃላቸው።

75 አሁን፡ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ የሁሉም እውነት በገለጠ ጊዜ እና ራሱ እና በቃሉ መገኘት ማረጋገጥ ሲጀምር፡ ጴንጤቆሰጤዎች፡ “ይህን እንቀበለዋለን” ይላሉ ብላችሁ አትጠብቁ። እንደ ሉተር፡ እንደ ዌስሊ፡ እና ሌሎቹ እንዳደረጉት በራሳችሁ መቆም አለባችሁ። ዘመኑ ስለደረሰ በራሳችሁ መጽናት አለባችሁ። እና አሰቀያሚ ዳክዬ የሚያስመስለኝም ይህ ነው። የተለየሁ የሚያደርገኝም ይህ ነው።

76 እና እንደ ውድ ወንድሜ ኦራል ሮበርትስ፡ እና ቶሚ ኦስቦርን፡ ቶሚ ሂክስ፡ እና ሌሎቹ መጀመር አልችልም፡ ምክንያቱም አብያተ ክርስቲያናት ከእኔ ጋር አይሰማሙም። ስለ እኔ እንዲህ ይላሉና፡ “እሱ በዘለአለም ደህንነት ያምናል። እሱ ባፐቲሰት ነው። በልሳን መናገርን እንደ መንፈስ ቅዱስ የመጀመሪያ ማስረጃ አድርጎ አያምንም። ከዚያ ሰውዬ ራቁ!” አያችሁ?

77 ነገር ግን ኑና ፊት ለፊት ተጋፈጡ። ተጋፈጡት። ሜቶዲሰቶች—ሉተራኖችን፡ መጋፈጥ ይችላሉ። ጴንጤቆሰጤ ሜቶዲሰቶችን ሊጋፈጡ ይችላሉ። እኔም ጴንጤቆሰጤዎችን መጋፈጥ እችላለሁ። በትክክል ትክክል ነው። እውነት ነው። ለምንድነው? እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን እየተጓዝን ስለሆን ነው። አያችሁ? ወደ ንጉሱ አውራ ጎዳና እየሄድን ነው፡ እና አብዝተን

በተጠጋን ቁጥር፡ ፀጋ በዛልን፡ የበለጠ ኃይል ተሰጠን፡ መለኮታዊ ነገሮች በዝቶልናል። እና እኛ እንዲህ ነን። መንፈስ ቅዱስ በመጀመሪያ እንደ ነበረ በብርሃን አምሳል የወረደበት ዘመን ይህ ነው፡ ያኔ በምድር በነበረ ጊዜ ያደረጋቸውን ተመሳሳይ ነገሮችን እያደረገ፡ በእሳት አምድ አምሳል፡ እራሱን ገለጠ። ኢየሱስም አለ፡ "ትክክል መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን እንዴት ታውቃላችሁ? ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል። ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል።"

78 አሁን፡ እናንተ የጴንጤ ወንድሞቼ። እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ። እኔ ከእናንተ አንዱ ነኝ። መንፈስ ቅዱስንም አግኝቻለሁ። በልሳኖች ተናግሬአለሁ፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ስቀበል ጊዜ አላገኘሁትም። የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ተጠምቄአለሁ፡ በልሳኖች ተናግሬአለሁ፡ ትንቢትም ተናግሬአለሁ፡ የእውቀት ስጦታዎች አሉኝ፡ ጥበብ፡ መተርጎም፡ እና ሁሉ እየተፈጸመ ይገኛል። ነገር ግን እነዚህን ሁሉ ሊሆንልኝ ያስቻለኝ፡ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆንኩ ነው። ኃይሉ፡ የእግዚአብሔር እሳቱ በነፍሴ ውስጥ ነው፥ የመጣው ያንን የእሳት ልሳን—ወደ ውስጤ ዘልቆ የእግዚአብሔር ያልሆነውን ሁሉ አቃጥሏል፡ አሁንም በመንፈሱ እመራለሁ። "**ወደዚህ** ሂድ፡" ሲለኝ፡ እሄዳለሁ። "**ወደዚህ** ሂድ፡" እሄዳለሁ። "**እዚህ** ተናገር፡" እናገራለሁ። "**ይህን፡ ያንን፡** እና **ሌላውን** አድርግ።" እያችሁ… ልክ እንደዚህ፡ በመንፈስ ትመራላችሁ። ፈቃዱን በእናንተ ዘንድ የሚሰራ፡ እግዚአብሔር ነው። ምንም ይሁን ምን፡ ፈቃዱን እየሰራ ነው።

79 አሁን፡ አዳምጡኝ። እዚህ መዝገበ ቃላት ላይ ያሉትን ጥያቄዎች ከመጀመራችን በፊት እዚህ ላይ ላንብብ። አሁን፡ ከቫቲካን ትርጉም፡ 7ኛው ዕትም፡ 190—1205፦

> "ሰዎቹ ይናገሩት የነበረው ድምጽ በሌላ አገር ቋንቋ ይናገሩ ነበር ብሎ ለመወሰን አስቸጋሪ ነው፡ ወይም ህዝቡን ያሰደነቀ መለኮታዊ የሆነው እንደሚነጥቅ ንፋስ የተባለው ነገርም እንዲሁ ነው።"

ሊረዱት አልቻሉም። አሁን ተከታተሉኝ። ሰዎቹ ይሁኑ…

80 በምሳሌ እገልጻለሁ። እዚህ ጋር፡ ድሆች እና ምስኪን የገሊላ ሰዎች አሉ። እዚህ ጋር ደግሞ ጎዳና ላይ የነበሩ አሉ። እንደዚህ ያለ ነገር አይተው አያውቁም፥ እጆቻቸው ወደ ላይ ከፍ አድርገዋል፡ ከላይኛው ክፍል ወጥተው፡ ወደ ታች፡ ወደዚያ ወጡ፡ ብቻ ተሞልተዋል፥ ገና ምን ትንፍሽ አላሉም። እያችሁ? ብቻ ወደዚያ ወጥተዋል። አሁን ደግሞ፡ እንዲህ እንበል፡ ወደዚያም ወጥተው እየተንገዳገዱ ነበር። ሰዎቹም አሉ… ግሪክ ወደ እኔ ሮጦ፡ ገሊላኛ እናገራለሁ፡ አለ።

አንተም ወደሱ ሮጠህ "ምን አገኘህ፡ ወዳጄ፡" ትለዋለህ?

81 "በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቻለሁ። የእግዚአብሔር ኃይል በዚያ ክፍል ውስጥ ወረደ። የሆነ ነገር ሆኛለሁ። ኦህ፡ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!"

ሌላኛው ደግሞ እዚያ ጋር፡ ከአረብ ጋር ይነጋገራል፡ እርሱ ገሊላዊ ሆኖ አረብ—አረብኛ ቋንቋ ይናገራል።

82 አሁን፡ ህዝቡ በአንድነት ሲሰበሰቡ፡ የሰበሰባቸው የሚናጠቀውን ንፋስ ነውን፡ ወይስ በባዕድ ቋንቋ ይናገሩ ስለነበር ነውን? አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስ

በትክክል አይናገርም... ልትመለከቷቸው የሚገባችሁ ሁለት ነገሮች አሉ። ይህም... እ—እንግዶቹ እንዲህ አሉ፡ “ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ ሰዎች ሁላችንም በተወለድንበት አንደበት እንዴት እንሰማለን? ” እየሰሙ እንጂ፡ እየተናገሩ ነበር አላለም።

83 ከዚያም ሰዎቹ እራሳቸው፡ እነዚያ ሰዎች ራሳቸው፡ ይህን ያብራሩታል። ጴጥሮስም ወደ አንድ ነገር ወጥቶ እንዲህ አለ፡ “የገሊላ ሰዎች፡ በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ሆይ፡ ይህ በእናንተ ዘንድ ይታወቅ (ሰዎች ገሊላውያኖቹ ቋንቋ አልነበራቸውም ይላሉ) ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን እና ቃሎቼን አድምጡ (ለሁሉም—በምንኛ ቋንቋ፡ ተናገራቸው? )፥ እነሆ፡ ከቀኑ ሦስተኛ ሰዓት ስለሆነ፡ እነዚህ እንደ መሰላችሁ አልሰከሩም፡ ይህ ግን በነቢዩ ኢዩኤል የተባለው ነው፥ ‘በመጨረሻው ቀንም እንዲህ ይሆናል፡ ይላል እግዚአብሔር፡ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ። ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ።’” ቀጠለ ቀጠለና፡ እንዲህ አለ፡ “እናንተ እጆቻችሁ የረከሱባችሁ ንጹሑን የእግዚአብሔር ልጅን ሰቅላችሁ ገደላችሁት። ዳዊት ስለ እርሱ ተናግሮ... ‘ነፍሱን በሲኦል አይተወውም፡ ቅዱሱንም መበሰበሰን ያይ ዘንድ አይተወውም።’” እንዲህ አለ፡ “ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን።” ይህንንም በሰሙ ጊዜ... አሜን! እነማን ናቸው? ከሰማይ በታች ያለው ሰው ሁሉ። ምን እየተካሄደ ነበር? “አሁን፡ ገሊላኛ እናገራለሁ፥ **ይህን** እናገራለሁ፥ ወይም **ይሄኛው** ልናገር... ? ... ” አላለም፡

84 ጴጥሮስ ገና ይህን ሲናገር፡ “እናንተ ሰዎች እና ወንድሞች ሆይ፡ ለመዳን ምን እናድርግ፡” ብለው ጠየቁ? ጴጥሮስም ቀመሩን ሰጣቸው። ሁሌም ሊሆን የሚገባው እንደዚያ ነው። አያችሁ?

85 ሁሌም እየጨመረ፡ ወደ እግዚአብሔር እየተዘረጋ የሚሄድ ነው፡ ተጠጉት። እንዴት ታውቃለህ? ይኸውላችሁ፡ ሉተር ስለ መጽደቅ በተቀበለ ጊዜ፡ ያንን መንፈስ ቅዱስ ብሎ ጠራው። እንዲሁም ነበር። እግዚአብሔርም ትንሽ ወደ ውስጥ ገባ አደረገው። ከዚያስ ምን አለ? ዌስሊ መቀደስን ተቀበለ፡ እርሱም “ወዳጄ፡ በመጮኽ፡ ትሞላለህ፡” አለ። ብዙዎችም ይጮኻሉ ነገር ግን አይሞሉም። ጴንጤቆስጤ በልሳኖች ሲናገሩ—በማይታወቁ ልሳኖች ሲናገሩ፡ “ወዳጄ፡ አገኘሃት፡” ይባባላሉ። ብዙዎቹ ግን አልተሞሉም።

በእነዚያ ምልክቶች የሚታወቅበት ምንም መንገድ የለም። “ዛፍን የምታውቁበት ብቸኛ መንገድ፡” ኢየሱስ እንዳለ፡ “በሚያፈራው ፍሬ ነው፡” የመንፈስ ሥራዎች፡ የመንፈስ ፍሬ። በኃይል የተሞላ ሰው ስትመለከቱም፡ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ነው፡ ከዚያ የተለወጠ ህይወት ታያላችሁ። ያመኑትን ሲከተሏቸው እነዚህን ምልክቶች ታያላችሁ፡- “በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፡ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ። እባብ ቢነድፋቸው፡ አይጎዳቸውም። የሚጠጣ ገዳይ ነገር፡ ቢጠጡ፡ አይገድላቸውም። በታመሙ ሰዎች ላይ እጃቸውን ይጭናሉ፡ እነሱም ይድናሉ።” ማይ! እነዚህ ምልክቶች የሚያምኑትን ይከተሏቸዋል። ግን ወደ እነዚያ እንዴት ትገባላችሁ? ስጦታዎቹ በአካሉ ውስጥ ናቸውና። ወደ አካሉ እንዴት ትገባላችሁ? ገባሁ ብላችሁ በመናገር አይደለም፥ ወደ አንዱ አካል በመጠመቅ ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 12፡13)። በአንድ መንፈስ

ሁላችንም ወደዚያ እካል ተጠምቀናል ስለዚህ ስጦታዎች ሁሉ ለእኛ ናቸው። ጌታ ይባርካችሁ።

86 አሁን፡ ይህን ቅጂ የሚሰማ ሰው ወይም እዚህ ካላችሁ መካከል ይሄን የሚቃወም ካለ፡ አስታውስ፡ ወንድሜ፡ በፍቅር ይሁን፡ እኔ እወዳችኋለሁና።

**93.** ዛሬ ማታ የመጀመሪያው ጥያቄ፦ **ወንድም ብራንሃም፡ ቴሌቪዥን ለዓለም እርግማን ነው ብዬ እሰባለሁ። አንተስ ምን ታስባለህ?**

87 እሺ፡ ማንም ይጻፈው ማንም፡ እኔም ከአንተ ጋር እስማማለሁ። ለአለም እርግማን አድርገውታል። ለዓለም በረከት ሊሆን ይችላል፡ ነገር ግን እርግማን አድርገውታል። እንደዚህ አይነት ነገር ሁሉ፡ ውድ ወገኖቼ፡ በራሳችሁ ላይ የምትመለከቱት ነገር ነው። ቴሌቪዥኑ እርግማን ከሆነ፡ ጋዜጣውም መርገም ነው፡ ሬዲዮውም መርገም ነው፡ እና ብዙ ጊዜ ስልክም ያው ነው። አያችሁ፡ አያችሁ፡ አያችሁ፡ አያችሁ? ከሱ የምታተርፉት መርገም ነው። ይሁን እንጂ በቀደም ማታ የተናገረው ሰውዬ፡ ከእንግዲህ ወዲህ በቴሌቪዥን ምንም ፕሮግራም አናደርግም ብሏል፥ በጣም ብዙ ገንዘብ ነው። ምስኪን የሙሉ ወንጌል ሰባኪ ፕሮግራሙን በቴሌቪዥን ለማስተላለፍ አቅም የለውም። ስለዚህ... ያ ወንድም በቀደም ማታ ላይ፡ ይመስለኛል፡ ከሆነ ቦታ ነው፡ እንግዲህ “ከሬድዮዎቻችሁ አቧራውን አራግፉ፡” ብሏል፡ ማለት የሆነ ሰው፡ ወይም፡ “ከየጥጉ አንስታችሁ ፕሮግራሞቹን ማዳመጥ ጀምሩ” ብሎ ተናግሯል። ይህ ትክክል ነው።

88 አንተ ውድ ሰው፡ የትም ሁን፡ እኔ ግን፡ በርግጠኝነት ከአንተ ጋር እስማማለሁ። በሰው ልጆች ላይ ክፉኛ መርገምት እየሆነ መጥቷል። በዚያ ውስጥ ይህን ሁሉ ለግብር ወደ መንግሥት መሄድ ያለበትን ገንዘብ እነሱ ይወስዱታል፡ እና በሲጋራ እና ውስኪ ፕሮግራሞች እና በመሳሰሉት ነገሮች ላይ በማስታወቂያ ላይ ያውሉታል፡ እርሱም በመንግስት ግብር ላይ ተመላሽ ያጽፉታል፥ ከዚያም እየዞሩ ሰባኪዎችን እየያዙ ትንሽ ገንዘብ ለማግኘት ወደ ፍርድ ቤት ይጎትቷቸዋል። ከአንተ ጋር እስማማለሁ፡ እጅግ አሰቀያሚ ነገር ነው። አሁን፡ ያ አይደለም... ታውቃላችሁ፡ ውጤቱ ያ ነው። አመሰግናለሁ፡ እህት፡ ወንድም፡ ይህን ጥያቄ የጠየቀ ሰው።

**94.** አሁን፡ ይኸኛው ደግሞ በጣም ጥሩ ነው። ጥያቄው፦ **በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ አንደኛ ሳሙኤል 18:10 ላይ፡ ከእግዚአብሔር የሆነ ክፉ መንፈስ እንዲህ እና እንዲያ አድርጓል ይላል። “ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ክፉ መንፈስ” ምን ማለቱ እንደሆነ አልገባኝም። እባክህ ይብራራልኝ።**

89 እሺ፡ ምናልባት በጌታ እርዳታ፡ እችላለሁ። እግዚአብሔር ክፉ መንፈስ ነው ማለት አይደለም። ይሁን እንጂ የሁሉም ነገር መንፈስ ግን ለእግዚአብሔር ተገዥ ነው። እና ሁሉም ነገር እንደ ገዛ ፈቃዱ ይሰራል። አየህ?

90 አሁን፡ በጥያቄህ ላይ፡ ሳኦልን ሊያሠቃየው ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለወጣው ክፉ መንፈስ ነው የምታወራው። በመሰረቱ፡ ከእምነቱ ወድቆ፡ ስለነበረ፡ በተበላሸ-ሁኔታ በማይረባ—መንገድ፡ ስሜታዊ ሆኖ ነበር። እና እምነታችሁን ስትክዱ፡ ክፉ መንፈስ—እግዚአብሔር ክፉ መንፈስ እንዲያሰቃያችሁ ይፈቅዳል።

91 አንድ ነገር ላነብላችሁ እፈልጋለሁ—በፍጥነት። እዚህ ላይ ሌላ አሳብ አለኝ። አያችሁ? መንፈስ ሁሉ ለእግዚአብሔር መገዛት አለበት። ኢዮሣፍጥና አክዓብ ወደ ጦርነት ሲወጡ ታስታውሳላልችሁ? እንደምታውቁት ከሁሉ በፊት፡ እንዲህ ሆነ—ሁለቱም በበሩ ላይ ቁጭ አሉ። ኢዮሣፍጥም ጻድቅ ሰው ነበረ፡ እና እንዲህ አለ (ሁለቱ ነገሥታት ቁጭ ብለው፡ ሠራዊታቸውንም አንድ አደረጉ) እና እንዲህ አለ "መሄድ አለብን ወይስ የለብንም ከእግዚአብሔር ዘንድ እንጠይቅ፡" አለው።

92 አክዓብም ሄዶ እያበላ ያሰባቸው፡ አራት መቶ ነቢያትን፡ ሁሉም፡ አንድ ላይ ሰበሰባቸው፥ በጥሩ ሁኔታ ላይ ነበሩ። ወደዚያ ወጥተውም፡ ሁሉም በአንድነት ትንቢት ተናገሩ፡ እንዲህም አሉ፡ "ውጣ፡ እግዚአብሔርም ድልን ይሰጥሃል። ወደ ሬማት-ዘገለዓድ ውጣ በዚያም እግዚአብሔር ነገሩን ያከናውንልሃል።" ከመካከላቸው አንዱ ለራሱ ጥንድ ቀንዶች ሠርቶ እንደ ምሳሌ ወዲያ ወዲህ ማለት ጀመረ፡ "በእነዚህ የብረት ቀንዶች፡ ከአገሪቱ ውስጥ ታሳድዳቸዋለህ፥ ሁሉ የአንተ ነው፡" ብሎ ተናገረ።

93 ነገር ግን ታውቃላችሁ፡ የእግዚአብሄር የሆነ ሰው ግን በእነዚህ ነገሮች እንዳይነካ የሚያደርገው አንዳች ነገር አለ። አያችሁ? ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር ካልተሰማማ፡ የሆነ ችግር አለ። እውነተኛ የሆነ አማኝ ሁሉ... ኢዮሣፍጥም አለ; "እንግዲህ፡ እነዚህ አራት መቶዎቹ ደህና ይመሰላሉ። ጥሩ ሰው ይመሰላሉ።"

አክዓብም ቀበል አረገና "ኦህ፡ በጣም ናቸው፡" አለው።

ኢዮሣፍጥ ግን፡ "ከነዚህ ውጪ ሌላ አንድ የለህም ወይ" አለው? በአንድ አሳብ የተሰማሙ አራት መቶ እያሉ አንድ ተጨማሪ ለምን አስፈለገ? በትክክል የማይመስል ነገር እንዳለ ስለተረዳ ነው። አያችሁ?

እንዲህ አለው፡ "አዎን፡ አንድ አለ፡ የይምላ ልጅ፡ እዚያ ጋር አለ፡" "እኔ ግን እጠላዋለሁ፡" አለ። አዎና። በማንኛውም ጊዜ ቤተክርስቲያኑን ትዘጋበታለህ። ከአገር የምታሰባርረው አይነት ሰው ነው። አያችሁ? አዎና። "እጠላዋለሁ።"

"ለምን ትጠላዋለህ? "

"ሁልጊዜ በእኔ ላይ ክፉ ትንቢት ይናገራል።" ኢዮሣፍጥ በዚያን ጊዜ የሆነ ነገር እንዳለ አውቋል—የሆነ ነገር ትክክል አልነበረም።

ስለዚህም "ሄዳችሁ ሚክያስን አምጡ፡" አላቸው።

እነርሱም ሊፈልጉት ወጡ፡ እሱም መጣ... እነርሱም በሄዱ ጊዜ፡ መልእክተኛ ልከው እንዲህ አሉት፡ "አሁን፡ አንዴ። አሁን፡ ይኸውልህ በሰነመለኮት የተመረቁ አራት መቶ ዶክተሮች ተገኝተዋል። በፒኤች፡ በኤልኤልዲ፡ እና በሁሉም ነገር፡ በአገሪቱ ውስጥ ካሉ ሁሉ የተመረጡ ናቸው።" "አሁንም፡ አንተ ምስኪን መሃይም ሰው፡ ከእነዚያ ቀሳውስት ሁሉ ጋር፡ መቃረን የለብህም፡" አሉት።

94 ይምላም እንዲህ አለ፡ ወይም ሚኪያስ ማለቴ ነው፡ እና እንዲህ አላቸው፦ "እግዚአብሔር በአፌ ውስጥ እስኪያስቀምጥልኝ ድረስ ምንም አልናገርም፡ እሱ የሚናገረውን በትክክል እናገራለሁ።" ይህ ደስ ይለኛል። ደስ ይለኛል። በሌላ አባባል፡ "በቃሉ ላይ እጸናለሁ።" ሌሎቹ ምንም ቢሉ። "ይሄው ነው፡"

አላቸው፡ እነሱም አሉት፡ “እኔ ነግሬሃለሁ። መጣል ካልፈለግህ በቀር፡ እነርሱ እንደሚሉት ማለት አለብህ።”

ስለዚህም ወደዚያ ወረደ። እርሱም አለው፡ “ወደ ላይ ልውጣን? ”

“ቀጥል፡” አለው። እንዲህ አለ፡ “ዛሬ ሰጠኝ። በጌታ ፊት ላቅርበው።” ደስ ይላል። በዚያች ሌሊትም ጌታ ተገለጠለትና፡ በማግሥቱም ወጣ። እና ወደዚያ እንደወጣ፡ እንዲህ አለ፡ “ሂድና ተከናወን፥ እስራኤል ግን እረኛ እንደሌላቸው በጎች፡ በተራሮች ላይ ተበትነው አየሁ፡” አለው። ኦህ፡ ማይ! ያም እንደ እብድ አረገው።

እርሱም፡ “አልነገርኩህምን? አውቄዋለሁ። ሁልጊዜ በእኔ ላይ ክፉ ይናገራል፡ የሚያደርገውም ልክ እንደዚህ ነው።”

95 ለምን? ከቃሉ ጋር ስለጸና ነው። ለምን? ከእርሱ በፊት ከነበረው፡ ከእውነተኛው ነቢይ፡ ከኤልያስ ዘንድ የእግዚአብሔር ቃል ወጣ፡ “የንጹሑን የናቡቴን ደም አፍስሃልና፡ ውሾችም ደምህን ይልሳሉ፡” ተብሎ ነበር። ክፉውንም ነገረው። ኤልሳዕ ወደ ሰማይ ሄዶ ነበርና። ነገር ግን ኤልሳዕ የእግዚአብሔር ቃል እንዳለው አውቆ፡ በቃሉ ጸንቶ ኖረ። በቃሉ ላይ መጽናት። ይህ ደስ ይለኛል።

96 መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው ካለ፥ ኃይሉ አሁንም አንድ ከሆነ፥ መንፈስ ቅዱስ የተጠማ፡ ይምጣ፡ ከቃሉ ጋር ይጽና ነው። አዎን፡ ወዳጄ! ሌሎች ምንም ይበሉ። ምንም ያህል ቢመገቡ የቱንም ያህል ትምህርት ቤት ቢገቡ፡ ከዚህ ጋር የሚገናኝ ነገር የለውም።

ስለዚህም እንዲህ አለ... ይህ ታላቅ ሰው በራሱ ላይ ባሉት ቀንዶች፡ ከአገሪቱ እና ከንጉሱ ፊቱ—የሚገፈትረው፡ መጣና (ምስኪኑን ሰባኪ) አፉ ላይ መታው። ተራ ሆሊ ሮለር መሆኑን ስለሚያውቅ ማንም እንደማይጠይቀው ያውቃል። ስለዚህ እንዲሁ አፉን መታው። እንዲህም አለው፦ “አንድ ነገር ልጠይቅህ እፈልጋለሁ።” እንዲህ አለ፡ “ከገባህ የእግዚአብሔር መንፈስ ከእኔ አልፎ ወደ አንተ በየት በኩል መጣ? ”

97 “እንደ ምርኮኛ ወደ ውጭ በጓሮው ውስጥ ሲያስቀምጡህ ታውቀዋለህ፡” ብሎ መለሰለት። እንዲህም አለ፡ “እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ አየሁ (አሜን! አሁን ሰሙ!)፡ የሰማይም ሠራዊትም በዙሪያው ተሰበሰቡ።” ጉዳዩ ምን ነበር? የጌታ ነብይ አክዓብ ላይ ምን እንደሚደርስበት አስቀድሞ ተናግሮ ነበር። እግዚአብሔር... የኤልያስ ንግግር አልነበረም፥ ያ የተቀባው ነብይ ነበር። ያ የእግዚአብሔር ቃል ነበረ፡ **ይላል የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር**። ሚክያስም አለ፡ “በታላቅ ጉባኤ ውስጥ የሰማይ ሰራዊት ሁሉ በእግዚአብሔር ዙሪያ ሲሰበሰቡ አየሁ። እርስ በርሳቸውም ይነጋገሩ ነበር። ጌታም አለ፡ ‘ማንስ ይወርድልናል፡ ከእናንተም ወርዶ፡ አክዓብን የሚያታልል፡ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲፈጸም፡ ወደዚያ ወርዶ እንዲመታ የሚያታልለው ማን አለ? ማንስ ይወርድልናል? ’”

98 እንግዲህ፡ አንዱ **ይህን** ወይም **ያንን** ሌላ ሲሉ ነበር። ከተወሰነ ጊዜ በኋላም፡ ክፉ መንፈስ፡ ውሸታም መንፈስ፡ ከታች ወጣና እንዲህ አለ “ብቻ ፍቀድልኝ። እኔ የውሸት መንፈስ ነኝ። ወርጄ ወደ ሁሉም ሰባኪዎች እገባለሁ፡ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ የላቸውምና፥ እንዲህ አደርጋቸዋለሁ

(በትምህርት—የሰለጠኑ ሰዎች ብቻ ናቸውና)—እነሆ ወርጄ፡ በሁሉም ዘንድ እገባለሁ፡ አታልላቸውማለሁ፡ በሐሰት ትንቢት እንዲናገሩ አደርጋቸዋለሁ።” ብሏል አይደል? እና እንዲህ አለ፡ “የምናታልላቸው በዚህ መንገድ ነው።” እና ወረደ።

እርሱም—እግዚአብሔርም “ሂድ ፈቅጄልሃለሁ፡” አለው።

99 ወርዶም ወደ እነዚያ ሐሰተኛ ነቢያት፡ በትምህርት ቤት ወደ-ሰለጠኑ አገልጋዮች ገባና፡ የሐሰት ትንቢት እንዲናገሩ አደረጋቸው። ለእግዚአብሔር ፈቃድ የሚሰራ የውሸት መንፈስ ነበር። ፍቀድልኝ አለ... እዚህ ጋር ምናልባት የምታዩት ሌላ ነገር፡ አንድ ደቂቃ ጠብቁኝ። ይህንን ተመልከቱ። ከእኔ ጋር ወደ አንደኛ ቆሮንቶስ 5ኛው ምዕራፍ፡ 1ኛው ቁጥር፡ አንድ ደቂቃ ብቻ እንድትከፍቱ እፈልጋለሁ። አንደኛ ቆሮንቶስ... ላይ አንድ ነገር ማየት ከፈለጋችሁ፡ እግዚአብሔር አንድ ነገር ሲያደርግ ይህን ተመልከቱ—ክፉ መናፍስት እንዴት እንደሚሰሩ፡ እንዴት—እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ... በጣም ጥሩ፡ ጳውሎስ ሲናገር፦

> **በእናንተ ዘንድ** ዝሙት **እንዳለ ይነገራል፡ እና እንደዚህ** ያለ ዝሙት... **በአሕዛብ መካከል እንኳ አልተሰማም፡...** (በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይህ ሲሆን ምን ታስባላችሁ? )... **የአባቱ ሚስት ያገባ ሰው አለና።**
>
> **እናንተም ታብያችኋል፡ ይልቅስ...** (እስኪ እንየው፡ ሁለት ገጽ የገለጥኩ ይመስለኛል... )... **እ—**እናንተም **ታብያችኋል፡ ይልቅስ እንድታዝኑ አይገባችሁምን፡ ይህን...** (አሁን፡ እዚህ ጋር አንዴ ጠብቁኝ። እ... አዎን፡ ልክ ነው። አዎን።)... **እንድታዝኑ...** (ይኸው።)**... ታብያችኋል፡ ይልቁንስ... እንድታዝኑ አይገባችሁምን፡ ይህን ሥራ የሠራው ከመካከላችሁ ይወገድ።**

100 እኔ አላውቅም። ማንም ሰው በዚህ ነገር ላይ መናገር ወይም መቀነስ አለበት ብዬ አላምንም፡ ሙግቴ ግን እኔ ስለማምንበትን ብቻ ነው፡ አንድ ጊዜ ሰው በመንፈስ ከተሞላ በኋላ ፈጽሞ አይወስድበትም። አያችሁ፡ አያችሁ?

> **እኔ ምንም እንኳ፡ በሥጋ ከእናንተ ጋር ባልሆን፡ በመንፈስ፡ ከእናንተ ጋር ነኝ፡ ከእናንተም ጋር እንዳለሁ ሆኜ፡ ይህን እንደዚህ በሠራው ላይ፡**
>
> **በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ አሁን ፈርጄበታለሁ፡ እናንተና መንፈሴም፡** ከ**ጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ጋር ተሰብሰበን፡**
>
> **መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ፡ እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው።**

101 እግዚአብሔር፡ በዚህ ምድር ላይ፡ አካሉ ለሆነችው ቅድሰት ቤተ ክርስቲያን ይናገራል፡ ያም (ይህ አሁን፡ ከብሉይ ኪዳን በኋላ፡ በአዲስ ውስጥ ነው) በሕዝቡ መካከል በጣም የረከሰ እና የቆሸሸ ሰው እንዳለ ከአባቱ ሚስት ጋር እንደሚኖር ይናገራል። አላቸውም፡ “በክርስቶስ አካል ውስጥ እንደዚህ ያለ ነገር... እናንተ፡ ቤተክርስቲያን ሆይ፡ ለጥፋት ለዲያብሎስ አሳልፋችሁ

ሰጡት... ” አያችሁ? የፈቀደው እግዚአብሔር ነው... እና አንዳች ነገር መደረግ እንዳለበት ካየ፡ መገረፍ ያለበት ሰው ካለ፡ ሰውዬውን ለመመለስ—ግለሰቡን የሚያሰቃዩት ክፉ መናፍስት ይለቅበታል። አሁን፡ ሰውዬው ላይም እንዲህ ሆኖ እናገኘዋለን...

102 ዛሬ በአብያተ ክርስቲያናት ላይ ያለው ጉዳይ ይኸው ነው። ሰው ወደ ክርስቶስ አካል መጥቶ ከአካላት አንዱ ሆኖ ክፉ ማድረግ ሲጀምር፡ ሁላችሁ አንድ ላይ ተሰባሰባችሁ ይህን ተመሳሳይ ነገር አድርጉ... እናንተም፡ የብራንሃም ተበርናክል ሆይ፡ ያንን አድርጉ። ምክንያቱ እሱን እስከያዛችሁት ድረስ፡ በደሙ ስር ነው። እና የቀደመውን ሰራው ደጋግሞ እየደጋገመ የሚሰራ ከሆነ። ተሰብሰባችሁ ለሥጋው ጥፋት ለዲያብሎስ አሳልፋችሁ ሰጡት፡ መንፈሱ ግን—በጌታ ቀን—ይድን ዘንድ ይህ ይሁን። የእግዚአብሔር መግረፊያ ሲገባ ታያላችሁ። ዲያብሎስ ሲይዘው ታዩታላችሁ። የየኣዘው እርኩስ መንፈስ ነው።

103 እና እዚህ የምታዩት ልጅ ታርሟል። ወደ ልቡም ተመልሷል። በሁለተኛው ቆሮንቶስ ውስጥ በእውነት በእግዚአብሔር ፊት ነጽቶ እናገኛለን።

104 እዮብን እዩት፡ ፍጹምና፡ ጻዲቅ ሰው ነው። እግዚአብሔርም ክፉው ዲያብሎስ እንዲመጣበት ፈቀደ፡ መንፈሱን ፍጹም ለማድረግ ቀጣው፡ ሌላም ሁሉ አደረገበት። አያችሁ? ስለዚህ እርኩሳን መናፍስት... እግዚአብሔር እቅዱን እና ፈቃዱን ለመስራት እርኩሳን መናፍስትን ብዙ ጊዜ ይጠቀምባቸዋል።

**95.** አሁን፡ ይሄኛው ደግሞ አከራካሪ የሆነ ጥያቄ ነው። ጥያቄ (ተመሳሳይ የእጅ ጽሑፍ ስለሚመስል፡ አንድ አይነት ሰው ነው ብዬ እሰባለሁ)፥ **ሰው በንጥቀት ለመሄድ መንፈስ ቅዱስ—እንዲለወጥ እና በንጥቀት እንዲሄድ መንፈስ ቅዱስ ሊኖረው ከተገባው፡ ከተጠያቂነት ዓመታት በፊት የሞቱ ህፃናት ሁኔታ ምን ይሆናል? የሚነሱትስ መቼ ነው?**

105 አሁን፡ ወንድሜ፡ እህቴ፡ ይህን ልነግርህ አልችልም። በየትኛውም ቦታ እንደፈለገሁት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምንም ቃል የለውም። ሀሳቤን መግለጽ ግን እችላለሁ። ስለዚህ፡ በእግዚአብሔር ጸጋ ለምታምኑ ይህ ጉልበት ይሆናችኋል። አያችሁ፡ ሰውዬው ማወቅ የፈለገው (በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው። አያችሁ? ) ሰውዬው ማወቅ የፈለገው በትንሳኤው ጊዜ—ህጻናት ምን ይሆናሉ፡ ምክንያቱ መነጠቅ ካለበት መንፈስ ቅዱስ ሊኖረው አይገባም ወይ... እንዳልኩት፡ ትክክል ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ያደረገ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው። እንደዚህ አይደለ—ወደ ሰማይ ለመሄድ አይደለም... መንፈስ ቅዱስ የሚሞሉ ሰዎች ስለመጀመሪያው ትንሳኤ ነው፡ እነሱም የተመረጡት ናቸው። እንዲሁም ቅሬታዎቻቸው... ሌሎቹ ሙታኖች ግን ለሺህ አመት በህይወት አይኖሩም። ከሚሊኒየም በኋላ፡ በሁለተኛው ትንሳኤ፡ በታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ ይነሳሉ። አያችሁ? ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥርዓት ነው። ይህ ሰው ግን ስለ እነዚህ ሕፃናት ማወቅ ይፈልጋል። ህጻናት... በሌላ አነጋገር፡ ከመወለዳቸው በፊት መንፈስ ቅዱስ ነበራቸውን? ተቀብለው ይሆን ወይ? እንግዲህ፡ ይህን እኔ መመለስ አልችልም።

106 አሁን ግን፡ እንዲህ እንበል፥ የሚሞቱ ሕፃናት፡ ወላጆቻቸው ምንም ቢሆኑም፡ እንደዳኑ እናውቃለን። አሁን፡ በዚያ ጉዳይ ላይ ከነቢያት ትምህርት ጋር

አልስማማም። እንዲህ ይላሉ—ከኃጢአተኛ ቤተሰብ የተወለደ ከሆነ፡ ያ ሕፃን ወደ ሲኦል እንደሚሄድ፡ እንደሚበሰብስ፡ መጨረሻውም እንደሚጠፋ ይናገራሉና። እንግዲህ፡ ኢየሱስ... ዮሐንስ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ “እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፡” ብሏል። እንግዲህ ይህ ህጻን ልጅ፡ በእግዚአብሔር ፍርድ ፊት ሊቆም የሚገባው ሰው ከሆነ፡ ኢየሱስ ኃጢአትን ለማስወገድ ስለሞተ፡ ኢየሱስ የሞተበት ዓላማ ኃጢአት ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ለማስወገድ ነው። ኃጢአታችሁ ተሰርዮላችኋል። ኃጢአቴ ተሰርዮልኛል። እና ይቅር የምትባልበት ብቸኛው መንገድ የእርሱን ምህረት በመቀበል ነው። አሁን፡ ህፃኑ ይቅርታውን መቀበል አይችልም፡ ስለዚህ ምንም በደል የለበትም። ፈጽሞ በደል የለበትም። ስለዚህ ወደ መንግሥተ ሰማያት የመሄድ ፍጹም የሆነ ነጻነት ነው።

107 እናንተ ግን እንዲህ ትጠይቃላችሁ፡ “በመነጠቅ ውስጥ ይሄዳሉን?” እሺ—አሁን፡ ይህ የራሴ ቃል ነው፥ ይህ የራሴ እሳቤ ነው። በ... በመጽሀፍ ቅዱስ ማረጋገጥ አልችልም። ይሁን እንጂ ተመልከቱ። እግዚአብሔር፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ ሰው ሁሉ በምድር ላይ እንደሚሆን የሚያውቅ ከሆነ... ይህን ታምናላችሁ አይደል? ትንኝን፡ ቁንጫን፡ ዝንብን ሁሉ ያውቃል፡ በምድር ላይ የሚሆነውን ሁሉ ያውቃል። ይህን ካወቀ...

108 ተመልከቱ። ለምሳሌ፡ ሙሴን እንውሰድ። ሙሴ ሲወለድ፡ ነብይ ነበረ። ኤርምያስን... እግዚአብሔር ኤርምያስን፡ “በእናትህ ማኅፀን ውስጥ ከመፈጠርህ በፊት፡ በማኅፀንዋ ሳትፈጠር፡ አውቄሃለሁ፡ ቀድሼሃለሁ፡ ለአሕዛብ ነቢይ አድርጌ ሾሜሃለሁ።” መጥምቁ ዮሐንስ፡ ከመወለዱ ከሰባት መቶ አሥራ ሁለት ዓመታት በፊት፡ ኢሳይያስ በራእይ አይቶታል፡ “በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምጽ ነው፡” ብሎታል።

109 የእግዚአብሔር አስቀድሞ መወሰን ወይም አስቀድሞ ማወቅ ስለ ትናንሽ ሕፃናት ሁሉንም ያውቃል (አያችሁ?)፡ ምን እንደሚያደርጉ። እንደሚሞቱም ያውቃል። ያውቀዋል። እግዚአብሔር ሳያውቀው ምንም ሊሆን አይችልም። ምንም ሊሆን አይችልም... ልክ እንደ መልካሙ እረኛ፡ እንዴት እንደሚያሰገባ... ይህ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ለመውሰድ፡ መጽሐፍ ቅዱስ **እከሌ-እና-እከሌ** ይላል ማለት አልችልም። ስለራሴ አሳብ ብቻ እወስደዋለሁ።

**96.** አሁን፡ ቀጣዩ ጥያቄ ምናልባት ይህ ሰው ከበቀደም ማታ ከተናገርኩት የወሰደው ይመስለኛል። **ሚስት ልጅ በመውለዷ ትድናለች የሚለውን አብራራልን።**

110 ሚስት ልጅ በመውለዷ አትድንም። አሁን ግን ለአፍታ ያህል ወደ አንደኛ ጢሞቴዎስ 2፡8 እንሂድ። እና መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሕፃኑ የሚናገረውን ብቻ እንወቅ። አሁን፡ ያ የካቶሊክ ትምህርት እንደሆነ አውቄአለሁ፡ ካቶሊኮች ሴቲቱ በመውለድ ትድናለች ይላሉና፡ ልጅ በመውለድ። እንዲህ አነሁን... ይሄን አላምንም። አንደኛ ጢሞቴዎስ 2ኛው ምዕራፍ፡ ከ 8ኛው ቁጥር እንጀምር፡ እና ለአፍታ እናንብብ። እሺ፡ አዳምጡ።

> **እንዲሁም ደግሞ፡** ሴቶቻችሁ **በሚገባ ልብስ ሰውነታቸውን ይሸልሙ...** (ይህን መጠየቅ አይገባን... ይገባናል’ዴ? ይህን ሰሙት።)... **ከእፍረትና...** (አቤት!)... **እራሳቸውን ከመግዛት**

**ጋር፥** በሽሩባና፡ **በወርቅ፡ ወይም በዕንቍ፡ ወይም ዋጋው እጅግ በከበረ ልብስ አይሸለሙ፥** (ወንድሞች ሆይ፡ እዚህ ጋር እያገዝኳችሁ እንደሆነ፡ ተስፋ አደርጋለሁ። በየቀኑ እና በየሶስት ቀኑ የሚቀያየሩ የጸጉር ጌጦች። አያችሁ? ክርስቲያናዊነት አይደሉም።)

**ነገር ግን (እግዚአብሔርን እንፈራለን ለሚሉት ሴቶች እንደሚገባ) መልካም በማድረግ እንጂ።**

ሴት **በነገር ሁሉ** እየተገዛች **በዝግታ ትማር።**

**ሴት ግን**... በዝግታ **ትኑር እንጂ፡ ልታስተምር ወይም... በወንድ ላይ፡ ልትሰለጥን አልፈቅድም።**

**አዳም ቀድሞ ተፈጥሮአልና፡ በኋላም ሔዋን ተፈጠረች።**

**... የተታለለም አዳም አይደለም፥ ሴቲቱ ግን ተታልላ በመተላለፍ ወደቀች።**

**ነገር ግን በመውለድ ትድናለች**... (አሁን፡ ልጆች ስለሚወልዱ፡ ስለ ዓለም ሴቶች እየተነጋገረ አይደለም።)... **በእምነት** ከቀጠለች... (አያችሁ? ከቀጠለች፡ እንዲሁ ናት... ስለሷ የሚናገርላት ሴት ይህች ናት፡ አስቀድማ የዳነች ሴት። ገባችሁ? ) ... በ**ፍቅር በቅድስናም ራሳቸውን እየገዙ ቢኖሩ።**

111 ልጅ በመውለዷ አይደለም የሚያድናት፡ ነገር ግን ልጆችን በማሳደግ፡ ግዴታዋን በመወጣት ነው፡ የልጅ ቦታ የሚተኩትን ድመቶች፡ ውሾች፡ እና ሌሎች-ነገሮች በማሳደግ፡ አይደለም፡ ሌሊቱን በሙሉ ስትዞር ለምታድረዋ የእናት ፍቅር ይሰጣሉ። አንዳንድ ሰዎች ይህን ያደርጋሉ። ይቅርታ፡ ግን ያደርጉታል። ለኔ ይህን መናገሬ በጣም አስቀቂ ነው፡ እውነት ግን እውነት ነው። አያችሁ? ከልጅ ጋር መታሰር አይፈልጉም። ልጅ በመውለድ፡ በእምነት፡ በቅድስና፡ እና በሁሉም ጨዋነት ከቀጠለች ግን፡ ትድናለች። **ከ** የሚለውን ቃል ግን፡ እናንተም ትድናላችሁ፡ ዳግም **ከ**ተወለዳችሁ። **ካ**መናችሁ ትፈወሳላችሁ። **ካ**መናችሁ መንፈስ ቅዱስ ትቀበላላችሁ፡ ተዘጋጁ፡ ለሱ **ከ**ተዘጋጃችሁ። እና እነዚህን ነገሮች ብታደርግ ትድናለች (አያችሁ? )፡ ሴት ስለሆነች ግን አትድንም። ትክክል ነው፡ ወንድም፡ እህቴ። በጭራሽ የካቶሊክ ትምህርት አይደለም። አሁንም ይሄው... ሌላ አከራካሪ የሆነ ጥያቄ። ከዚያም ተጨማሪ ሌላ አንድ ይኖረናል። ለእሱ ጊዜ ያለን ይመስለኛል። ጊዜያችንን እጠቀማለሁ። እንግዲህ፡ እነዚህ—እነዚህ ሁሉ የሪቫይቫሉ ውጤት ናቸው። እነዚህ ጥያቄዎች፡ የስብሰባው ውጤት ናቸው።

**97.** አሁን፡ **ወንድም ብራንሃም** (በታይፕ የተጻፈ ነው)፡ **ሰው በልሳኖች ተናግሮ የራሱን መልእክት ይተረጉም ዘንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነውን? ከሆነ፡ እባክዎን ያብራሩልን። አንደኛ ቆሮንቶስ ወይም ቆሮንቶስ** 14፡ 19 **እና እንዲሁም ቆሮንቶስ** 14፡27።

112 እሺ፡ ወደ መጽሀፍ ቅዱስ ቃል እንሂድና ምን እንደሚል እንይ። ከዚያ በኋላ ይህ ነገር የምናደርገው እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሆኑ አለመሆኑን እናያለን። ሁሌም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆን እንፈልጋለን። እና ቆሮንቶስ 14 ላይ። አሁን፡ ሰውዬው ማወቅ የፈለገው አንድ ሰው በልሳን የተናገረውን የራሱን መልእክት

በራሱ መተርጎሙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከሆነ ነው። “እንዲህ ከሆነ፡ ቆሮንቶስ 14:19ን አብራራልን።” እሰኪ፡ 14 እና 19 እንየው። እሺ፡ ይሄው ነው።

> **ነገር ግን… ሌሎችን ደግሞ አስተምር ዘንድ፡** በማኅበር **እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ፡ አምስት ቃላት… በአእምሮዬ… ልናገር** እወዳለሁ።

አሁን፡ ቀጣዩን መረዳት የፈለጉት፡ 27ኛው ቁጥርን ነው።

> **በልሳን** የሚናገር **ቢኖር፡ ሁለት፡ ወይም ቢበዛ… ሦስት ሆነው፡ በተራቸው ይናገሩ፥ አንዱም ይተርጉም።**

113 አሁን፡ ሰውዬው ለማግኘት እየሞከረ ያለውን ነገር ልውሰድ (እኔ የፈለግኩት—አንዴ የሆነ ነገር አነብላችኋለሁ)። ያ ወንድም ወይም ያቺ እህት ማግኘት የፈለጉት ነገር ግን፡ “በልሳን የሚናገር ሰው የተናገረውን መልእክት እራሱ ሊተረጉም ይገባዋልን? ” አሁን፡ ውድ ወዳጄ፡ በዚሁ ምዕራፍ 13ኛውን ቁጥር ካነበብክ፡ ይነግርሃል፥

> **ስለዚህ በልሳን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ።**

114 አዎን። የራሱን መልእክት መተርጎም ይችላል። አሁን፡ እንዲህ… እናድርግ… እሺ፡ እ… እዚህ ጋር ያለውን በሙላት አንብቡት፡ እና ታዩታላችሁ… ሙሉውን ምዕራፍ አንብቡት። ደስ ይላል፡ ያብራራዋል።

115 አሁን፡ ከዚያ ሳንወጣ… አሁን፡ በልሳን ስለመናገር፡ ይህ እየተቀዳ ስለሆነ፡ በመለኮታዊ ፈውስ እና በክርስቶስ ዳግም ምጽአት እንዲሁም፡ በ—በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ እና በሚመጣው ዓለም ኃይል የማምነውን ያህል፡ በልሳኖች በመናገር አምናለሁ ማለት እፈልጋለሁ፥ የማምነውን ያህል በዚያ አምናለሁ፡ በልሳን መናገር ግን የራሱ ቦታ እንዳለው አምናለሁ ልክ የክርስቶስ መምጣት የራሱ ቦታ እንዳለው ይህም ቦታ አለው፥ መለኮታዊ ፈውስ የራሱ ቦታ አለው፥ ሁሉም ነገር የየራሱ ቦታ አላቸው።

116 አሁን፡ ለእናንተ ሰዎች፡ ይህን ለማለት እድሉን አግኝቻለሁና፡ ላብራራው እፈልጋለሁ። እና ማንንም ከጎዳሁ፡ ማንንም ለመጉዳት አይደለም። ግራ መጋባት ለመፍጠር ፈልጌ አይደለም። ግን ሰሙት። በጴንጤቆስጤ ሰዎች በማይታወቁ ቋንቋዎች መናገራቸው ችግሩ (እኔም ራሴ፥ እኔም ጴንጤ ነኝና። አያችሁ? )… አሁን፡ ችግሩ ይህ ነው፥ ይህም አያከብሩትም። ሌላ ነገር ደግሞ፡ በዘፈቀደ ይለቁታል። ወደ ቃሉ አይመለሱም።

117 አሁን ስሙኝ። መንገዱ ይህ ነው—የቤተ ክርስቲያን አወቃቀር—ይህ ነው። አሁን፡ በጴንጤቆስጤ ቤተክርስቲያን ውስጥ፡ እኔ የዚህች ቤተ ክርስቲያን ፓስተር ከሆንኩ፡ እንዴት እንደማዋቅረው እነግራችኋለሁ (አያችሁ? )፡ ፓስተር ብሆን ኖሮ—ሁሌም እዚህ የምሆን ቢሆን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ላለው የእያንዳንዱ ስጦታ ተከታይ እሆን ነበር። በመጀመሪያ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠመቁ እነግራቸዋለሁ። ከዚያ በኋላ፡ እያንዳንዱ የአንደኛ ቆሮንቶስ 12 ስጦታዎች በቤተክርስቲያኔ ውስጥ መንቀሳቀስ አለበት፡ ወደዚያ ካስገባኋቸው፡ መላውን አካል ይንቀሳቀሳል።

118 አሁን፡ ካስተዋላችሁ… አሁን አስተያየት አልሰጥም። አስታውሱ፡ አንዲት ቃል ባልተቃወምኩ ነበር—ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስን መሰደብ

ይሆንብኛልና። እና ይህን በክፉ እንደማልናገረው እግዚአብሔር ያውቃል። አያችሁ? ነገር ግን ይህን የምለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት እይታ የምሰጣችሁ ለሃያ ዓመታት ያህል ካጠናሁት በኋላ ነው። ወደ ሠላሳ ዓመታት ያህል እየሰበክሁ ቆይቻለሁና። እና በብዙ ነገር አልፌአለሁ፡ በብዙ ነገር ተቦጫጭቄአለሁ፥ ምን እንደሚመስል መገመት ትችላላችሁ። እና እያንዳንዱን ሰው፡ እና አስተምህሮአቸውን፡ አለምን አይቻለሁ። እና መሻቴ ስለነበረ ተቀበልኩት። ከእኔም አልፎ የሰው ልጆች ሁሉ መሻት ነውና። እዚህ ጋር መለየት ነበረብኝ። እናንተም መለየት ነበረባችሁ። እና እንደ ሐሰተኛ ነቢይ ብሄድ፡ ነፍሴን አጠፋታለሁ የእናንተም ከእኔ ጋር አጠፋለሁና። ስለዚህ ከዕለት—ከዕለት እንጀራ የበለጠ ነው፥ ከአንጋፋነት የበለጠ ነው፥ ከሌላው ሁሉ ይበልጣል፥ ለእኔ ህይወት ነው። አያችሁ? ስለዚህ ዘወትር እጅግ ቅን መሆን እፈልጋለሁ።

119 አሁን፡ ወደ አንዳንድ የጴንጤቆስጤ አብያተ ክርስቲያናት ሂዱ፡ የመጀመሪያው ነገር… (ሁሉንም ማለቴ አይደለም። አንዳንዶቹም አሉ… ) ብዙ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብታችሁ መሰበክ ስትጀምሩ፥ በምትሰብክበት ጊዜ፡ አንድ ሰው ተነስቶ በልሳኖች ይናገራል። እንግዲህ፡ ይህ የተወደደ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ፈጽሞ የተሞላ ሊሆን ይችላል፡ ምናልባትም በዚያ ሰው አልፎ የሚናገረው መንፈስ ቅዱስ ሊሆን ይችላል፡ ቁም ነገሩ ግን፡ የሰለጠኑ አለመሆናቸው ነው። ይህ ከመሰውያው የሚነገረው አገልግሎት በምሪት ከሆነ፡ የነብያት መንፈስ ለነብይ ይገዛል። አያችሁ? ተመልከት? “ሁሉም ነገር ይደረግ… ” አሁን፡ ጳውሎስ “አንዱ ሲናገር” ወዘተረፈ፡ ሲል ለምን እንዳለ እንይ… “እሱ በመጣ ጊዜ፡ ግራ መጋባት ነበር።”

120 አሁን፡ የመሰውያ ጥሪ አድርጌ፡ አንዱ ተነስቶ በልሳን ቢናገር። በቃ… እንደው፡ የመሰዊያው ጥሪ አለማድረግ ይሻላል። ያቋርጠዋል። አያችሁ?

121 ከዚያ በኋላ፡ ሌላው ደግሞ አለ። ብዙ ጊዜ ሰዎች ተነስተው ልሳን እየተናገሩ፡ ሰዎች ወዲያ ወዲህ እያዩ፡ ማስቲካቸውን ያኝካሉ። እግዚአብሔር ሲናገር፡ ዝም በሉ፡ አድምጡ! እውነቱ ያ ከሆነ፡ በዚያ ሰው ውስጥ የሚናገረው መንፈስ ቅዱስ ከሆነ፡ ዝም ብላችሁ አዳምጡ፡ አክብሩት። ትርጉሙ ሊመጣላችሁ ይችላልና። አያችሁ? ጸጥ ብላችሁ ጠብቁት፥ ትርጓሜውን ተጠባበቁ። አሁን፡ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ምንም አስተርጓሚ ከሌለ፡ በአካሉ ውስጥ ዝም ሊሉ ይገባቸዋል።

122 ስለዚህ፡ በልሳን ሲናገሩ፡ መጽሐፍ እንደሚል፡ ለራሳቸውና ለእግዚአብሔር ይናገሩ። በማይታወቅ ቋንቋ የሚናገር ራሱን ያንጻልና። አሁን፡ የማይታወቁ ልሳኖች፥ የአነጋገር ዘዬዎች፡ ቋንቋዎች ሌላ ናቸው። “ምንም አይደሉም፡” ነገር ግን ድምጽን የሚያመጣው ሁሉ… ትርጉም አለው ብሏል። ለምሳሌ… መለከት ቢሰማ፡ ድምጹ ምን እንደሚመስል መለየት አለባችሁ (… ስትነፋት) ራሳችሁን ለጦርነት እንዴት ማዘጋጀት እንዳለባችሁ አታውቁም። በልሳኖች የሚናገር ማንም ቢኖር፡ እና “ቱት” ከሆነች፥ ይህች ብቻ ከሆነች፡ ምን ማድረግ እንዳለበት ማን ያውቃል። ነገር ግን **ነጋሪት** ከሆነ፡ ትርጉሙም “ተነሱ” ማለት ነው! **ጥሩምባ** ሲነፋም፡ ትርጉሙ “ቁጭ በሉ።” አያችሁ? ስለ **መንፋት** ብቻ ከሆነ “መንፋት” ነው። ትርጉም ሊሰጥ ይገባዋል፡ እና መናገር

ብቻ መሆን የለበትም። ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፡ ተርጓሚ ከሌለ፡ ተርጓሚ ካለ ግን፡ እንግዲያውስ ልሳኖች የቤተክርስቲያን ናቸው።

123 አሁን፡ ለጥያቄህ፡ ውድ ወዳጄ፡ እንዲህ ይላል፡ "አምስት ሺህ... ሰዎች ይረዱት ዘንድ አምስት ቃላት ብናገር እመርጣለሁ ይላል፡ ሰዎች የማያውቁት አምስት ሺ ቋንቋ (ወይም ከዚያ በላይ) ከመናገር ይልቅ ያላል።" እውነት ነው። ነገር ግን ቀጥላችሁ እንብቡት፥ "... በመገለጥ ወይም በመተርጎም ለማነጽ ካልሆነ በቀር።" እያችሁ? ለማነጽ ነው።

124 አሁን፡ ምን እንደ ሆነ ትንሽ አሳብ ልሰጣችሁ እንዲህ—ቢሆንስ... እያደገች ያለችውን የዚህች ቤት ክርስቲያን እረኛ ብሆን፡ እግዚአብሔር እረኛ እንድሆናት ቢሾመኝ፡ የማስተዳድርበት መንገድ ይህ ነው፦ በዚያ ውስጥ ስጦታ ያለው እያንዳንዱን ሰው እሰበስባቸዋለሁ። እና አገልግሎት ከመጀመሩ ከአንድ ሰዓት በፊት አንድ ክፍል ውስጥ ለብቻቸው፡ እንዲገናኙ አደርጋቸዋለሁ። ከመንፈስ ሰር ቁጭ እንዲሉ አደርጋለሁ። እና መጀመሪያ የሚሆነው፡ አንዱ ይነሣል፡ በልሳን የመናገር ስጦታ አለው። በልሳኖችም ይናገራል። ሁሉም ሰው ጸጥ ይላል። ከዚያም አንዱ ተነስቶ የሚናገረውን ይተረጉመዋል። አሁን፡ ያ ለቤተክርስቲያን ከመነገሩ በፊት፡ መጽሐፍ ቅዱስ በሁለትና በሦስት ምስክሮች መፈረድ አለበት ይላል። አሁን፡ ያ ማለት መንፈሳዊ የመለየት ጸጋ ያለበት ሰው ይሁን (እያችሁ? )፡ ምክንያቱ እነዚያን ነገሮች ብዙ ጊዜ ክፉ መንፈስ ይጠቀምባቸዋል። (እያችሁ? ) ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ ተናግሯል። ይሁን እንጂ፡ የእግዚአብሄር ኃይልም በዚያ ውስጥ አለ። እስኪ ክፉ የማይገባበት ጉባኤ ካለ ንገሩኝ። የእግዚአብሔር ልጆች በሚሰበሰቡበት ክፉ በመካከላቸው የማይገባበት ሰፍራው ካለ ንገሩኝ። በሁሉም ይገኛል። በዚህ አትበሳጩ። እያችሁ? ሰይጣን የትም አለ። አሁን፡ ይኸው ነው። አንዱ በልሳን ይናገራል። እና፡ የመለየት ጸጋ ያላቸው ሶስት ሰዎች ቁጭ ይላሉ። እና አንድ ሰው በልሳን ተናግሮ መልእክቱን ይሰጣል። አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስ በመጥቀስ ሊሆን አይችልም፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ከንቱ ድግግሞሾችን አይጠቀምም፡ እንዲህ እንዳናደርግ ነግሮናል። እያችሁ? ስለዚህ በዚያ መንገድ አይደለም። ለቤተክርስቲያን መልእክት ነው።

125 በዚህ ሪቫይቫል ውስጥ እስካሁን ሁለት ነገሮች አሉን። እያንዳንዳቸው ምን እንደነበሩ ተመልከቷቸው—ፍጹምና፡ እንከን አልባ ናቸው። እያችሁ? ውስጥ ይነካሉ። አንድ ሰው ይነሳል፡ በልሳኖች ይናገራል፡ ይተረጉመዋል፡ ከዚያም ወደ ኋላ ዞር ይላል፡ ለተሰበከው ስብከት ማረጋገጫ ይሆናል። ሌላኛው ደግሞ በቀደም ማታ ተነሣና፡ በትንቢት መንፈስ ሆኖ—እንዲህ አለ፡ እና የሆነ ነገር ተናገረ፡ የሚናገረውን ነገር ሳያውቀው፡ በመጨረሻው ላይ ጮክ ብሎ ተናገረ እንዲህ በማለት፡ "በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው።" ወዲያውኑ በፍጥነት የሆነ ነገር በፍጥነት ያዘኝና "እንድውም ይህ ጌታ ራሱ መምጣቱን የሚያምን የተባረከ ነው፡" አለኝ።

126 እናም ያ—ያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በህንጻው ላይ ፈሰሰ። እያችሁ? ያም ለማነጽ ነው። እኔም ሰዎቹንመንፈስ ቅዱስን መቀበል እንዳለባቸው ለመንገር እዚያ ቆሜ ነበር። ዲያብሎስም በሕዝቡ ዙሪያ ገብቶ፡ "አትሰሙት፡ ጸጥ በሉ፡" ማለት ጀመረ።

እህቴም እንዲህ አለችኝ፡ “ቢሊ፡ አንተ ስትሰብክ በጣም ደስተኛ ነበርኩ፡ ተነስቼ በግድግዳው ውስጥ መዝለል እንደምችል ይሰማኛል።”

እኔም ይኸው ነው። “ተነሺና ዝለይ፡” አልኳት።

ከዚያ እንዲህ አለች፡ “አንተ ያን ማድረግ ስትጀምር ግን፡” “ህዝብ መንጫጫት ጀመረ፡” አለችኝ፡ “ወዲያውም ምንም የማልጠቅም እንደሆንኩ ተሰማኝ፡” አለችኝ።

127 እኔም እንዲህ አልኳት፡ “ዲያብሎስ ነው። ሰይጣን ነው። ያንን የሚያደርገው እሱ ነው፡” “ምንም ቢሆን መነሣት ነበረብሽ፡” አልኳት። መንፈሳዊ መሰዋዕት—መሰዋዕቶችን፡ ሰሙን የሚያመሰግኑ የከንፈር ፍሬ፡ ለእግዚአብሔር የምናቀርብ ካህናት ነን። ኢያችሁ?

128 አሁን፡ አሁን፡ የሆነው ይኸው ነው። ያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ራሱ፡ “የሚያምን የተባረከ ነው” በማለት ለቀቀው... ነገሩ ያ ነውና። እኔ ሁለት፡ ሶስት ተከታታይ ምሸቶች ያንን ለማስረዳት ጣርኩኝ፥ ከዚያ በኋላ፡ መንፈስ ቅዱስ ራሱ (በምሪት) ተናገረ፡ “በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው” አለ። እና ምንም ነገር ከመናገሬ በፊት፡ “ጌታ በዚህ እንደ መጣ የሚያምን የተባረከ ነው።” ማለት እችል ነበር። ኢያችሁ? እኔም ይህን ስናገር ኖሬአለሁ፡ መንፈስ ቅዱስ ማለት እግዚአብሔር በእናንተ ውስጥ ማለት ነው። ኢያችሁ? እነርሱም ገብቷቸዋል። ኢያችሁ? ከዚያም መንፈስ ቅዱስ በሕዝቡ መካከል ወረደ። ትንቢት፡ እንዴት እንደሚያንጽ—ኢያችሁ?

129 አሁን፡ በትንቢት እና በነቢይ መካከል ልዩነት አለ። ትንቢት ከአንዱ ወደሌላው ይሄዳል፡ ነቢይ ግን ከልጅነቱ ይወለዳል። የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል አላቸው! በእነሱ ላይ መፍረድ ፈልጌ አይደለም። በኢሳይያስ፡ ወይም በኤርምያስ፡ ወይም ከነብያት አንዱ ፊት ሲቆሙ አይታችኋቸው አታውቁም፡ ምክንያቱ ለእነሱ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** አላቸው! በሕዝቡ መካከል ሰላለው የትንቢት መንፈስ ግን፡ መጠንቀቅ አለባችሁ፡ ምክንያቱም ሰይጣን ይጠቀምበታል። ኢያችሁ? እንግዲህ። መዳኘት አለበት።

130 አሁን፡ እነሆ ሪቫይቫል—እናደርጋለን። አሁን፡ እናንተ አገልጋዮች ሆይ፡ በደንብ ስሙኝ። ሪቫይቫልን እያዘጋጀን ነው። ይሁን። ወይም መደበኛ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ እያደረግን ነው። ቤተ ክርስቲያን ዘወትር እሳት ናት። ዘወትር መሆን አለበት። ምናልባት፡ ጸጋ ያላቸው አምስት ወይም ስድስት ሰዎች አሉን፥ አንዱ ልሳን ሲናገር፡ ሁለት ወይም ሶስትም በልሳን ሊናገሩ ይችላሉ፡ አራት ወይም አምስት በልሳን ሊናገሩ የሚችሉ ሊኖሩን ይችላሉ፡ በማይታወቁ ልሳኖች፡ በልሳኖች የመናገር ሰጦታ አላቸው። ከመካከላቸው ሁለት ወይም ሶስት መተርጎም ይችላሉ። ምናልባት አንድ—ሁለቱ፡ ወይም ሦስቱ የጥበብ ሰጦታዎች ይኖራቸዋል። በጣም ጥሩ። ሰጦታ ያላቸው ሰዎች ሁሉ፡ ይገናኛሉ... እናንተ... ሰጦታዎች የተሰጣችሁ “ክብር ለእግዚአብሔር፡ በልሳኖች እናገራለሁ! ሃሌ ሉያ!” እንድትሉ፡ ለጨዋታ አልተሰጣችሁም፡ እራሳችሁን እ—እ—እያዋረዳችሁ ነው። የተሰጣችሁ፡ እንድትሰሩበት ነውና። ያልተማሩ በእኛ መካከል ሊኖሩ ስለሚችሉ፡ ድርሻችሁ ዋናው አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት በቤተክርስቲያን ይሁን።

131 ከዚያም ወደ ክፍሉ ገብታችሁ፡ እዚያ ተቀመጡ፡ እናንተ ሰዎች በአንድነት ሁኑ፡ ምክንያቱም በወንጌል ውስጥ የሰራ-ባልደረቦች ናችሁ። እዚያ ላይ ሁኑ። “ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ እንድናውቀው የምትፈልገው ነገር አለን? የሰማይ አባት ሆይ፡ ንገረን በሉ፡” ጸሎትን፡ እና ልመናን አቅርቡ፥ መዝሙርንም ዘምሩ። መንፈሱ በቀጥታ ይወርዳል፡ በአንድ ሰው ላይ ይመጣል፡ በልሳን ይናገራል። አንዱም ተነሥቶ “የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡” ይላል። ምን ይላል? ስሙኝ። “ወንድም ጆንስን አሁን ከሚኖርበት አካባቢ እንዲወጣ ንገሩት፡ ነገ ከሰዓት አገሪቱን የሚጠራርግ አውሎ ንፋስ አለና፥ ቤቱንም ያፈራርሰበታልና። ንብረቱን ይዞ ይውጣ!”

132 አሁን፡ ያ—መልካም ነገር ነው። ነገር ግን አትቸኩሉ። በዚያ ውስጥ የማስተዋል መንፈስ ያላቸው ሶስት ሰዎች መኖር አለባቸው። አንደኛ፡ “ከጌታ ዘንድ ነው” ማለት አለበት። ሌላኛውም፡ “ከጌታ ዘንድ ነው” ማለት አለበት። በሶስት ላይ ሁለት—ሁለት ወይም ሣስት ምስክሮች። በቂ ነው። ከዚያ በኋላ በመዝገብ ውስጥ ይጽፋታል። መንፈሱ የተናገረው ነውና። ያን ጊዜ። ወደ ጸሎታቸው ይመለሱ። ጌታንም ያመሰግኑ።

133 ከአፍታ በኋላ፡ “**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** (ነብይ ይነሣና) **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ ዛሬ ማታ፡ ከኒው ዮርክ ከተማ፥ አንዲት ሴት በሰትሬቸውር ትመጣለች፥ ወደ ሕንጻው በእሰትሬቸውር ትገባለች። በጭንቅላቷ ላይ አረንጓዴ ሰካርፍ ይኖራታል። በካንሰር ሞት አፋፍ ላይ ናት። እንዲህ እንድትሆን ያደረጋት ነገርም ይህ ነው፡ የአሰራ ስድስት አመት ልጅ ሳለች ከቤተክርስቲያኑ ገንዘብ ሰርቃለችና፡ ጌታ አዝኖባታል። እነዚህን ነገሮች እንዲነግራት ለወንድም ብራንሃም ንገሩት። **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ ንሰሐ ከገባች፡ ትፈወሳለች።” ቆይ አትቸኩሉ። ይህ መልካም ነው፡ ነገር ግን አትቸኩሉ። የመለየት ጸጋ ባለቤት ለመባል፡ ሰምህን ወረቀት ላይ ለማሰፈር ትፈልጋለህን? ሰምህን ታሰጠራለህን?

134 “ከጌታ ነው።” አንዱ፡ “ከጌታ ዘንድ ነው” ይበል። ያን—ጊዜ ታሰፍረዋለህ፡ “**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ እነሆ አንድ ሴት ትመጣለች፡ **እንዲህ-እንዲያ** ይሆናል።” የመንፈስ መለየት ያላቸው፡ ሁለት ወይም ሣስት ሆነው ሰማቸውን ይፈርሙበታል። ከዚያ በሙሉ መልእክቶቻቸው ይጨርሳሉ። እሺ።

135 ከአፍታ በኋላ ደወሎቹ ሲደወሉ ይሰማሉ። ቸርች ሊጀመር ነው። ያን ጊዜ መልእክቶቻቸውን ያመጣሉ፡ እዚህ ጠረጴዛው ላይ ያሰቀምጡታል። እዚህ መቀመጥ ያለባቸው እዚህ ጋር ነው። እኔም የሆነ ቦታ እያጠናሁ፡ እየጸለይኩ ነው። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ዝማሬዎች ከተዘመሩ በኋላ እወጣለሁ። ቤተ ክርሰቲያን ሁሉም በሥርዓት ተቀምጧል፡ ሰዎች እየገቡ፡ ቁጭ ብለው፡ እያሰላሰሉ፡ እየጸለዩ ይቆያሉ፥ መሆንም ያለባችሁ እንደዚሁ ነውና። እርስ በርሳችሁ ለመነጋገር ወደ ቤተ ክርሰቲያን አትምጡ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር ወደ ቤተ ክርሰቲያን ኑ። ህብረት አድርጉ። እያችሁ? እና ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት እናደርጋለን። እዚህ መጥተን ሰንናገር፡ ሁሉም በጸጥታ፡ በአክብሮት፡ መንፈሰ ይንቀሳቀሳል። የፒያኖ ተጫዋች የዝማሬ አገልግሎት ከመጀመሩ ከአምሰት ደቂቃ ቀድሞ ይመጣል፡ ጣፋጭ ጨዋታ ይጀምራል፥

በመስቀል ሞተ መድኃኒቴ፡
እኔን ለማዳን ከኃጢያቴ፥

ወይም ሌላ ድንቅ ዝማሬ፡ እጅግ ቀስ ባለ መንገድ። የመንፈስ ቅዱስን መገኘት ወደ ስብሰባው ያመጣል። ገባችሁ? እሺ።

136 ሰዎች ተቀምጠዋል። አንዳንዶቹ መሰውያው ድረስ መጥተው—ከልባቸው ያለቅሳሉ፡ አገልግሎቱ ከመጀመሩ በፊት ንስሐ ይገባሉ። መንፈስ ቅዱስ ሰላለ ነው። አያችሁ? ቤተ ክርስቲያን ምጥ ላይ ነች። ክርስቲያኖች ጸሎት ላይ ናቸው፥ ሰፍራቸውን ይዘዋል። ቁጭ ብለው ማስቲካ እያኘኩ፡ እንዲህ ለማለት አይመጡም፡ "ሄይ፡ ጓደናዬ፡ ሊፒስቲክ አቀብይኝ፥ ይኸውልሽ… ይሄን አርጊልኝ። ታውቂያለሽ። ታውቂያለሽ… በቀደምለታ፡ ሱቅ ላይ በነበርኩ ጊዜ፡ ልንገርሽ፡ ልመነትፍሽ ብዬ ነበር። እንደዚህ አይቼ አላውቅም… ምን ይመስልሻል?" አቤት፡ ይቅር ይበለን! የእግዚአብሔር ቤት ትሉታላችሁ። ምክንያቱም፡ ነውር ነው። የክርስቶስ አካል በአንድነት ሰትሆን። ሁላችንም ቁጭ እንላለን።

አጠገብህ የተቀመጠ ሰውዬ፡ "በቀደም በዚያ ሰንሄድ ታውቃለህ፡ ይሄ **እከሌ-እና-እከሌ** ደግሞም **እከሊት-እና-እከሌ-እና-እከሌ**፡ ብሎ ይናገራል…" ውጭ ቢሆን መልካም ነው፡ እዚህ ጋር ግን የእግዚአብሔር ቤት ነው።

137 ወደ ጸሎት ግቡ፥ ድርሻችሁን ተወጡ። ይህን ለወንድሞች፡ እላለሁ እንጂ፡ ለቤተ ክርስቲያናችሁ አላልኩም። ምን እንደምታደርጉ አላውቅም፥ ለዚህ ተበርናክል እየተናገርኩ ነው። ለጓሮዬ በር እናገራለሁ። አያችሁ? በትክክል።

138 አሁን፡ እንደዚያ ሆናችሁ ሰትገቡ፡ በመጀመሪያ ሊሆን የሚችለው፡ ፓስተሩ ይወጣል። ገና ፍሬሽ ነው ያለው። **ይህን፡ ያንን**፡ እና **ሌላውም** መልስ መስጠት አይጠበቅበትም። ገና ከአገልግሎቱ ጠል—መውጣቱ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሰር ቆይቷል። ብዙ የእሳት ልሳኖች ወደ ተሰበሰቡበት በቀጥታ ይቀላቀላል። አምድ ወደ መሆን ደርሷል (አያችሁ?)፡ እንቅሰቃሴ ላይ ነች። ወደዚህ ዞር ሲል፡ ይሄን ያገኛል። "የቤተክርስቲያን መልእክት ነው፥ '**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ ወንድም ጆንስ ከቤቱ እንዲወጣ። ነገ ከሰአት በኋላ ሁለት ሰዓት ላይ አውሎ ነፋሱ መሬቱን ይጠርጋል። ዕቃውን ይዞ ቶሎ ይውጣ።'" ወንድም ጆንስ ያን ደርሶታል። በጣም ጥሩ። መዝገብ ላይ ሰፍሯል። "**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**፡ ዛሬ ማታ **እከሊት-እና-እከሌ** የተባለች ሴት ትመጣለች፡ እ—እሷም **እንዲህ-እና-እንዲያ** አድርጋለች።" (አሁን እንዳልኩት፡ አያችሁ፡ እንደዛ።) በጣም ጥሩ፡ ያም ሰፍሯል። በቃ። አሁን ሁሉም በየድርሻቸው ተቀምጠዋል። በጣም ጥሩ።

139 ከዚያ በኋላ ወደ መልእክቱ ይገባል። እና መጀመሪያ እንደምታውቁት፡ መሰበክ ይጀምራል። ማንም አያሰናክለውም፥ ሁሉም ሰፍራ ሰፍራውን ይዟልና። አሁን፡ እንቀጥላለን፡ መልእክቱን እንሰብካለን።

140 እና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ… መልእክቱ ሲያልቅ መጀመሪያ የሚሆነው ነገር፡ የፈውስ መሰመር ይጀምራል። እነሆ አንድ ሴት መጣች። አስቀድሞ የሆነ ሰው በልሳን ሰለሷ እንደምትመጣ ተናግሮ ነበር። አያችሁ? እያንዳንዳችን ምን እንደሚሆን እናውቃለን። እያንዳንዳችን እናውቃለን። አሁን በመካከላችሁ ባሉ

የእሳት ልሳኖች እምነት እንዴት እንደሚገነባ ተመልከቱ። አንድ ላይ መሰብሰብ ጀምራለች። ለምን፡ የተጠናቀቀ ሥራ ስለሆነ፥ አበቃ።

ያቺ ሴት… እንዲህ እላለሁ፡ “ወይዘሮ **እከሊት-እና-እከሌ**፡ ከኒውዮርክ ከተማ፡ እዚህ ተቀምጣለች… ” አያችሁ?

“ኦህ፡ ልክ ነው። ይህን እንዴት አወቅክ? ”

“ከጌታ ዘንድ ወደ ቤተ ክርስቲያን የተላከ መልእክት ነው። የአሥራ ስድስት ዓመት ልጅ ሳለሽ፡ **እንዲህ-እንዲያ** በተባለ ቦታ አልነበርሽምን—ከዚያ ከቤተ ክርስቲያን ጥቂት ገንዘብ ወሰደሽ፡ ሰርቀሽ፡ ሄደሻል፡ አዲስ ልብስ አልገዛሽበትምን? ”

“ኦህ፡ ልክ ነው። ትክክል ነው።”

“እግዚአብሔር ዛሬ ማታ በወንድም **እከሌ-እና-እከሌ**፡ በልሳን ይህን ተናግሮናል፥ ወንድም **እከሌ-እና-እከሌ** ተረጎመው፥ ወንድም **እከሌ-እና-እከሌ** እዚህ ጋር እንዲህ ተናገረ፡ መናፍስት በመለየት ጸጋ፡ ከጌታ ዘንድ እንደሆነ መሰከረ። ይህን እውነት ነው።”

“አዎን!”

“ከዚያ በኋላ፡ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይልሻል**፡ ሂጂና አስተካክይ፡ ከካንሰር ነጻ ትወጫለሽ።”

141 ወንድም ጆንስ ወደ ቤቱ ሄዶ፡ የጭነት መኪና ያመጣና፡ የቤት ዕቃውን፡ ይጭንና፡ ከዚያ ይወጣል። ነገ ከሰአት በኋላ ሁለት ሰዓት ላይ፡ ዞዊ! ነገሩን ሙሉ በሙሉ ያተረማምሰዋል። አያችሁ? ከዚያ በኋላ ቤተ ክርስቲያን ክብር ትሰጣለች… “ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ስለ ቸርነትህ፡ ተመስገን።” ስለዚህ፡ ቤተ ክርስቲያንን፡ ማነጽ ማለት፡ ያ ነው።

142 እሺ፡ ይህ ሁሉ ከተናገሩ በኋላ ካልተፈጸመስ? ያን ጊዜ ክፉ መንፈስ በመካከላችሁ እንዳለ ታውቃላችሁ። ያንን ክፉ ነገር እያስፈልጋችሁም። ስማያት በጴንጤቆስጤ እውነት ተትረፍርፈው ሳለ—ክፉው ምን ይጠቅማችኋል? ከዲያቢሎስ ዘንድ ያረጀ ምትክ አትቀበሉ። እውነት የሆነውን ተቀበሉ። እግዚአብሔር ይዞላችኋልና። እግዚአብሔር አስቀድሞ ትክክል እንደሆናችሁ እስኪያረጋግጥ ድረስ፡ ሁሉንም ነገር አስቀምጣችሁ፡ ከእንግዲህ ጉባኤዎች አታድርጉ፡ ምክንያቱም በወንጌል ሥራ ላይ የቤተ ክርስቲያን ረዳት ናችሁ። አሁንስ፡ ምን እንደሆነ ተረድታችኋል?

143 እና ልሳኖች፡ የማይታወቁ ልሳኖች… ሁሉም ሰው—የሚናገርውን ያውቃል። ይናገራል፡ ይሁን እንጂ ድምጽ ሁሉ ትርጉም አለው። ይህም ትርጉም አለው። [ወንድም ብራንሃም አጨበጨበ—አርታዒ።] “ግላክ፡ ግላክ፡ ግላክ!” ይ—ይህም—በሆነ ቦታ ላይ ትርጉም አለው።

144 አፍሪካ በነበርኩበት ጊዜ፡ አላመንኩም ነበር፡ ነገር ግን ድምጽ የሚፈጥር ነገር ሁሉ የሆነ ትርጉም ነበረው። መጽሐፍ ቅዱስም ድምጽ የሚያወጣ ሁሉ፡ ትርጉም የሌለው ነገር የለም። እያንዳንዱ ድምፀ ለሆነ ነገር የሆነ ትርጉም አለው። ምክንያቱም፡ ሰዎች ሲናገሩ እሰማለሁ… “የእግዚአብሔር ልጅ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡” እላለሁ።

145 ከመካከላቸው አንዱ ይመጣና [ወንድም ብራንሃም የአፍሪካን አስተርጓሚ ድምጽ አስመስለ ይላሉ—አርታዒ።]። ሌላ ይመጣና [ወንድም ብራንሃም ምሳሌአዊ ገለጻ አደረገ።]። ይህ ሁሉ "የእግዚአብሔር ልጅ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡" ስለተባለ ብቻ ነው። አያችሁ? አንድ ነገር… ለእኔ ምንም ትርጉም የለውም፡ ለእነሱ ግን እኔ ለእናንተ እንደነገርኳችሁ ቋንቋ ነበር። የዙሉ፡ ፆሳ፡ ባሱቶ፡ እና ሌሎች፡ ተርጓሚዎች ሁሉ ሲመጡ፡ የተባለው ነገር በሙሉ፡ ሁሉም ይረዱታል። እና እነዚያ ሰዎች ሲያጉተመትሙ የምትሰሟቸው ነገሮች፡ ማጉተምተም ይመስላችኋል፡ አይደለም፥ ትርጉም አለው። ስለዚህ ልናከብረው ይገባናል፡ ስፍራውን መጠበቅ አለባችሁ።

146 አሁን ደግሞ፡ ምናልባት መልእክት የለም። እና፡ ጉባኤው አልቆ፥ የመሰውያ ጥሪ ተደርጓል። ከአፍታ በኋላ የሆነ ሰው ይመጣል (ምንም መልእክት አልነበረም) አንድ ሰው እድሉን እንዳገኘ ይነሳል። መንፈስ ቅዱስ… አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ብሏል፡ "ተርጓሚ ከሌለ ዝም ይበል።" ምንም ያህል መናገር ቢያምርህም፡ ጸጥ በል።

147 "እኔ አልችልም፡" ብላችኋል። መጽሐፍ ቅዱስ ትችላላችሁ ብሏል። አያችሁ? ስለዚህ—ይኸው ነው። አያችሁ? ጸጥ ይበል።

148 ከዚያ በኋላ፡ ነገር ሁሉ ስርዓት የሚይዝበት ጊዜ፡ ሲገኝ፡ ያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ መልእክቱን እንዲናገር ካስገደደው፡ ያን ጊዜ ይናገር። ማድረግ ያለባችሁ ይህ ነው። ተርጓሚው ይመጣል፡ እንዲህም ይላል፡ "እዚህ ውስጥ ሳሊ ጆንስ የምትባል ሴት አለች (ይህ ስም ያላት ሴት እንደማትኖር ተስፋ አደርጋለሁ፡ ግን… ) ሳሊ ጆንስ። (አያችሁ? ) ጥሪ የምናደርግላት የመጨረሻ ሌሊት ይህ እንደሆነ ንገሯት። በህይወት የምትቆይበት ጊዜዋ አጭር ነው ንስሓ ግቢ በሏት።" አሁን፡ ሳሊ ጆንስ በተቻላት በፍጥነት ወደ መሠዊያው ትሮጣለች (አያችሁ? )፡ ምክንያቱም ይህ የመጨረሻ ጥሪዋ ነው። አያችሁ? መልእክት መስጠት እንዲህ ነው፡ ወይም ምስክር፡ ወይም ሌላ።

149 በሥራ ላይ ያለችው የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ማለት ይህች ናት። እርኩሳን መናፍስት ሊገቡባት የሚችሉበት፡ ምንም መግቢያ አይኖራቸውም… መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል ይናገራልና፡ "ተራ በተራ ይሁን፡ እና ሶስት በመሆን፥ ሁለት ወይም ሶስትም ይፍረዱት።" ቤተ ክርስቲያን ማለት እንዲህ ናት። ዛሬስ ምን ላይ ደርሰናል? መዝለል፡ መ-መንቀጥቀጥ፡ ሌላው በልሳን እየተናገረ መሳሳቅ፥ ሌላውም ሌላ ነገር ያያል፡ ስለ ሌላ ነገር ማውራት እና ማጨናነቅ፥ ፓስተሩ አንድ ነገር እያደረገ፥ ሌላው በዙሪያውን ያውካል። እንግዲህ፡ ይህ ልክ አይደለም። ምናልባት ፓስተሩ እየሰበከ ሊሆን ይችላል፡ እና የሆነ ሰው ተነስቶ ያቋርጠዋል… ምናልባት መጽሐፍ ቅዱስን እየተነበበ… መጽሐፍ ቅዱስ እየተነበበ ሳለ፡ ሌላ ሰው ከበስተጀርባ ልሳን ይናገራል። ኦህ፡ እንዲህ አይሁን! አያችሁ? ሰባኪው በመድረክ ላይ ይሰብካል፡ ሌላው ይነሣና፡ ልሳን በመናገር ያቋርጠዋል። ችግር የለውም። መንፈስ ቅዱስ አይደለም ማለቴ አይደለሁም፡ ይሁን እንጂ የመንፈስ ቅዱስ አጠቃቀም መረዳት አለባችሁ (አያችሁ? )፡ አጠቃቀም።

አሁን፡ እ—እንዲህ… ለአንድ ተጨማሪ ጥያቄ ስፍራ አላችሁ? እንግዲያውስ፡ ነገ እሁድ። እንዲህ፡ እናደርጋለን… እንዲህ… አንድ እዚህ

አለ። በጣም መልካም ይመስለኛል። አሁንም፡ ሁላችሁ ለተጨማሪ ጥቂት ደቂቃዎች ከታገሳችሁኝ፡ እባካችሁ። እና፡ እንዲህ አደርጋለሁ... ይህን—ይህን እንድትረዱት እፈልጋችኋለሁ። ሆን ብዬ ያስቆየሁት ነገር ነው። ይህች የመጨረሻዬ ናት።

አሁን፡ መጀመሪያ፡ ሰውዬው የጠየቃቸውን ሁለት ነገሮች አነባለሁ። በሚያምር የእጅ ጽሑፍ፡ ባረጀ ወረቀት ላይ የተጻፈ ጽሑፍ ነው። ምማን እንደሆነ አላውቅም፡ በሁለቱም—ስም አልተፈረመበትም።

**98. ወንድም ብራንሃም፡ አገልጋዮች በአገልግሎታቸው ታዳሚዎቹን ይህን ያህል መሰጠት እንዳለባቸው፡ እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው በመናገር ለገንዘብ ረጅም ልመናዎች ማድረግ አለባቸውን? ይህ ትክክል ከሆነ፡ ማወቅ እፈልጋለሁ። ወይም ስህተት ከሆነም፡ ማወቅ እፈልጋለሁ። ይህ በጣም ረብሾኛል።**

150 አሁን፡ ይኸውልህ፡ ወዳጄ፡ እኔ የማስበውን፡ እኔ የማስበውን ነገር እነገርሃለሁ። አያችሁ? እንግዲህ፡ ይህ ማልካም ነገር አይደለም። እጅግ አስከፊ ነገር ይመስለኛል።

151 እና፡ እንደሚመስለኝ። ወደ ማሳው የላከኝ እግዚአብሔር ነው። እኔ ራሴ የተጣበብኩባቸው ጊዜአቶች አጋጥመውኝ ተመልክቻለሁ... እና ምንም አይነት ገንዘብ እ—አልነበረኝም። እኔም "የመባውን ሳህን አዙሩ፡" አልኳቸው።

ሥራ አስኪያጁም ወደ እኔ መጥቶ፡ "ተመልከት፡ ቢሊ፡ ዛሬ ማታ የአምስት ሺህ ዶላር ዕዳ አለብን፡ ጓዴ። እሱን ለመክፈል ጀፈርሰንቪል ላይ ገንዘብ ይዘሃል'ዴ? "

152 እኔም "ምንም ችግር የለም። እግዚአብሔር ነው የላከኝ፡ ባይሆን ኖሮ አልመጣም ነበር። (አየህ? ) የመባውን ሳህን ብቻ አዙሩት፡" እለዋለሁ።

እና ስብሰባው ከማለቁ በፊት፡ አንድ ሰው ይመጣና "ታውቃለህ፡ ጌታ አምስት ሺህ ዶላር እንድሰጥ በልቤ አኖረ፡" ይላል። አየህ፡ አያችሁ? በመጀመሪያ፡ ያንን ለማድረግ ምሪት ተቀበሉ።

153 በመጎተት፡ እና በመለመን፡ ገንዘብንም በማጭበርበር አላምንም። ስሕተት ይመስለኛል። አሁን፡ ወንድሜ ሆይ፡ አንተ ራስህ ይህን ያደረግክ እንደሆነ፡ ስሜትህን መጉዳት አልፈልግም። አየህ? ም—ምናልባት ያንን ለማድረግ ከእግዚአብሔር ዘንድ ቀጥተኛ-የሆነ-ምሪት ተቀብለህ ይሆናል። እኔ ግን ይህን የምናገረው ስለራሴ ነው። በዚያ አይነት ነገር አላምንም።

154 አሁን፡ እየዞሩ የሚናገሩ አገልጋዮችን አውቃለሁ... በቅርብ ጊዜ፡ አይቻለሁ... ጴንጤቆስጤዎች ግን፡ አይደሉም፡ ሌሎች ናቸው... እና፡ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው (አያችሁ)፡ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ናቸው። በትልቅ የካምፕ ጉባኤ ላይ ነበር። ገርቲ፡ አንቺም ነበርሽ፡ ሌሎች ብዙዎችም ነበሩ። እናም በአንድ ታዋቂ የሐይማኖት ተቋም ውስጥ ከከሰዓት ቀኑን ሙሉ እያካሄዱ ነበር—ሁለት ወይም ሶስቱ አንድ ላይ ነበሩ (እነዚያ መደበኛ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡ እዚህ ከተማ ውስጥ እንዳሉ ዘመናዊ ቤተክርስቲያኖቻችን፡ እና የመሳሰሉት) በትልቅ ስብሰባ ላይ—እና ቀኑን ሙሉ እንዲህ ሲናገሩ ዋሉ፡ መድረክ ላይ ቆሞ—በስብሰባው ላይ ገንዘብ ካላበረከቱ፡ እግዚአብሔር

ሰብላቸውን እንደሚያጠፋ፡ ልጆቻቸውን ፖሊዮ እንደሚታመሙ፡ እና ልዩ ልዩ ነገር በማለት እያስፈራሯቸው ነበር። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ከፊት ሆኖ፡ እውነት እንደሆነ እመሰክራለሁ። "ለእግዚአብሔር እና ለተከታዮቹ ሰድብ ነው፡" አልኩ። እግዚአብሔር ከላካችሁ፡ ኃላፊነት ይወሰዳል። እሱ ካልላካችሁ ግን፡ የሐይማኖት ተቋሙ ኃላፊነት ይወሰዳል። እናንተ—ግን... እግዚአብሄር ከላካልችሁ፡ ኃላፊነት ይወሰዳል።

## 99. በመንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ስላለው የገና ጨዋታስ?

155 እንግዲህ፡ ስለክርስቶስ ከሆነ፡ ምንም ችግር ላይኖረው ይችላል። ስለ ሳንታ ክላውስ ከሆነ ግን፡ በሱ አላምንም። ጨርሼ አ—አድጌአለሁና— ከዚያ ነገሮች ጨርሼ አድጌአለሁ። በሳንታ ክላውስ በጭራሽ አላምንም። አያችሁ? እንዲሁም በአንዳንድ የክሪስማስ ነገሮቻቸው አላምንም፡ ከንቱ ነገር ይመስለኛል። እና... እኔ እንደማስበው የክርስቶስ የሆነውን ሁሉ ከክሪስማስ አውጥተው ሳንታ ክላውስን የተኩት ይመስለኛል።

156 እና ሳንታ ክላውስ ልብ ወለድ ታሪክ ነው። (የልጆችን ስሜት፡ እየጎዳሁ እንደማይሆን፡ ተስፋ አደርጋለሁ።) ነገር ግን ልንገራችሁ። በቅርብ ጊዜ፡ የዛሬ ሃያ-አምስት፡ ሰላሳ አመታት በፊት፡ አንድ አገልጋይ እዚህ ከተማ ላይ መጥጦ ነበር፡ እዚህ ከተማ ውስጥ ያለውን የታላቅ ቤተ ክርስቲያን—ፓስተር ነው፡ በደንብ እንተዋወቃለን፡ የቅርብ ጓደኛዬ ነው፡ ወደ እኔ መጣ። ቻርሊ ቦሃኖን ነው (ወንድም ማይክ፡ ጥሩ ጓደኛዬ የሆነውን ቻርሊ ቦሃኖንን፡ ታስታውሰዋለህ)... በዚያ በቢሮው ውስጥ ቁጭ አለና "ለልጆቼ ወይም የልጅ ልጆቼ ይሄንን ውሸት ከእንግዲህ ወዲህ አልነግራቸውም፡" አለኝ። እንዲህም አለ፡ "ትንሹ ልጄ አሥራ ሁለት ዓመት ሲሞላው ወደ እኔ መጣና፡ ስለ ሳንታ ክላውስ ተናገረኝ... " እርሱም፡ አለ፡ "ለምን... የኔ ውድ፡ የምነግርህ ነገር አለኝ፡" አለ፡ "ማሚ... " እና፡ የሰራቸውን ነገሮች መናገር ቀጠለ።

ከዚያም ከተመለሰ በኋላ፡ እንዲህ አለ። "ታዲያ፡ አባዬ፡ ይህ ኢየሱስ ያው ነውን? "

157 እውነቱን ተናገሩ። ሳንታ ክላውስ የሚባለው ሰው፡ ክሪስ ክሪንግል ወይም ቅዱስ ኒኮላስ የተባለ የካቶሊክ እምነት ተከታይ ነው፡ ከብዙ ዓመታት በፊት ለህጻናት መልካም እያደረገ ይዞር የነበረ ጀርመናዊ የካቶሊክ ቅዱስ ነው። እስከ አሁን ድረስ እንደ ወግ ተሸክመውታል። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የእግዚአብሔር ልጅ ነው። እሱ እውነተኛ ነው፡ እሱም ህያው ነው።

አሁን፡ አንድ ጥያቄ አለች፡ የመጨረሻ ናት፡ እጅግ በጣም...

158 አሁን ተመልከቱ። በዚህ ላይ ከእኔ ጋር ላትስማሙ ትችላላችሁ። አስታውሱ፡ ከእኔ ጋር ካልተስማማችሁ፡ በመልካም ወዳጅነት ይሁን። እሺ? እወዳችኋለሁ፡ እና እናንተን መጉዳት አ—አልፈልግም። እንደው እንዲሁ፡ ቅን መሆን እፈልጋለሁ። ካልቻልኩኝ... ለልጄ ውሸት ብናገር፡ ውሸታም ነኝ። አያችሁ? እውነቱን ልነግረው እፈልጋለሁ።

159 አሁን፡ ስለ ሳንታ ክላውስ እነግረዋለሁ፡ እንዲህ እላለሁ፡ "አዎን፡ እርግጥ ነው፡ ሳንታ ክላውስ ይህ ነው። የገና ምሽት ላይ አባትህን ጠብቀው።" አያችሁ? አዎን።

160 ታውቃላችሁ፡ በቀደም ለት እንትና ጋር ሄጄ ነበር፡ እና ልሙከራ ብዬ አንዲት ህጻን ልጅ ላይ ሞከርኩት። የተከፈለኝ ከትላንትና ወዲያ ይመስለኛል። ህንጻው ውስጥ ነበርኩ። እና እዚህ ኩዋከር ሜይድ አጠገብ፡ ቆመው ነበር። የቤት አስቤዛ ለመግዛት ወጥቼ ነበር። እና ሁለታችንም፡ እኔ እና ሚስቴ፡ አብረን ነበርን። እና ዕድሜዋ ከአሥራ ስምንት ወር ገደማ የማትበልጥ፡ ህጻን ሚጢጢ ልጅ ነበረች፡ እሷም በዚያ ቆማ፡ እየሄደች፡ ትዘምር ነበር፡ “ዲንጊል ቤልስ፡ ዲንጊል ቤልስ… ” እኔም አልኩ… ታውቃላችሁ፡ በዚያ በህጻን አቋሟ፡ በትንሹ ጋሪ ላይ ቆማለች።

አልኳትም፡ “የገና አባትን እየጠበቅሽ ነው? ”

እሷም “እሱ’ኮ አባቴ ነው፡ ሚስተር፡” አለችኝ።

እኔም “ትንሿ ልብሽ ትባረክ፡ የኔ ማር። ጥበበኛ ነሽ፡” አልኳት።

እንግዲህ፡ ወዳጆች ሆይ፡ ትክክለኛው ስቲከር ይህ ነው። እና በዚህ… እዘጋለሁ። ኦህ፡ ይህ—ጠጣር የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው፡ ቢሆንም ለሁሉም ሰው የሚገባ ስቲከር ነው። እና ለብዙ ዓመታት በውስጤ ይኖራል፥ እና በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ… እና አሁን ወደኋላ አካባቢ ቁጭ ብላ ያለችውን፡ ውድ ባለቤቴ፡ ዛሬ ከሰአት በኋላ ያንን ጥያቄ እንደተጠየቅኩ ስትሰማ፡ ጠየቀችኝ፡ “ቢሊ፡ ይሄን እንዴት ትመልሰዋለሁ? ” “እኔ ራሴ ሁሌ ግራ ያጋባኛል፡” አለችኝ። “በፍጹም ሊገባኝ አልቻለም፡” አለች። እና አለች…

እኔም እንዲህ አልኳት፡ “የኔ ውድ፡ ዛሬ ማታ ነይ። በእግዚአብሔር እርዳታ የተቻለኝን አደርጋለሁ።”

## 100. ወንድም ብራንሃም፡ እባክህ ዕብራውያን 6:4 እስከ 6 ድረስ አብራራ።

161 በእውነቱ አንድ ጊዜ… ተመልከቱ፡ አሁን እዚህ በእምነታችን፡ በጸጋችን ላይ፡ የአማኞች ደህንነት፡ ማለቴ፡ የቅዱሳን፡ የቅዱሳን ትእግስት፡ መመልከት አለባችሁ። ዕብራውያን 6ኛው ምዕራፍ፡ 4 እስከ 6።

አሁን፡ ልክ ይሄን… እንደጨረስኩ፡ ግልጽ እንደማደርግላችሁ እግዚአብሔር እንዲረዳኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ይቅርታ፡ ለዛሬ ማታ ያዘጋጀሁት መልእክት አ—አለኝ፥ ምናልባት ጠዋት ጉባኤው—ላይ ተመሳሳይ ነገር እሰብካለሁ። ከዚያ እሄዳለሁ።

162 አሁን፡ ይህን ትክክለኛ ስቲከር። እያችሁ? አሁን፡ ማየት አለባችሁ። አሁን አስታውሱ፡ እኛ እዚህ ቸርች ውስጥ የምናምነው እና የምናስተምረው እንዲህ ነው፡ የመጣ ሁሉ እና የጮኸ ሁሉ፡ በልሳን የሚናገር ሁሉ፡ ከሰባኪው ጋር የሚጨባበጥ ሁሉ፡ የዘላለም ሕይወት አገኘ ማለት አይደለም። እኛ የምናምነው ግን ዘለአለማዊ ህይወት ካለህ፡ እግዚ አብሔር የዘለአለም ህይወት ከሰጠህ፡ ለዘለአለም ከአንተ ጋር እንዳለ ነው። እያችሁ? ምክንያቱም ተመልከቱ፡ ከሌላችሁ፡ ኢየሱስ የሐሰት አስተማሪ ይሆናል። በቅዱስ ዮሐንስ 5፡24 ላይ፡ እንዲህ አለ፡ “ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፡ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ፡ ወደ ፍርድ ከቶ አይመጣም።” አሁን፡ ከእርሱ ጋር ተከራከሩ። “አብ የሰጠኝ ሁሉ… አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም። (ቅዱስ ቃሉን እየጠቀስኩ ነው።) የሚመጣውም

ሁሉ... አባቴ አስቀድሞ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም። አባቴም የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል። (አያችሁ? ) ወደ እኔ የሚመጣውንም ሁሉ፡ የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ (ቅዱስ ዮሐንስ 6)፡ በመጨረሻውም ቀንም አስነሣዋለሁ።" እነዚህ የእርሱ ቃላት ናቸው።

163 አሁን ተመልከቱ። ወደ ኤፌሶን ምዕራፍ 1 ልመለስ ከፈለግኩ፡ ጳውሎስ ይሰብካል... እንግዲህ፡ የቆሮንቶስ ሰዎች እያንዳንዳቸው፡ ልሳን እና መዝሙር ነበራቸው። በሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ያን ችግር እንዳልገጠመው አስተውሉ። ምንም ተናግሮ አያውቅም። በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን፡ እና በሮሜ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ ልሳኖችን ጠቅሶ ያውቃል'ዴ? አይ! ልክ እንደ ቆሮንቶስ ሰዎች ልሳኖች እና ሁሉም ነገር ነበራቸው፡ ነገር ግን በሥርዓት ይጠቀሙባቸው ነበር። የቆሮንቶስ ሰዎች ሰርኣት ማስያዝ አልቻሉም። አያችሁ? ጳውሎስ ግን ወደዚያ ወርዶ ቤተ ክርስቲያንን ሰርዓት አስያዘ።

አሁን፡ እሱ... ኦራል ሮበርትስ እንዳለው፡ አምናለሁ "እግዚአብሔር መልካም አምላክ ነው፡" አለ። ይህን አታምኑም?

164 እናንተም እንዲህ ትላላችሁ፡ "እሺ፡ ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ልሳን ያላቸው ጴንጤቆስጣሎችስ ታዲያ? " መንፈስ ቅዱስን ያላቸው ይመስለኛል። በእርግጠኝነት አላቸው። እሺ፡ ለምን? ተከታተሉ። መልካም አምላክ እንደሆነ ታምናላችሁ? ቶማስ አንድ ጊዜ እንዲህ አለ። "ታውቃላችሁ፡ ጌታን... "

ሌሎቹ ሁሉ አምነውታል። እንዲህ አሉ፡ "ኦህ፡ እሱ ህያው እንደሆነ እናውቃለን!"

"ኦህ፡" ቶማስም አለ፡ "አይ፡ አይ፡ እኔ አላምንም። የማምንበት ብቸኛው መንገድ፡ አንዳንድ ማስረጃዎች ሊኖሩኝ ይገባል። ጣቶቼን ከጎኑ እና በእጆቹ ውስጥ ባሉት የምስማሮች ምልክቶች ውስጥ ማስገባት አለብኝ።"

መልካም አምላክ ነው። እንዲህ አለው፡ "ቶማስ ሆይ፡ ና ቅረብ። ይኸውልህ።"

"ኦህ፡" "አሁን አምናለሁ፡" አለ ቶማስ።

165 እንዲህም አለው፡ "አዎን፡ ቶማስ ሆይ፡ ስላየኸኝ፡ ስለዳሰስከኝ፡ እጅህንም... እጅህንም ከጎኔ ስላኖርክ፡ አምነሃል። ነገር ግን ሳያዩ የሚያምኑ ዋጋቸው እንዴት ይበዛል።" መልካም አምላክ ነው። በእርግጥ የልባችሁን መሻት ይሰጣል። ብቻ እንመነው። ይህ ለ—ለ—ለሰይጣን የሞቱ ሰትሮክ ነው። ሰው እግዚአብሔርን እንደ ቃሉ ሲያምነው፡ ወንድሜ ሆይ፡ ሰይጣንን ዘወትር የሚገድለው ይህ ነው። ለሰይጣን ከባዱ ሞት፡ ሰው እግዚአብሔርን እንደ ቃሉ ሲያምነው ነው። አዎን፡ ወዳጄ። እንዳልኩት፡ "ሰው በዚህ ብቻ አይኖርም (ኢየሱስ፡ በቀደም ሌሊት)፡ ከሚወጣውን ቃል ሁሉ እንጂ.... "

166 አሁን፡ ይህን አስተውሉ። አሁን የመጀመሪያውን ጥቅስ ልጀምር፥

> **ስለዚህ የክርስቶስን የመጀመሪያው የሚናገረውን ትምህርት ትተን፡ ወደ ፍጻሜ እንለፍ፥...** (እንግዲህ፡ መጀመሪያ እንድታውቁልኝ የምፈልገው፡ ጳውሎስ እዚህ ከማን ጋር ነው የሚናገረው? ከዕብራውያን ጋር። "ዕብራውያን፡" ይላልና፡ ከላይ፡ የዕብራውያን መጽሐፍ ይላል። ልክ ነው? ኢየሱስን የተቃወሙት

አይሁዶች… ይህን—ተረድታችኋል አሁን? የሕጉን ጥላ የክርስቶስ ምሳሌ መሆኑን እያሳያቸው፡ ከአይሁድ ጋር እየተነጋገረ ነው። አሮጌዎቹ ነገሮች ሁሉ የአዲሱ ጥላዎች ናቸው። አሁን ተመልከቱ።)

… **የክርስቶስን የመጀምሪያውን የሚናገረው ትምህርት ትተን፡ ወደ ፍጻሜ እንለፍ፥…**

167 አሁን፡ ስለ ትምህርቶች ሲያናግራቸው ቆይቷል። እንቀጥል እና ፍጹም ስለሆኑ ነገሮች እንነጋገር። አሁን፡ እስከ ቤዛችሁ ቀን **ድረስ** በመንፈስ ቅዱስ ስትታተሙ በእግዚአብሔር ፍጹም ሆናችኋል። “ከእግዚአብሔር የተወለደ (እንደኛ ዮሐንስ) ኃጢአትን አያደርግም፡ የእግዚአብሔር ዘር በእርሱ ይኖራልና፡ ኃጢአት መሥራት አይችልምና።”

168 ተሞልቻለሁ ብሎ የሚያስብ ሳይሆን፡ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው፡ ከእግዚአብሔር መንፈስ የተወለደ ግን ኃጢአትን አያደርግም፡ የእግዚአብሔር ዘር በእርሱ ውስጥ ይኖራልና፡ ኃጢአትንም አይሠራም። እያችሁ? መጽሐፍ ቅዱስ ይላል? ስለዚህ ይኸው ነው። አንተ… ስራህ ምንድነው፡ አይደለም፡ ወይም፡ ዓለም ስለ አንተ ምን ያስባል አይደለም፡ እግዚአብሔር ምን ያስባል እንጂ። እያችሁ፡ እያችሁ? ሊሆን አይችልም… ከተማው ላይ በሰዓት አርባ ማይልስ ማሽከርከር ትችላለህ፡ የሚል በከተማው ከንቲባ የተጻፈ ትእዛዝ ይዤ፡ ፖሊሱ እንዴት ሊያስረኝ ይችላል? አይሆንም። በእግዚአብሔር ፊት የማያቋርጥ የደም መስዋዕት እየፈሰሰልኝ እንዴት ኃጢአት እሠራለሁ፡ ሊያየኝም አይችልም፥ በ—በእኔ እና በእግዚአብሔር… በመካከላችን፡ የደም ከለላ እያለ? ሞተናልና፡ ሕይወታችንም በክርስቶስ በእግዚአብሔር ተሰውሮአልና፡ በመንፈስ ቅዱስ ታትሟልና። በእግዚአብሔር ፊት ክፉውን ነገር እንዴት መስራት ይቻላችኋል? “የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብንሠራ (ዕብራውያን 10)፡ ከዚህ በኋላ ስለ ኃጢአት መስዋዕትነት የለም።” እዚህ ሆን ብሎ ኃጢአት መሥራት (እያችሁ? ) የማይቻል ነው።

169 አሁን፡ እንቀጥል እና እናንብብ። እሺ።

… **ወደ ፍጻሜ፥ መሠረትን ደግመን አንመሥርት—እርሱም ከሞተ ሥራ ንስሐና፡** በ… **እግዚአብሔር እምነት፡**

**ስለ ጥምቀቶችና፡… እጆችንም ስለ መጫን፡** ስለ **ሙታንም ትንሣኤ፡ ስለ… ዘላለም ፍርድም ትምህርት ነው።**

**እና… እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ ይሄን እናደርጋለን።**

(ከ 4 ኛ ቁጥር ለመጀመር የፈለጉበት ቦታ፡ ይኸውና።) **አንድ ጊዜ… ብርሃን የበራላቸውን፡ ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን፡ ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን፡**

**መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና፡ ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን፡**

**በኋላም የካዱትን፡ እንደገና ለንስሐ እነርሱን—ማደስ የማይቻል ነው፥ ለራሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታልና፡ ያዋርዱትማልና።**

170 አሁን፡ አሁን፡ ይህ ከምታነበው ሰፍራ፡ ይህ ይመስላል፡ ሰው መንፈስ ቅዱስ ከተቀበለ በኋላ፡ ባክ አርጎ ይጠፋል ይመስላል። ይሁን እንጂ ይህ ፈጽሞ የማይቻል ነው። አያችሁ? አይጠፋም። ከጠፋ ግን፡ ክርስቶስ ዋሽቷል። አያችሁ? እንዴ ብርሃን ለበራላቸው ፈጽሞ የማይቻል ነው። አሁን፡ እዚህ ተመልከቱ። ምን እያለ ነው? እሱ እየተናገረ ያለው ለእነዚያ የድንበር ላይ አይሁዳውያን ነው። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላውን ሰው በፍጹም አላለም፥ እሱ ያለው፡ “የእግዚአብሔርን ቃል ከቀመሰ።”

171 አሁን፡ እንድታዩት እና እንዲያመልጣችሁ፡ በምሳሌ ላሳያችሁ። አሁን፡ ለእነዚህ አይሁዶች እየጻፈ ነው። አንዳንዶቹ የድንበር አማኞች ናቸው። አያችሁ? እንዲህ ይላቸዋል፡ “አሁን፡ ስለ እነዚህን ሰራዎች ትተን ስለ ፍጽምና እንነጋገር።” እንዲህ ይላል፡ “አሁን፡ ስለ ጥምቀት፡ ስለ ሙታን ትንሳኤ፡ እጆችን ስለመጫን፡ እና ስለ ሌሎች ነገሮች እየተናገርን ነው፥ አሁን ግን እንቀጥልና ስለ ፍጽምና እንነጋገር። አሁን፡ ወደ መንፈስ ቅዱስ ስትመጡ እንነጋገራለን። በሰብሰባ ዙሪያ ላይ፡ ለረጅም ጊዜ ተንጠልጥላችሁ ቆይታችኋል… ”

172 እነዚያን ሰዎችም አይታችኋል። ዙርያ ላይ ያንዣብባሉ እንጂ፥ አይገቡም አይወጡም። መንፈስ ቅዱስ ደስ ይላቸዋል። ዙርያው ላይ ይመጣሉ። እና ምናልባት መንፈስ ቅዱስ የሆነ ነገር ሲያደርግ፡ ሰዎች፡ ተነሥተው ይጮኻሉ፡ ስለዚህ ወለሉ ላይ ዘለው ይንከባለላሉ፡ እነሱ ራሳቸው ግን ፈጽመው ሊቀበሉት አይፈልጉም። በጭራሽ፡ አይፈልጉም! አያችሁ? እንዲህም ይላሉ፡ “ኦህ፡ አዎን፡ ይህ’ኮ ጥሩ ነገር ነው። ኦህ፡ ስለዚህ ጉዳይ እኔ አላውቅም።” አያችሁ፡ አያችሁ፡ አያችሁ? የድንበር አማኞች። እስኪቀምሱት ድረስ እጅግ ቢቀርቡትም፡ አይቀበሉትም። አያችሁ? እና፡ በኋላ ሙሉ በሙሉ ርቀው እስኪጠፉ ድረስ በዙርያው ሲያንዣብቡ ይቆያሉ። በዚህ ተበርናክል ተመሳሳይ ነገር ያደረጉ፡ የብዙዎችን ስም መጥራት እችላለሁ። እንደገና ወድቀው፡ ወደ ንስሃ ራሳቸውን ለማደስ፡ ንስሃ መግባት አይችሉም። መንፈሱን አሳዝነው ከራሳቸው እንዲርቅ ያደርጉታል። እጅግ ቅርቡ የነበሩ ሰዎች…

173 እስኪ፡ ከእኔ ጋር ይህን ክፈቱ (አሁን፡ ጊዜ እንደሌላችሁ፡ አውቃለሁ) ነገር ግን ወደ ኦሪት ዘዳግም 1ኛው ምዕራፍ ሄዳችሁ ካነበባችሁ፡ ተመሳሳይ ነገር ታገኛለህ። ኦሪት ዘዳግም 1ኛው ምዕራፍ፡ ምልክት አድርጉበት። እና፡ ከ19ኛው ቁጥር ጀምራችሁ እስከ 26ኛው ድረስ አንብቡ። ዘዳግም… ታገኙታላችሁ… አሁን ተመልከቱ። መላው እስራኤል… ሰዎች ወደ ቃዴስ-በርኔ የደረሱበት ጊዜ ነው። ኦህ፡ አንድ ነገር እየሁ! ይህን ተበርናክል፡ ይህ የጴንጤቆስጤ ዓለም አሁን ቃዴስ-በርኔ ይገኛል። ትክክል ነው፡ ወንድም ኔቪል። በቃዴስ-በርኔ፡ የዓለም ፍርድ ወንበር እንገኛለን (የፍርድ ወንበር ያ ነበረ)።

174 ሰላዮችም ሄዱ። ኢያሱ “አሁን ሰላዮችን፡ ላክሁ፡” አለ፡ ወይም ሙሴ፡ ማለቴ ነው፡ “እነሆ ከየነገዶቻችሁም፡ አንድ አንድ ሰው፡ አስራ ሁለት፡ ሰላዮችን ልኬአለሁ። ምድሪቱን እንዲሰልሉ እና ሪፖርት እንዲያመጡ ላክኋቸው።” ልክ ነው?

በተመለሱ ጊዜም፡ ከአሥራ ሁለቱ ዘጠኙ፡ “ኦህ፡ ጥሩ ምድር ናት፡ ግን ኦህ፡ ሞሕረት ያድርግልን እንጂ፡ አንወርሳትም አሉ። ኦህ፡ ማይ! አሞራውያን በዚያ አሉ፡ እኛም በፊታቸው እንደ አንበጣ እንመስላለን። የታጠቁ ሰዎች ናቸው።

ግንቦቻቸው ታላቅ ነው። ኦህ፡ ከባድ ነው… ምነው፡ አንተ ወደዚህ ባታወጣን በግብፅ ወደዚያ በሞትን ይሻለን ነበር።”

175 ኢያሱ እና ካሌብ ግን፡ ወጥተው ማሕበሩን ዝም አሰባሏቸው፥ “ልንወርሳት እንችላለን፡” አሉ። አዎን፡ ወዳጄ! ይኸው ነው። አሁን ተመልከቱ። ምን ሆነ? ካሌብና ኢያሱ እግዚአብሔር የተሰፋውን ቃል እንደ ሰጠ ያውቃሉ፦ “ምን ያህል ትልቅ እንደሆኑ፡ እንቅፋቶቹ ምን ያህል እንደሆኑ፡ ምን ያህል ከፍ እንደሚሉ፡ ምን ያህል ታላቅ እንደሆኑ አይገደኝም፡ ከዚህ ጋር በምንም አይገናኝም። እግዚአብሔር ተናግሯልና፡ እናሸንፋታለን።” እና ከዚያ ከሁለት ሚሊዮን ተኩል ውስጥ፡ ወደ ምድሪቱ የተሻገሩት፡ ሁለት ሰዎች ብቻ መሆናቸውን ታውቃላችሁ? ምክንያቱም እግዚአብሔር በተናገረው እውነት ላይ እምነት ነበራቸው። አሜን!

176 አሁንም፡ ተበርናክሏ፡ በቃዴስ-በርኔ ላይ ቆማለች። ተመልከቷቸው፡ ሰዎቹ ከምድሪቱ ፍሬ ወይኑን እስኪቀምሱ ድረስ በጣም ቅርብ ነበሩ። ወይኑን በልተዋልና። ካሌብና ሌሎቹ ተሻግረው የወይኑን ፍሬ ሲያመጡ፡ እነዚያ ሰዎችም እየሳቡ በልተዋል። “ኦህ፡ መልካም ናቸው፡ ነገር ግን አንችላቸውም።” “የእግዚአብሔርን በጎ ሥራ የቀመሱ፡ መንፈስ ቅዱስን የቀመሱ፡ ቸርነቱን አይተዋል፡ ቀምሰውታል፡ የእግዚአብሔርን ቃል ቀምሰዋል… ” አይታችሁታል? ከሰዎቹ መካከል፡ አንዳቸውም እንዲሻገሩ አልተፈቀደላቸውም። በገዛ ምድራቸው፡ በምድረ በዳው ጠፉ። በጭራሽ አልተሻገሩም፡ ያንን እስከ መቅመስ ድረስ ግን ተቃርበው ነበር፡ ለመቀበል ግን በቂ ጸጋ እና እምነት አልነበራቸውም። ያ ነው።

177 አሁን። አሁን ይህን ደብዳቤ ለጻፈውን ውድ ሰው። የሚቀጥለውን ቁጥር ብቻ እናንብብ። አንድ ደቂቃ ተከታተሉኝ። ጳውሎስን ተመልከቱት። አሁን 7ኛውን እናንብብ፦

> **ብዙ ጊዜ በእርሰዋ ላይ የሚወርደውን ዝናብ… የምትጠጣ መሬት፡ ለሚያርሱአትም ደግሞ** የምትጠቅምን **አትክልት የምታበቅል፡ ከእግዚአብሔር** በረከትን **ታገኛለችና፥**
>
> **እሾህና ኩርንችትን ግን ብታወጣ፡ የተጣለች ናት ለመረገምም ትቀርባለች፥ መጨረሻዋም መቃጠል ነው።**

178 አሁን፡ ምን እንደሚል ተመልከቱ? አሁን ተመልከቱ። እዚህ ላይ ጥያቄ ነበር፥ እና፡ ከዚያ በኋላ እንዘጋለን… ይህ ነገር ለብዙ ዘመናት ሲያሰጨንቀኝ የኖረ ነገር ነው።

179 አንድ ጊዜ በሚሻዋካ፡ ኢንዲያና ሰዎች በልሳኖች በሚናገሩበት ጉባኤ ላይ ሄጄ ነበር። አሁን፡ ከሕዝቤ ፊት ነኝ። ስለ እነዚያ ሰዎች ሰምታችኋል… የህይወት ታሪኬን ሰናገር ሰምታችሁኛል፡ “እዚህ ጋር አለ። እዚህ ጋር አለ፡” በማለት ሰለተናገረው ጥቁር ሰው ሰምታችኋል። ይህን፡ ነግሬአችኋለሁና።

180 ብቻ ዋናው ነገሩ፥ ሁለት ሰዎችን አይቼ ነበር። ሁለቱም… አንደኛው መልእክት ያመጣል፡ ሌላኛው ይተረጉመው ነበር። አንደኛው መልእክት ያመጣል፡ ሌላኛው ይተረጉመው ነበር። እና ወንድሜ ሆይ፡ ትክክል ነበሩ። በዚያም… እንዲህ አሰብሁ፡ “ይገርማል! እንዲህ አይነቱ ነገር አይቼ አላውቅም።” “በመላእክት ጉባኤ ውስጥ ገባሁ፡” አልኩ። እንዲህ አይነት ነገር፡ አይቼ አላውቅም ብዬ አሰብኩ… አንዱ ይናገር ነበር፡ ሌላኛው ደግሞ…

181 እና እንደ ተራ ሰባኪ፡ በዚያ ቁጭ በዬ ነበር፡ እ... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]... በሆነ ሰዓት ላይ ሁለቱም እጆቻቸውን ጨበጥኳቸው። በህይወቴ እንደዚህ አይነት ሰዎች አይቼ አላውቅም። መልእክት ይናገሩ ነበር፡ ሌላኛው ይተረጉመዋል። እና ኧረ፡ ኧረ! ድንቅ ነበር! አንዱ ይናገራል፡ ሌላኛው ይተረጉመዋል። ሁለቱም... እና እጃቸውን ወደ ላይ ሲያነሱ ነጭነት ይሆናሉ። እና እንዲህ አሰብኩ፡ "ኦህ፡ ኧረ፡ ኧረ! ህይወቴን በሙሉ የት ነበርኩ? ለካ ነገሩ ይሄ ነው!" እኔም "ኧረ፡ ፔንጤቆስጤዎች ትክክል ናቸው፡" አልኩ። ይህ በትክክል እውነት ነው።

182 ከዚያም ብዙ አይቼ አላውቅም ግን እዚህ አካባቢ ያሉትን፡ እነ... ምናልባት ተልዕኮ የነበራቸው ሁለት ሴቶችን አይቻለሁ። እነሱም ይንጫጫሉ፡ አንደኛዋ ሌላኛዋን "የመንጋ አውራ ዶሮ፡" ትላታለች፡ እና፡ ልክ እንደዚያ አይነት፡ ናቸው፡ እርስ በእርሳቸው ትጨቃጨቃሉ። አሁን ሴቶቹን መናቄ ወይም ሌላ ነገር አይደለም፡ ይሁን እንጂ... ዝቅተኛ—የሚባል ደረጃ ነው። ከእናንተ... ወንድም ግራሃም፡ ታስታውሱታላችሁ። ያኔ ትንሽ ልጆች ነበራችሁ። ያን ጊዜም፡ እንደዚያ ነበር።

እና ሰማኋቸው፡ እና እንዲህ አሰብኩ፡ "ኦህ፡ ማይ፡ ከመላእክት ጋራ ተገናኘሁ።"

183 አንድ ቀን በቤቱ ጥግ እየዞርኩ ሳለሁ፡ በሁለተኛው ቀን አካባቢ፡ ከሰውየው አንዱን አገኘሁት። ሰላም አልኩት፡ "ጤና ይስጥልኝ፡ ወዳጄ?"

ሰላም አለኝ፡ "ጤና ይስጥልኝ?" እንዲህም አለኝ፡ "ሰምህ... ማን ነበር?"

"ብራንሃም፡" እባላለሁ አልኩት።

እንዲህም አለኝ፡ "ከየት ነህ? ከእዚህ ነህ?"

"አይ፡ ከጄፈርሰንቪል ነኝ፡" አልኩት።

እንዲህ አለኝ፡ "አይ፡ ጥሩ ነው። ጴንጤ ነህ?"

"አይ፡ ጌታዬ፡ አይደለሁም፡" አልኩት። እንዲህ አልኩት፡ "የጴንጤቆስጤ የመንፈስ ቅዱስ አቀባበል አልቀበለውም፡" አልኩት፡ "ቢሆንም፡" "ለመማር መጥቻለሁ፡" አልኩት።

184 "አይ፡ በጣም ደስ የሚል ነገር ነው፡" አለኝ። እያነጋገርኩት ሳለሁ፡ መንፈሱን ያዝኩት (ጉድጓዱ አጠገብ እንደነበረች ሴት)፡ እና ትክክለኛ ክርስቲያን ነበረ። ወንድሜ፡ ማለቴ በትክክል የታነጸ ሰው ነው። መልካም ሰው ነው። አሁን፡ ሁላችሁም... በስብሰባዎቼ ውስጥ የነበራችሁ እነዚህ ነገሮች ሲሆኑ ያያችሁ አላችሁ? አያችሁት? ሰውዬው በጣም መልካም ሰው ነው። ስለዚህ፡ እንዲህ—አሰብኩ፡ "አቤት! እንዴት ያለ፡ ግሩም ነው!"

185 ያን ጊዜ ወደ ማታ፡ ከሰዓት አካባቢ ላይ፡ ሌላኛው ሰውዬ ደግሞ አገኘሁት። እንዲህም አልኩት፡ "ጤና ይስጥልኝ፡ ወዳጄ?"

እሱም አለኝ፡ "ጤና ይስጥልኝ? ማን ልበል?" እኔም ነገርኩት። እርሱም አለኝ፡ "እ... ጴ—ጴንጤ ነህ?"

“አይ፡ ወዳጄ፡ ጴንጤ አይደለሁም፡ አይመስለኝም፡” አልኩት። “ለመማር ብቻ ነው የመጣሁት፡” አልኩት።

እኔም፡ እርሱም፡ “መንፈስ ቅዱስ ተሞልተሃል፡” ብሎ ጠየቀኝ?

“እንጃ አ—አላውቅም፡” አልኩት። “እናንተ ዘንድ ባለው መስረት ከሆነ፡ የተሞላሁ አይመስለኝም፡” አልኩት።

እርሱም ጠየቀኝ፡ “በልሳኖች ተናግረህ ታውቃለህ? ”

እኔም፡ “አላውቅም፡ ወዳጄ!”

“እንግዲያውስ አልተሞኣልህም፡” አለኝ።

186 እኔም “አዎን፡ ሳ—ሳይሆን አይቀርም፡” አልኩት። እንዲህ አልኩት፡ “አላውቅም። ለሁለት ዓመት፡ ገደማ ሰብኬአለሁ፡” “ስለዚህ ነገር ብዙም አላውቅም፡” አልኩት። እንጃ “ምናልባት አላውቅም ይሆናል፡” አልኩት። “ሊገባኝ አልቻለም… ” አልኩት። ለምን መሰላችሁ፡ እሱን ለመያዝ እየሞከርኩ ነው (አያችሁ? )፡ መንፈሱን ለመያዝ። በያዝኩት ጊዜም፡ ግብዝ አይቻለሁ ካልኩኝ እሱን ነበር፡ ከግብዞች አንዱ ነው። ሚስቱ ጥቁር-ጸጉር ያላት ሰትሆን፥ ወርቃማ-ጸጉር ካላት ሴት ጋር ይኖር ነበር፡ ከሷም ሁለት ልጆች ወልዷል፥ እና በልሳኖች በመናገር፡ በተቻለ መጠን ፍጹም በሆነ መልኩ መተርጎም ይችላል። እኔም እንዲህ አልኩኝ፡ “አሁንስ፡ ጌታ ሆይ፡ ምን ውስጥ ገባሁ? ” ከመላእክት፡ ወደ ምን እንደገባሁ እንጃ። እንዲህ አልኩኝ፡ “እ—እ—እኔ ወግ አጥባቂ ነኝ፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ መሆን አለበት። ትክክል መሆን አለበት። ጌታ ሆይ፡ የሆነ ቦታ የሆነ ስህተት አለ። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ”

187 በዚያ ማታም ወደ ሰብሰባው ሄድኩ፡ እና መንፈሱ ይወርዳል፥ እና ወንድሞች ሆይ፡ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ፡ በትክክል ይሰማችኋል። አዎን፡ ወዳጄ! ባይሆን፡ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ከመንፈሴ ጋር ተመዝግቧል። እና ገና ወጣት ሰባኪ ነበርኩ፡ እና ሰለ መንፈስ መለየት፡ እንዴት እንደሆነ አላውቅም ነበር። ይሁን እንጂ በዚያ ቁጭ ብዬ ነበር። እና ያዳነኝ አምላክ ራሱ አውቀዋለሁና፡ ያንኑ ተመሳሳይ ሰሜት ነበር… በዚያ ሕንፃ ውስጥ በጣም አስደናቂ ሰሜት ነበር፡ በታሪያው ላይ እየተንሳፈፍኩ እንደነበረ ይሰማኝ ነበር። አሰብኩት…

188 አንሺ አምስት መቶ ያክሉ ነበር። አሰብኩት፡ “ማይ፡ ኦህ ማይ!” ሁለት ወይም ሶስት መንጎች አንድ ላይ ነበሩ። አሰብኩት፡ “ማይ! እንዴት ሊሆን ይችላል፡ አልኩ? አሁን፡ ያ ታላቅ መንፈስ በዚህ ሕንፃ ውስጥ እንደዚያ ይወርዳል፥ በዚያም፡ ይሄኛው ወደዚያ ሲንቀሳቀስ አየሁት፡ ሰዎቹ በልሳን ይናገራሉ፡ ይተረጉሙታል፡ መልእክቱን በትክክል ያስተላልፋሉ— ከእነርሱም አንዱ ግብዝ ሁለተኛውም እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው ነው።” እኔም አሰብኩ፡ “አሁን፡ ግራ ተጋባሁ። ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም።”

189 እና፡ ወዲያውኑ ከዚያ በኋላ፡ ጥሩ ጓደኛዬ፡ ወንድም ዴቪስ (ታውቁታላችሁ)፡ ፑፔት ሆነሃል አለኝ። ያም የሴት አሻንጉሊት፡ ማለት ነው። ያን ጊዜ፡ አላገባሁም ነበር፡ እናም… እኔን ይተርበኛል፡ እና እንዲህ እያልን ቀጠልን፡ እንዲሁ በመልካም መንገድ ይቀልድብኝ ነበር።

190 ያን ጊዜ አነስተኛ ቦታ ነበረችን… እና እናትህ ኣና እኛ ሁላችንም በተለያዩ ቦታዎች ጉባኤ እናደርግ ነበር። ያን ጊዜ—ተበርናክሉ አልተጀመረም ነበር፡ እና በልዩ ልዩ ቦታዎች አነስተኛ ጉባኤዎች እናደርግ ነበር። በመጨረሻም አንድ ቀን፡ ከብዙ አመታት በኋላ፡ ተበርናክሉ ከተሰራ በኋላ፡ ለመጸለይ ወደ ግሪን ሚል ወደ ዋሻዬ ወጣሁ፡ ምክንያቱም ወንድም ዴቪስ በ—በ—በጽሑፎቹ ላይ ስለእኔ እጅግ አስቀቂ ነገሮች ተናግሮ ነበርና። እኔ እወደዋለሁ። ምንም ነገር እንዲሆን አልፈልግም፡ እና እኔም—ለእርሱ ለመጸለይ ወደዚያ ወጣሁ። ወደዚያም ወጥቼ፡ ወደ ዋሻው ገባሁ። እዚያም ሁለት ቀን ያህል ቆየሁ። እኔም አልኩ፡ "ጌታ ሆይ፡ ይቅር በለው። እ—እንደዚያ ማለቱ አይደለም—ለማለት ፈልጎ አይደለም።" እና አንድ ነገር አሰብኩ፡ "ታውቃላችሁ… " አንድ ቃል ወደ ልቤ ገባ።

191 እኔም ወጣሁ። እና አንድ ግንድ ነበረ (ያቺ ግንዱ አሁንም በዚያ እንደተጋደመ አለ፡ በቅርብ ጊዜ በዚያ ነበርኩ) ከተራራው ወርዶ ከጅረቱ ዙሪያ በሚመጣ ትንሽ መንገድ ላይ ተኝተዋል። እና እግሮቼን ግንዱ ላይ ሰቅዬ፡ ወደ ተራሮቹ ወደ ኋላ—እየተመለከትኩ ነበር፡ መጽሀፍ ቅዱሴንም እንዲህ አጋድሜው ነበር። እያሰብኩ ነበር፡ "ታውቃላችሁ… " ስለ አንድ ቃል አሰብ ነበር፥ "እንጥረኛው፡ እጅግ ከፋብኝ፡ እያለ ይናገራል።" ታውቃላችሁ… "እስኪ እሱን ላንብበው፡" ብዬ አሰብኩ። መጽሐፍ ቅዱሴን ከፈትኩ፡ እና እንዲህ አልኩ፡ "እሺ… " ፊቴን ጠራረግኩ፡ ነፋሱም ነፈሰና ዕብራውያን 6 ከፈተ። "አይ፡" "እዚያ ላይ አይደለም፡" አልኩኝ። እንደዚህ መልሼ አሰቀመጥኩት። ንፋሱም ነፈሰ እንደገናም ከፈተው። እኔም "እንዴ፡ ነፋሱ እንዲህ ከፈተው፡ ያ እንግዳ ነገር ነው፡" አልኩኝ። ስለዚህ "እንግዲያውስ፡ ማንበብ አለብኝ፡" ብዬ አሰብኩ። እና እንዲህ ይላል፦

> **አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን፡… ሰማያዊውንም ሰጦታ** የቀመሱትን **ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን፡ መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና፡ ሊመጣ** ያለውን **የዓለም ኃይል… የቀመሱትን።**

"እንጃ፡ ይህ ምንም ሊገባኝ አልቻለም፡" ብዬ አሰብኩ። ቀሪው የምዕራፉ ክፍል፡ ኣስከ ታች ድረስ አነበብኩት። ምንም አላገኘሁበትም። "አይ፡ እ—እ እንዲሁ ዝም ብሎ ነው፡" አልኩኝ። እና—እንደዚህ አየሁት እና፡ ወደ ኋላ ተመለስኩበት። እኔም የሆነ ነገር ገባኝ፡ እንዲህ አልኩኝ፡ "እሺ፡ ይህ ምን ይሆን? " ማንበቤን ቀጠልኩ፡ እያነበብኩት፡ እያነበብኩትም ነበር፡ "በቃ፡ ሊገባኝ አልቻለም፡" አልኩ። እንዲሁ ቀጠልኩና… እስከ ታች ድረስ ወረድኩ፦

> **… አንድ ጊዜ ብርሃን የበራ**ላቸውን፡**…**

እና እንዲህ ወደሚልበት ቦታ ደረሰ፦

> **ብዙ ጊዜ በእርሰዋ ላይ የሚወርደውን ዝናብ… የምትጠጣ መሬት፡ ለሚያርሱአትም ደግሞ የምትጠቅምን** አትክልት የምታበቅል፡ **ከእግዚአብሔር** በረከትን **ታገኛለችና፥**
>
> **እሾህና ኵርንችትን ግን ብታወጣ የተጣለች ናት፡ ለመረገምም… ትቀርባለች፥** ፍርዷም **መቃጠል ነው።**

192 “ምን ማለት እንደሆነ ይገርማል? ” አልኩኝ፡ ብቻ... አሁንም፡ ስለ ሌላ ስለ ምንም ነገር እያሰብኩ አልነበረም። እኔ የማስበው ያ ብቻ ነበር። በዚያ ቁጭ ብዬ፡ ጌታ ስለ ወንድም ዴቪስ እና ስለ ሌሎቹ ራእይ እንዲያሳየኝ እያሰብኩ ነበር። እና ቁጭ ብዬ ሳለሁ፥ ተመለከትኩ፥ እና ከፊት ለፊቴ ባለው ባዶ ቦታ ላይ የሆነ ነገር ሲወጣ አየሁ። የወጣውም ዓለም ነበር። ሙሉ ለሙሉ ታርሶ ያበቃለት፡ የተሰባበረ ይመስል ነበር። እና አንድ ሰው ከፊት ለፊቱ ዘር የሞላበት ት—ት—ትልቅ ነገር ይዞ ወጣ፡ እርሱም ሲሄድ ዘሩን በምድር ላይ ሁሉ እየጣለ ነበር። በምድር ሁሉ ዙርያ ተመላለሰ፡ ከዚያ በኋላ ከዓይኔ ተሰወረ። እሱ ከዓይኔ እንደተሰወረ፡ እነሆ እጅግ-ተንኮለኛ መሳይ፡ ጥቁር ልብስ የለበሰ ሰው መጣ፡ እየሄደም፡ እንደዚህ ይዞር ነበር፡ **ዊው**፡ **ዊው**፡ ክፉ ዘሮችን ይዘራ ነበር፡ **ዊው**፡ **ዊው**። እኔም ተመለከትኩት፡ እና ምድር ስትዞር...

193 ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ስንዴው ወጣ። ስንዴውም በወጣ ጊዜ፡ በዚያው ኩርንችቶች፡ እና አሜኬላዎች፡ እሾሆች፡ ክፉ አረሞች ወጡ፡ ሌሎች ብዙ ነገሮች ወጡ፡ የወተት አረም፡ እና በስንዴ መካከል የሚበቅሉ ነገሮች ሁሉ ወጡ። እና ሁሉም አብረው እያደጉ ነበር። ከዚያ በኋላ፡ እጅግ ክፉ እና ትክክለኛ ድርቅ መጣ፡ ትናንሾቹ ስንዴዎች አንገታቸውን እንዲህ አቀረቀሩ፡ ኩርንችቶች፡ እና አሜኬላዎች፡ እሾሆቹም፡ አንገታቸውን አቀረቀሩ። እያንዳንዱ አረም፡ **ቁና**፡ **ቁና**፡ **ቁና**፡ **ቁና**፡ ይተነፍሱ ነበር። ትንፋሻቸው ይሰማችኋል። ዝናብ፡ ዝናብ እያሉ ይጣሩ ነበር።

194 እና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፡ አንድ ትልቅ ደመና መጣ፡ ዝናቡም በኃይል ፈሰሰ። በዚያ ላይ በወረደ ጊዜም፡ ስንዴው እየዘለለ መደሰት ጀመረ፡ “ክብር! ሃሌ ሉያ! ጌታ ይመስገን!” ትንሹ መጥፎ አረምም ወደ ላይ ዘለለ እና ተደሰተ፡ “ክብር! ጌታ ይመስገን! ሃሌ ሉያ!” እሾሆቹ እና ሌሎቹ ሁሉ፡ ማሳው ላይ እየተደሰቱ፡ ዘለሉ፡ “ክብር! ሃሌ ሉያ! ጌታ ይመስገን!”

እንግዲህ፡ “ሊገባኝ አልቻለም፡” አልኩኝ።

195 ራእዩም ተወሰደ፥ በዚያውም እንደገና ወደ ኋላዬ ተኛሁ፥ “ለመረገም የቀረበ ኩርንችት።” ከዚያ በኋላ ገባኝ። ኢየሱስም “ዝናብ በጻድቃንና በኃጢአተኛው ላይ ይወርዳል፡” ብሏል። አንድ ሰው፡ እንደ ሌሎቹ በትክክለኛው መንፈስ ቅዱስ እያገለገለ፡ በልሳን እየተናገረ እና በጉባኤ መካከል ቁጭ ብሎ ከእግዚአብሔር መንግስት የራቀ ሊሆን ይችላል። ይህ በትክክል እውነት ነው። ኢየሱስ፦ “በዚያ ቀን ብዙዎች ቆመው፡ ‘ጌታ ሆይ፡ በስምህ አጋንንትን አላወጣሁምን? በስምህ ትንቢት አልተናገርሁምን (አልሰበክሁምን)? በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግሁምን ይሉኛል? ’” ኢየሱስም፦ “እናንተ ዓመፀኞች፡ ከእኔ ራቁ፡ ከቶ አላውቃችሁም ይላቸዋል።” ይሄኛውስ?

196 ትክክለኛውን ትርጉሙ ይህ ነው። አያችሁ? ከሰማይ የወረደውን መልካሙን ዝናብ ቀምሰውታል። ከመጀመሪያቸውም፡ የተሳሳቱ ነበሩ። ከመጀመሪያው ግባቸው ልክ አይደለም፥ የልባቸው አሳብ ቅን አይደለም። ይሄን፡ እናንተም ታውቁታላችሁ። እ... እንደምታውቁት፡ በመኸር ጊዜ እንዲህ አሉት፡ “ሄደን ሁሉንም እንንቀላቸውን? ”

197 እንዲህም አለ፡ “አብረው ይደጉ፡ በዚያም ቀን እነዚህ እሾህና አሜከላዎች በአንድ ላይ ይቃጠላሉ፡ ስንዴውም ወደ ጎተራው ይገባል።” አሁን፡ የትኛው

እሾህ እንደሆነ፡ የትኛው አሜከላ፡ ወይም የትኛው ስንዴ እንደሆነ እንዴት ታውቃላችሁ? "ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።" አያችሁ፡ ወንድም፡ እህቶቼ፡ መልካም ዛፍ መጥፎ ፍሬ ማፍራት አይችልም። ምንም ቢሆን፡ በሆነ መንገድ ላይ፡ ትገናኛላችሁ። ስለዚህ፡ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት በመፈለግ... ይሄን በጻፈው ሰው ደስተኛ ነኝ። አያችሁ?

198 አሁን፡ ያኔም የድንበር አማኞች፡ አብረዋቸው ነበሩ። ከግርዛታቸው ጋር አብረው ተገርዘው ነበር። እግዚአብሔር ተስፋ ወደ ገባት ምድር፡ እስከ ዳርቻዋ ድረስ ደረሱ። ብዙ ሰዎች ዳርቻዋ ድረስ ይጓዛሉ። እስከ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ድረስ ይሄዳል ያኔ ይቃወመዋል። እራሱን አሳልፎ መስጠት አይፈልግም። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እስከ መጠመቅ ድረስ ወደ ቃሉ ይቀርባል፡ በኋላ ግን ጀርባውን ይሰጣል፡ ከዚያ በኋላ ይንቀዋልና አያየውም።

199 በመጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ውስጥ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቀ አንድም ሰው የለም፡ አንዲት ቃል የለችም። የጀመረችው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ናት፡ በሉተር ቀጠለ፡ ወደ ዌስሊ ወረደ፡ እና እዚህ ድረስ አለፈ። በትክክል። መጽሐፍ ቅዱሳዊው ሥርዓት ግን በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። ሐዋርያዊ ጥምቀት ያ ነው። ያንን ተቀብላችሁ በሐይማኖት ተቋም ውስጥ መኖር አትችሉም። ትክክል ነው።

200 አሁን፡ እነዚህ ነገሮች ይታዩአችኋል? የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ የመንፈስ ስጦታዎች፡ እግዚአብሔር የሚያወጣቸው ነገሮች... የመንፈስ ፍሬ ፍቅር፡ ደስታ፡ ትዕግስት ነው (ኦህ፡ እናንተም እንዲህ ትላላችሁ፡ "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ እግዚአብሔር ይባርክህ፡ እኔ ታጋሽ ነኝ።" ይመስላል። በቅርብ ጊዜ ወደ ኦሃዮ ወጥቼ ነበር፡ እና አንድ ሰው ጠየቀኝ፡ ደብዳቤ ጽፎ ሰዎችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዳጠመቅሁ ጠየቀኝ። አንድም ቃል ትንፍሽ አላልኩም። ለማንኛውም ማወቃቸው አልቀረም፡ አስራ ሰድስት ተባባሪ አገልጋዮች መጡ። ትዕግስት ይህ ነው አይደል!)—ትዕግስት፡ መልካምነት፡ የዋህነት፡ ገርነት፡ ትዕግስት፡ እና መንፈስ ቅዱስ። አያችሁ?

201 ወንድም፡ እህቶች ሆይ፡ አሁን—ያለነው በቃዴስ-በርኔ ላይ ነን። አሁን ቅምሻ ላይ ናችሁ። ትናንት ማታ መንፈስ ቅዱስ በላያችን ላይ ወረደ፡ እንደሚነጥቅ ንፋስ፡ ወደ እኛ ገባ። በብዙዎቻችሁ ላይ አርፏል። ዛሬ አገልጋዮች እዚህም እዚያም ቤቶችን እየጎበኙ፡ እጅን በመጫን መንፈስ ቅዱስን ለሚፈልጉ እየጸለዩላቸው ናቸው። በሌላ ነገር አትተኩት። አንዳንድ ጩኸቶች አትቀበሉ። ስሜታዊነትን አትቀበሉ። እግዚአብሔር እስኪቀርጻችሁ አዲስ ፍጥረት እስኪያደርጋችሁ፡ አዲስ ሰው እስኪያደርጋችሁ ድረስ ጠብቁት። አሁን ቅምሻ ላይ ናችሁ፡ እየቀመሳችሁ ናችሁ፡ እርግቧ ወደ ማዕዱ ትምራችሁ፡ በጉ—እና እርግቧ አብረው ተቀምጠው፡ ለዘላለምም በእግዚአብሔር ቃል ላይ ይመገቡ። ሰማይና ምድር በሚያልፉ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር ቃል ይኖራልና። እውነት ነው።

202 እባካችሁ አክራሪ ነው ብላችሁ አታስቡኝ። ከሆንኩባችሁ፡ ለመሆን ፈልጌ አይደለሁም። ባለኝ እውቀት፡ በተሻለ መልኩ፥ ለ—ለጥያቄዎቻችሁ መልስ እንደሰጠሁ ተስፋ አደርጋለሁ።

203 ስለዚህ፡ በዕብራውያን 6 ላይ፡ ብታዩት፡ ጳውሎስ ለዕብራውያን ሲናገር፡ “እንግዲህ፡ እስከዚያ ድረስ ከእናንተ ጋር አብረን እንኳዛለን።” ሁሉም ይመጣሉ። አያችሁ? አላቸውም፡ “አሁን፡ እናንተ... ” ማለት መጥተው የቀመሱትን ነው።

204 በአጋጣሚ ወደ ህንጻው መለስ ብዬ ስመለከት ነበር። የሕያው አምላክን ማስረጃ ለእናንተ ላሳያችሁ ነው። ይህን ሰው እንዲጋለጥ እንዳላደርገው ተስፋ አደርጋለሁ። በቅርብ ጊዜ ከአንድ ጉባኤ ወጥቼ፡ ወደዚህ መጣሁና፡ ስለ አንድ መልካም ወዳጄ ማስታወቂያ ነግሬአችሁ ነበር፡ የግል ጓደኛዬ፡ የአደን አጋሬ፡ ለእኔ ጥሩ የሆነ ሰው፡ በእኔ ቤተክርስቲያን የኖረ ሰው ነው፡ ወንድሜ የነበረ ሰው፥ ባስቲ ብዬ እጠራው ነበር። ሰሙ ኤቨረት ሮጀርስ ይባላል፥ መኖሪያው ሚልታውን ነበር። እዚህ መጥቼ ማስታወቂያውን ስናገር ስንቶች ታስታውሳላችሁ? እዚህ ሆስፒታል ውስጥ ተኝቶ ነበር፥ ዶክተሮቹ ኦፕራሲዮን አድርገውበት፡ ከፍተውታል፡ እና በካንሰር ተበልቶ ስለነበረ መልሰው ሰፉት። እንዲህም አሉት፡ “ቶሎ ይሸነፋል፥ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ይሞታል፥ መጨረሻይ ይህ ነው። በቃ፡ ይጠፋል።”

205 እዚህ መድረክ ላይ ቆሜ፡ እንዴት እንደጸለይኩለት ታስታውሳላችሁ? ወርጄ ወደ ክፍሉ ገባሁ፡ በልቤ ውስጥ የሆነ ነገር እየበላኝ ነበር። ወደ ክፍሉ ገባሁ፡ እንደገባሁ ሌሎቹ ሁሉ ወጡልኝ... ወንድም ኤቨረት ተኝቶ ነበር። መቼም ይህን ታስታውሳላችሁ። ገባሁና፥ እንዲህ አልኩት፡ “ወንድም—ወንድም ባስቲ።” (ባስቲ ብዬ እጠራው ነበርና።)

206 ከረጅም ጊዜ በፊት የብራሽ አርቦር ስብሰባዎችን ስናደርግ፡ በዚያ በኮረብቶች ላይ የነበሩ ሜቶዲስቶች (ገርቲ፡ አንዷ ነበረች)፡ ተደብቀው እየመጡ፡ የምናገረውን ለማየት በወይኑ እርሻው ውስጥ እየሾለኩ ነበር፡ እና፡ የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ታወግዘናለች ብለው ፈርተው ነበርና። እና፡ ሄጄ እዚያ ራእይ አየሁ፡ እና በጣሳ ውስጥ የተከመረ ስጋን አየሁ። ብዙ ዓሳዎችን ያዝኩና ሁሉንም አሰርኳቸው፡ መንጠቆው ላይ እ—አንጠለጠልኳቸው፡ ከዚያ መንጠቆውን ጠመጠምኩት። እና ስመለከት... ይህ ሁሉ በራእይ ነበር፥ ያን ቀን ማታ ብዙ ሰዎችን ከብራሽ አርበር ስር ት—ትቼ ወደ ወንድም ራይት ወደ ኮረብታው ወጣሁ። እና በሚቀጥለው ቀን ጠዋት እንኳን ሊያገኙኝ አልቻሉም። እንዲህ አልኳቸው፡ “እንዳችሁም... ”

207 እና ቆሜ እየሰበክሁ ሳለሁ፡ እነሆ ያ ብርሃን መጣ፥ የእሳት ዓምድ በፊቴ ተንጠልጥሎ “ይህን ሰፍራ ለቀህ ወደ ጫካዎቹ ውረድ፡ በዚያም ከአንተ ጋር እናገራለሁ፡” አለኝ። በዚያው ቀን ነበር፡ በማግስቱ ኮረብታው ላይ አገኙኝ። እኔም መኪናዬን በአረም ውስጥ ደብቄ፡ በዚያ ላይ ነበርኩ፡ ሌሊቱን ሙሉ እና በማግስቱ ሁሉ ሲጸልይ ወደ ተራራው ላይ ነበርኩ። አንዳንዶቹ መጥተው መኪናውን አገኙና፡ ወደዚያ ወጡ... ወንድም ግርሃም ስኔሊንግ፡ እዚህ ጋር፡ መንፈስ ቅዱስን እና የአገልግሎት ጥሪን የተቀበለው ያን ቀን ነበር።

208 ተኝቼበት በነበረው እዚያ ኮረብታው ላይ፡ አብረን ስለምንነጋገርባቸው ነገሮች እና ብዙ ነገሮች እንዳደርግ ነ—ነገረኝ። በመያዣ ላይ የተንጠለጠሉትን የአሳዎቹን ራእይ ስጠና፡ “ይህ የሚልታውን ቤተ ክርስቲያንህ ነው፡” አለ።

ከእነርሱም አራት ወይም አምስት ተፈናጥረው ወጡ፥ እኔም ጠየቅኩ፡ “እነማን ናቸው? ”

“ከመካከላቸው አንዱ ጋይ ስፔንሰር እና ሚስቱ ናቸው። ሌላኛው ሌላ ስፔንሰር ነው፡ እና የእነሱ የሆኑት፡” ናቸው አለኝ። እና ለተለያዩ ሰዎች፡ ምን እንደሚፈናጠር ነገራቸው።

209 እኔም ነገርኳቸው፥ “ማናችሁም እንዳትበሉ፡” አልኳቸው። እኔና ሚስቴ ገና... አልተጋባንም ነበር፥ እና ከእህት ስፔንሰር ድንቅ እህት ጋር፡ ሌሊቱን ሙሉ ከሷ ጋር ለማደር ወደ ቤቷ ሄደች። ጋይ ስፔንሰርም፡ በቆዳ ጫማ ውስጥ ከቆሙ ሰዎች ሁሉ ድንቅ የሆነ ሰው ነው። እርሱም––ወደዚያም ወረደ፡ ኦፓልም ሚዳን፡ “አሁን፡ ይኸውልሽ... ” አለቻት፡ እንዲህ አለቻት፡ “ይኸውልሽ፡ ሚዳ፡ እኔ ወንድም ቢልን አምነዋለሁ።” “ኦፓል ሲርባት ግን፡ ሃምና እንቁላል መብላት አለባት፡” አለች። እሷም ወደዚያ ሄዳ፡ እንቁላሎቿን እና ሃሟን ጠብሳ፡ ልትበላው ተቀመጠችና፡ መባረክ ጀመረች፡ እና ጠረጴዛውን ተደግፋ፡ አለቀሰች፡ መንካት አልቻለችም። ከዚያም ወደ አደን መጡ።

210 እናም በዚያ ቀን በኮረብታው ላይ፡ ምን እንደሚሆን በትክክል ነገረኝ። እንዲህም አለ፡ “እነዚህ ይሄዳሉ፡ እና እነዚህ ሁሉ ይሄዳሉ።” እርሱ ግን ትልቅ የታሸገ-ሥጋ ይዞ ነበር። እንዲህም አለኝ፡ “ይህንን ለወደፊት ለሚልታውን ህዝብ አቆየው።” እና በቀደም ምሽት ወንድም ክሪችን ሰማሁት... ትናንት ማታ እዚህ ቁጭ ብሎ ነበር። እንጂ... ወንድም ክሪች፡ ዛሬ ማታ እዚህ አለህ? ወንድም ክሪች ወደ እኔ ሲመጣ፡ ጠራኝ እና፡ እህት ክሪች፡ አባቷ ተጋድሞ ስለነበረ፥ እያለቀሰች ነበር። “ወንድም ቢል፡ እንዳትነግረው፡ እየሞተ ነው፡” አለኝ። “በካንሰር ተበልቷል፥ ዶክተሮቹ ከፍተውታል፡ ሙሉ በሙሉ በካንሰር ተወሯል፡” አለኝ። እና ዊል ሆል (ሁላችሁም ታስታውሱታላችሁ)፡ ያንኑ ዶክተር ቀዶ ጥገና ባደረገለት ጊዜ በጣም በካንሰር ተሞልቶ ነበር... በዚያ ቀን ጠዋት ሽኮኮ ለማደን መንገድ ጀምሬ ነበር፡ እና በዚያ ክፍል ውስጥ የተንጠለጠሉ አፕሎች አይቼ ነበር። (ይህን ታሪክ ታስታውሱታላችሁ? ) እናም ሰውዬው ዛሬ በህይወት አለ። ከዓመታት በፊት ነው። እሱ እና ወንድም ባስቲ ጓደኛሞች ነበሩ።

211 እና ወደ ሆስፒታሉ ወረድኩ፡ አዲሱ ሆስፒታል (ስሙን ረሳሁት፡ በኒው አልባኒ ነው) አዲሱ ሆስፒታል። እና ባስቲን ለማየት ሄድኩኝ፥ ወደ ክፍሉ ገብቼ፡ “ወንድም ባስቲ፡” አልኩት።

እሱም “ወንድም ቢል፡” አለኝ። በዚያ ወፍራም የእጅ መጨባበጥ እጄን ያዘ፥ የአንደኛው የዓለም ጦርነት አርበኛ ነበር፡ በፊቱ አልናገርም፡ ነገር ግን ባረጀ ሰማያዊ ሸሚዝ ስር እንደሚመታ ጥሩ ልብ። እጄን ያዘኝ። በቤቱ ውስጥ ኖሬአለሁ፥ በቤቱ ውስጥ በልቻለሁ፥ በቤቱ ውስጥ ተኝቻለሁ፡ ልክ እንደ ወንድሙ ነበርኩ። ከልጆቹ ጋር፡ ልክ እንደ––እንደ ዘመዳሞች ነን። መልካም ሰው ነው።

212 እርሱም... በጌታ ዘንድ ጨርሶ አልመጣም ነበር። እ... በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጠመቅኩት። ነገር ግን በዚያ ቀን ያ የሜቶዲስት ሰባኪ፡ “በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የተጠመቃችሁ ሁሉ፡ ከጉባኤዬ ሥር ውጡ ባላቸው ጊዜ።” ደህና ነበር። ጆርጅ ራይት እና ሌሎቹ ወጡ። በዚያ ቀን ከሰአት በኋላ በቶተን ፎርድ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለማጥመቅ ወደዚያ ወረድኩ። መላው

ጉባኤው በውኃ ውስጥ ገብቶ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቀ። ዝም ብዬ ቀጠልኩ። ምንም ችግር አልነበረም። እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ከሆነ፡ ማን ይቃወማችኋል? ሰውዬው የት እንደሄደ፡ ምን እንደደረሰበት እንኳ አላውቅም።

213 ብቻ፡ ወደ ሆስፒታሉ ገባሁ። በካንሰር ተጠቅቶ ተጋድሞ ነበር፡ ዶክተሮች ሊረዱት አልቻሉም፡ ምንም ሊያደርጉለት አልቻሉም ብቻ መልሰው ሰፉት። ባስቲ እንዲህ አለኝ፡ “ወንድም ቢል፡ ይህ በዓላማ ሆኗል። የሆነ ነገር ሆኗል፡” አለኝ።

እኔም “አዎን፡ ባስቲ፡” አልኩት። እና እንደምታውቁት፡ ሁልጊዜ የምናገረው ልክ እንደሚነጥቅ ንፋስ መሳይ ሲመጣ፡ የመንፈሱ ስሜት ይሰማኝ ጀመረ።

እንዲህ… ወደዚህ ሰገባ፡ በዚያ ጥግ ላይ ቀስተ ደመና ነበረ፡ በዚያ ጥግ ላይ ቆሞ ነበር። ቀስተ ደመና ቃል ኪዳን ነው፥ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን። በዚያም ቀን እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። እጆቼን በወንድም ባስቲ ላይ ጫንኩኝ እና ጸልይኩለት።

ዶክተሮቹም፡ “እየተዳከመ ይሄዳል። ይሞታል። ምንም ማድረግ አይቻልም… በጥቂት ቀናት ውስጥ ይሞታል” ይሉ ነበር። ባስቲ ሮጀርስ ግን… ይህ ይሆነው የዛሬ ብዙ ብዙ ሳምንታት በፊት ነው፡ እና ባስቲ ሮጀርስ፡ ድሮ በህይወቴ እንደማውቀው ሁሉ ጤናማ እና ጠንካራ ሆኖ፡ እነሆ ዛሬ ማታ በቤተክርስቲያን ውስጥ ቁጭ ብሏል። እስኪ ተነሳ፡ ወንድም ባስቲ። ይኸውላችሁ። ሁላችንም፡ እግዚአብሔርን እናመሰግን።

በላይኛው ክፍል ውስጥ ተሰብስበው፡
ሁሉም በስሙ ሲጸልዩ።
በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ፡
ለአገልግሎትም ኃይል መጣ።
አሁን፡ በዚያ ቀን ያደረገላቸው
እንዲሁ ለእናንተም ያደርጋል።
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፥ (ሃሌ ሉያ!)
አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

እንዲህ ነን ባይሉም፡
የሚያውቃቸው ማንም ባይኖር፡
ሁሉም በዓለ ሃምሳን ተቀብለዋል፡
በኢየሱስ ስም ተጠምቀዋል፥
በሩቅ በቅርብ ያሉትን እየተናገሩ፡
ኃይሉ አሁንም አንድ ነው እያሉ።
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፥ (ሃሌ ሉያ!)
አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

አሁን፡ ና፡ ወንድሜ፡ ይህን በረከት ፈልግ
ይህም ልብህን ከኃጢአት ያነጻል፡
የደስታ ቃጭሎች ማስማት ይጀምራል
የነፍስህን ነበልባል ሁሌ ይጠብቃል፥
ኦህ፡ አሁን በልቤ ውስጥ እየነደደ ነው፡
አቤት፡ ክብር ለስሙ ይሁን፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

እንዘምረው!

ኦህ፡ አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አ ንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፥ (ሃሌ ሉያ!)
አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

እስኪ ስንቶች አንዱ ናችሁ? እጆች ይነሱ። ኦህ፡ ማይ! ኦህ፡ አንዱ በመሆኔ እንዴት ደስ ብሎኛል!

አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፥ (ሃሌ ሉያ!)
አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

በላይኛው ክፍል ውስጥ ተሰብሰበው፡
ሁሉም በስሙ ሲጸልዩ፡
በመንፈስ ቅዱስ ተጠመቁ፡
ለአገልግሎትም ኃይል መጣ፥
አሁን፡ በዚያ ቀን ያደረገላቸው
እንዲሁ ለእናንተም ያደርጋል፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

ኦህ፡ አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፥ (ሃሌ ሉያ!)
አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

አሁን፡ ያንን ዝማሬ እንደገና እየዘመርን ሳለ፡ እያንዳንዳችሁ ዘወር እንድትሉ፡ እና በአጠገባችሁ ያለውን ሰው ሰላም እያላችሁ፡ "አንተስ አንዱ ነህን?" እንድትሏቸው እፈልጋለሁ፡ አያችሁ? በጣም ጥሩ።

ኦህ፡ አንዱ ነኝ፡ (ወንድም ኔቪል፡ እንደሆንህ አውቃለሁ። ወንድም ካፕስ፡ እንደሆንክ አውቃለሁ። አንተ መሆናችሁን አውቃለሁ። እንደሆናችሁ አውቃለሁ... ? ... )
... አንዱ ነኝ፥
ኦህ፡ አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

214 ኦህ፡ ከእነርሱ አንዱ በመሆናችሁ ደስ አይላችሁምን? ሰንቶች መሆን ትፈልጋላችሁ? እጆች ይነሱ። እሺ። አሁን፡ እኔ እዘምርላችኋለሁ፥

እንግዲህ ወንድሜ ና፡ ይህን በረከት ፈልግ
ይህም ልብህን ከኃጢአት ያነጻል፡
የደስታ ቃጭሎች ማሰማት ይጀምራል፡
የነፍስህን ነበልባል ሁሌ ይጠብቃል፥
ኦህ፡ አሁን በልቤ ውስጥ እየነደደ ነው፡
አቤት፡ ክብር ለስሙ ይሁን፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

ኦህ፡ አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፥ (ሃሌ ሉያ!)
አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

215 ልጅቷ ለጴጥሮስ የተናገረችውን አስታውሱ፡ "አንተ ከነሱ አንዱ አይደለህምን?" በጣም ደስ ብሎኛል፡ እናንተስ? ታውቃላችሁ፡ ጴጥሮስ በጴንጤቆስጤ ቀን እንዲህ አለ፡ "ይሄ ነው!" አሁን፡ ሁሌም እላለሁ፡ "**ይህ ያ** ካልሆነ፡ **ያ** እስኪመጣ ድረስ በመጠባበቅ፡ **ይህንን** በማግኘቴ ደስተኛ ነኝ።" ትክክል ነው። **በዚህ** ደስ ብሎኛል።

አንዱ ነኝና፡ አንዱ ነኝ
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ፥
ኦህ፡ አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

216 ኦህ፡ በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ሰፍራ መሰባሰብ፡ ከመንፈስ ጋር መነጋገር፡ ውደ ቃሉ መቅረብ፡ ስለሚመጣው መልካም ነገር ማውራት፡ ይህ አስደናቂ አይደለምን። በጣም መልካም ነው። ያንን በማወቄ በጣም ደስ ብሎኛል፡ እናንተስ? ክርስቲያን በመሆናችሁ ደስተኞች ናችሁ? ኃጢአቶቻችሁ በደሙ ሥር በመሆናቸው ደስተኞች አይደላችሁምን? ከእነዚህ ቀናት በአንዱ ይመጣል፡ እኛም ከእሱ ጋር እንሄዳለን። ያን ጊዜ አስቡት፡ እርጅና ሁሉ ከእኛ ይወገዳል፥ በሽታ ሁሉ፡ ህመሞች በሙሉ፡ የሟች ሕይወት ሁሉ ይለወጣሉ። ኦህ፡ ማይ! እዚህ ቆመው የነበሩ አንጋፋ ወንድሞች ትዝ ይሉኛል። አስታውሳለሁ… ራቢ ሎሰንን ሰንቶች ታስታውሱታላችሁ? አቤት፡ አብዛኞቻችሁ። ያን ዘንጉን ይዞ ትዝ ይለኛል። እኔም ከኋላ እዚህ ጋር ቁጭ ብዬ። እንዲህ የምትለዋን መዝሙር ይዘምር ነበር… (አንዴ፡ ወንድም ቴዲ።) ዜማውን ከተጫወተልኝ፡ ልሞክረው። እንጃ።

ነገ ደስታን ይጠብቀኛል፡
የእንቁ በሮች በሰፊው የሚከፈቱበት፡
እናም ይህን የሃዘን ሸለቆ ሰሻገር፡
እርፋለሁ ከወዲያ ማዶ።

አንድ ቀን የሟች አእምሮ ከማይደርስበት፡
አንድ ቀን፡ መቼ እና የት እግዚአብሄር ያውቃል፡
የሟች ህይወት መንኮራኩሮች ሁሉ ሲቆሙ፡

ያን ጊዜ በጽዮን ተራራ ለመኖር እሄዳለሁ። (እዎን።)

217 በውስጣችን እየዞሩ ያሉት እነዚህ ትናንሽ መንኮራኩሮች— በዚህ ሟች ህይወት ውስጥ የሚዞሩ ትንንሽ ስሜቶች እና መንኮራኩሮች፡ ማየት፡ መቅመስ፡ መዳሰስ፡ ማሽተት፡ እና መስማት ናቸው፡ አንድ ቀን ጸጥ ይላሉ። ያን ጊዜ እኔ፡ ራሴና፡ እናንተም፡ በጽዮን ተራራ ላይ ለመኖር እንሄዳለን። ኦህ፡ ይህ ደስ ይለኛል፡ እናንተስ? ያንን የተባረከ ዋስትና እንዳለን እወቁ። እሺ። የጥንቱን የጥምቀት ዝማሬያችንን ስንቶች ታውቁታላችሁ? አሁን፡ እንለውጠዋለን። የማስናበቻ መዝሙር እንዘምር፥

የኢየሱስ ስም ከናንተ ጋር ይሁን፡
የሀዘንና የዋይታ ልጅ፥
ደስታ እና ምቾት ይሰጣል፡
በሄዳችሁበት አትለዩት።

218 የኢየሱስን ስም ከእናንተ ጋር ይሁን። በመንገድ ላይ፡ ይህ ይሁንላችሁ። በጣም ጥሩ፡ አንድ ላይ አሁን። አትርሱ፡ ከጠዋቱ ሰምንት ሰዓት ላይ የጸሎት ካርዶች ለስብሰባው ይሰጣሉ። ስብሰባው ዘጠኝ-ተኩል ላይ ይጀምራል። አሰር ላይ እሰብካለሁ። ለታመሙ የጸሎት አገልግሎት በአሰራ አንድ ሰዓት አካባቢ ይጀምራል።

219 ነገ ከሰአት በኋላ፡ ነገ ምሽት በተበርናክሉ ውስጥ የሰብከተ ወንጌል መልእክት ይሆናል። ነገ ማታም፡ ከኃጢአታችሁ ንሰሐ የገባችሁ እና ያልተጠመቃችሁ ሁሉ፡ ጥምቀት ይኖራል… ገንዳው ክፍት ይሆናል፥ ሕዝቡን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም እናጠምቃለን።

220 አሁን ሁላችንም በአንድነት፡ ድምፃችንን ከፍ አድርገን እንዘምረው። ወንድም ባሰቲ፡ ምን ያህል ደስተኛ እንደሆንኩ እና ምን ያህል እግዚአብሔርን እንደማመሰግነው አላውቅም። ታውቃላችሁ፡ ወደ ዶክተሩ ሄዶ ነበር። እና እንደነገሩኝ ዶክተሩ ፍጥጥ ብሎ ተመለከተውና፡ ምን ማሰብ እንዳለበት ጠፋው። ያንኑ ሰውዬ መሆኑን ማወቅ ተሳነው። ኦህ፡ የእግዚ አብሔር ስራ ምሰጢር አይደለም። ልክ ነው? በጣም ጥሩ።

ሰሙን ውሰዱ….

አንቃጭሉት!

… ካንተ ጋር፡
የሀዘንና የዋይታ ልጅ፡
ደስታ እና ምቾት ይሰጣል፡
ስለዚህ፡ በሄዳችሁበት ከእናንተ ጋር ይሁን።

ድንቅ ስም፡ (ድንቅ ሰም!) ኦህ ውብ ሰም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ሰም፡ (ኦህ፡ ድንቅ ሰም!) ኦህ ውብ ሰም!
የምድር ተሰፋ የሰማይ ደስታ።

221 እሺ። ጉባኤውን አሁን ወደ ፓስተር አሳልፋለሁ። ጥቂት ቃላት ይናገራል፡ ወይም በጸሎት እንዲዘጋልን ሌላ ሰው ይጋብዛል፡ እንዳሰበው ይሁን።

59-1219 ጥያቄ እና መልስ በመንፈስ ቅዱስ ዙርያ
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org